# በኢየሱስ እናምናለን

# ትምህርት አራት

# ካህን

# We Believe in Jesus

## Lesson Four

## The Priest

**ተርጓሚ፡ እሽቴ በለጠ**

THIRD MILLENNIUM MINISTRIES

Biblical Education. For the World. For Free.

## ማውጫ


1. **መግቢያ**
2. **ብሉይ ኪዳናዊ ዳራ**

መመዘኛዎች

በእግዚአብሔር  የተሾመ

ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆነ

ተግባር

መሪነት

ሥርዓቶች

ምልጃ

ጥበቃዎች

ታሪካዊ እድገት

ፍጥረት

ውድቀት

ዘፀአት

ንጉሣዊ አገዛዝ

ግልፅ/ውስን ትንቢቶች

3. **ምልዓት በኢየሱስ**

መመዘኛዎች

በእግዚአብሔር የተሾ መ

ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆነ

ተግባራት

መሪነት

ሥርዓቶች

ምልጃ

ጥበቃ

ታላቁ ሊቀ ካህን

ካህን እንደ ንጉሥ

የካህናት መንግሥት

4. **ዘመናዊ ተዛምዶ**

መስዋዕት

መታመን

አገልግሎት

አምልኮ

እርቅ

ሰላም

አንድነት

ተልዕኮ

ምልጃ

ልመና

ጠበቃ

## 5. ማጠቃለያ

# 1. መግቢያ

አብዛኛዎቻችን በአንድ ታዋቂ ሰው ብጠራ ብለን አንዳንድ ጊዜ በምናባችን እናሰላስላለን፡፡ ያም ቢሆን እንዴት እንዴት ልንሆን እንደሚገባንም እናስባለን፡፡ ራሳችንንም እንዲህ ብለን እንጠይቃለን፡፡ "የሚያስተዋውቀኝ ሰው ይኖር ይሆን? ምን መልበስ አለብኝ? ምን ማድረግስ ይገባኛል? ምን መናገር አለብኝ? እዚያ ስደርስ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ማን ያሳየኛል?"

እስኪ እንግዲህ እጅግ በከበረው የእግዚአብሔር ዙፋን ባለበት ክፍል ውስጥ ስለመገኘት አስቡ፡፡ እርሱ የሁሉ ነገር ፈጣሪ ነው፡፡ ስለዚህም ተመሳሳይ የሆነ እንዲያውም እጅግ ከዚያም የጠነከረ ስሜት ይሰማናል፡፡ "እኔን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስተዋውቀኝ አንድ ሰው ይኖር ይሆን? ምን ላደርግ ይገባኛል? ምንስ መናገር አለብኝ? በእግዚአብሔር ፊት እንዴት መሆን እንደሚገባኝ ማን ያሳየኛል?"

ደስ የሚያሰኘው ነገር፣ ከእግዚአብሔር ጋር እንገናኝ ዘንድ የሚያዘጋጀን፣ እኛንም ከእርሱ ጋር የሚያስተዋውቀን፣ እግዚአብሔርም በርኅራኄ እንዲመለከተንና ፍርዱንም እንዳንፈራ የሚያደርገን አንድ አለ፡፡ ያም ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፣ እርሱ ታላቁ ሊቀ ካህናችን ነው፡፡

በኢየሱስ እናምናለን ከሚለው ተከታታይ ትምህርታችን ይህ አራተኛውና "ካህን" የሚል ርዕስ የሰጠነው ትምህርት ነው፡፡ በዚህ ትምህርት፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የክህነት አገልግሎት ማለትም በእግዚአብሔርና በህዝቡ መካከል መካከለኛ የመሆንን አገልግሎት ኢየሱስ እንዴት እንዳሟላ እንዳስሳለን፡፡

ቀደም ባሉት ትምህርቶች እንደተመለከትነው፣ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር መንግሥቱን የሚያስተዳድርባቸውን ሦስት ቢሮዎች እንደመሠረተ ተመልክተናል፡፡ ቢሮዎቹም የነቢይ፣ የካህንና የንጉሥ ናቸው፡፡ አዲስ ኪዳን በማለት በምንጠራው የእግዚአብሔር መንግሥት የመጨረሻ እርከን ውስጥ ሦስቱም አገልግሎቶች በኢየሱስ የመደምደሚያ ፍፃሜያቸውን አግኝተዋል፡፡ በዚህም ምክንያት፣ በታሪክ ውስጥ የእነዚህን አገልግሎቶች አስፈላጊነትና ተግባር ማጥናታችን ኢየሱስ በዚህ ዘመን የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዴት

እያስተዳደረ እንደሆነና የእርሱን ታማኝ ተከታዮች ግዴታና በረከቶችን በአግባቡ ለመገንዘብ ያስችለናል፡፡ በዚህ ትምህርት፣ በኢየሱስ የካህንነት አገልግሎት ላይ እናተኩራለን፡፡

ካህንን እንደሚከተለው እንተረጉመዋለን፡

በእግዚአብሔርና በህዝቡ መካከለኛ ሆኖ የሚቆም እግዚአብሔርም ከእርሱ የተነሣ ወደተቀደሰው ጎላዌው ሰዎችን የሚያቀርብበትና በረከቱንም የሚያስተላልፍበት ሰው ነው፡፡

ሁላችንም እንደምናውቀው እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በሁሉም ስፍራ በዐይን የማይታይ ሆኖ ይኖራል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ግን፣ ራሱን ግልፅ በሆነና በተለየ መንገድ የሚገልጥበትም ጊዜ አለ፡፡ ለምሳሌ፣ በሰማያት ያለውን የዙፋኑን ውበትና ግርማ የገለጠበት ጊዜ አለ፡፡ አንዳንድ ጊዜም ይህንን በምድርም ላይ ያደርጋል፡፡ እናም ፍጥረታት ይህንን በመሰለው የእግዚአብሔር ማንነት መገለጫ ወደ እኛ በሚቀርቡ ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን የመገለጡን ባርኮት ለመቀበል፣ በሚገባ ልንዘጋጅ፣ በአግባቡ ልንወከልና ልንመራ ይገባናል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ ይህንን መሳዩ የማዘጋጀት፣ የመወከልና የመምራት ሥራ የካህናት ሥራ ነው፡፡

ልክ ስለ ኢየሱስ የነቢይነት አገልግሎት እንደተማርንበት ትምህርት ሁሉ፣ አሁን የምናየው የኢየሱስ የክህነት አገልግሎትም ሦስት ርዕሶችን ይሸፍናል፡፡ በመጀመሪያ፣ የካህናትን አገልግሎት ብሉይ ኪዳናዊ ዳራ እንመረምራለን፡፡ ሁለተኛ፣ ይህ አገልግሎት በኢየሱስ ስብዕናና ሥራ እንዴት እንደተፈፀመ እንቃኛለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ የኢየሱስን የካህንነት ሥራ ዘመናዊ ተዛምዶ እንመለከታለን፡፡ እስኪ በመጀመሪያ የኢየሱስን የካህንነት አገልግሎት ብሉይ ኪዳናዊ ዳራ እንመልከት፡፡

## 2. ብሉይ ኪዳናዊ ዳራ

አብዛኞቹ ክርስቲያኖች በብሉይ ኪዳን ስለነበረው የክህነት አገልግሎት ሲያስቡ አዕምሯቸው ፈጥኖ የሚሄደው በዘሌዋውያን ምዕራፍ 8 እና 9 ወደ ተጠቀሱትና በሙሴ ዘመን ካህናት እንዲሆኑ ወደተሾሙት ወደ አሮንና ወደ ዝርያዎቹ ነው፡፡

ነገር ግን ከሙሴም ዘመን ቀደም ብሎ እንኳን፣ እግዚአብሔርን ያገለገሉ ካህናት እንደነበሩ እውቅና መስጠት ጠቃሚ ነው፡፡ ሰፋ ባለ ሁኔታም ስንመለከተው፣ የሰው ልጆች ሁሉ አባት የሆነው አዳም፣ በኃጢአት ከመውደቁ አስቀድሞ እግዚአብሔር የእርሱ ካህን እንዲሆን መርጦት ነበር፡፡ ከአዳምም ቀጥሎ፣ የሰው ልጆች ሁሉ የእግዚአብሔር ካህናት እንዲሆኑ ተጠርተዋል፡፡

ከዚያ ጠለቅ ባለው መንገድ ስንመለከተው ደግሞ፣ በአብርሃም ዘመን መልከ ጼዴቅ የተሰኘውንና በዘፍጥረት ምዕራፍ 14 የተጠቀሰውን ሰው እናገኘዋለን፡፡ እርሱ የሳሌም ንጉሥና ካህን ነው፡፡ በኢዮብ ምዕራፍ 1 ስንመለከት ኢዮብን ራሱን ለቤተሰቡ እንደ ካህን ሲያገለግል እናገኘዋለን፡፡ ዘፀአት ምዕራፍ 3 ስናነብብ ደግሞ፣ የሙሴ አማት ዮቶር በምድያም የእግዚአብሔር ካህን ነበር፡፡ በስተመጨረሻ ደግሞ፣ እግዚአብሔር አሮንና ቤተሰቡ ሌሎቹን ዓይነት ክህነቶች በመተካት ይፋ የሆነና ሁሉን አቀፍ የሆነ የክህነት አገልግሎት እንዲሰጡ ሾማቸው፡፡ እነዚህ የተለያዩ ሰዎች ግን የጌታ እውነተኛ ካህናት ሆነው አገልግለዋል፡፡ እያንዳንዳቸውም የኢሱስ የክህነት አገልግሎት ብሉይ ኪዳናዊ ዳራ አካል ናቸው፡፡

የክህነትን አገልግሎት ብሉይ ኪዳናዊ ዳራ በሦስት መንገዶች እንዳስሰዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የካህንን መመዘኛ እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ ተግባራቸውን እንዳስሳለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ወደፊት ከሚመጣው የክህነት አገልግሎት ብሉይ ኪዳን የሚጠብቃቸውን እናያለን፡፡ አስቀድመን በብሉይ ኪዳን ካህናት ሊያሟሉ የሚጠበቅባቸውን እንመልከት፡፡

## መመዘኛዎች

የጥንቱ ካህናት እንዲያሟሉ የሚጠበቅባቸው የተለያዩ መመዘኛዎች አሉ፣ እኛ ግን ቅዱሳት መጻሕፍት ትኩረት የሰጡባቸውን ሁለቱን እንጠቅሳለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ካህናት በእግዚአብሔር የተሾሙ መሆኑን እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ ያለባቸውን ለእግዚአብሔር ታማኝ የመሆን ግዴታ አፅንዖት እንሰጠዋለን፡፡ ካህናት በተሰጣቸው ቢሮ እግዚአብሔርን ለማገልገል የተሾሙ መሆኑን በመመልከት እንጀምር፡፡

## በእግዚአብሔር መሾም

በብሉይ ኪዳን፣ ካህናትን የሚሾም እግዚአብሔር ብቻ ነበር፡፡ ካህናት በምንም መንገድ ራሳቸውን አይሾሙም፡፡ በድምፅ ብልጫም ወደ ቢሮው አይመጡም፡፡ በነገሥታት ወይንም በሌሎች ገዢዎችም አይሾሙም፡፡ ካህናት ራሳቸው እንኳን በምትካቸው የሚያገለግሉ ሰዎችን መምረጥ አይችሉም፡፡

በዘፀአት ምዕራፍ 28 ቁጥር 1፣ እግዚአብሔር ለሙሴ እነዚህን ትዕዛዛት ሲሰጥ የተናገረውን አድምጡ

አንተም ወንድምህን አሮንን ከእርሱም ጋር ልጆቹን ከእስራኤል ልጆች መካከል ለይተህ ካህናት ይሆኑልኝ ዘንድ ወደ አንተ አቅርብ አሮንን የአሮንንም ልጆች፥ ናዳብን አብዮድንም አልዓዛርንም ኢታምርንም፥ አቅርብ።

በዘፀአት ምእራፍ 28 ተከታትሎ የሚመጣው ዝርዝር መመሪያ አሮንን ሊቀ ካህን እንዲሆን እግዚአብሔር የሾመው ሹመት ፈጽሞ ሊተካ የሚችል እንዳልሆነ ያመለክታል፡፡ ዘኁልቁ ምዕራፍ 18 ቁጥር 22 እና 23 ደግሞ ነገሩን ገፋ ያደርገውና ከእስራኤል ነገዶች ማንኛውም የካህንን ሥራ ሢሠራ ቢገኝ፣ ያ ሰው ይሞታል ብሎ ይናገራል፡፡

ዕብራውያን ምዕራፍ 5 ከቁጥር 1 እስከ 4 ደግሞ ሃሳቡን በእነዚህ ቃላት ያረጋግጣል፡

> ሊቀ ካህናት ሁሉ ስለ ኃጢአት መባንና መስዋዕትን ሊያቀርብ ከሰው
> ተመርጦ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ ስለ ሰው ይሾማልና፤
> እርሱ ራሱም ደግሞ ድካምን ስለሚለብስ፥ ላልተማሩትና ለሚስቱት
> ሊራራላቸው ይችላል፤
> በዚህም ምክንያት ስለ ሕዝብ እንደሚያቀርብ እንዲሁ ስለ ራሱ
> ደግሞ መስዋዕትን ስለ ኃጢአት ሊያቀርብ ይገባዋል።
> እንደ አሮንም በእግዚአብሔር ከተጠራ በቀር ማንም ክብሩን ለራሱ
> የሚወስድ የለም።

ይኸው ተመሳሳይ መርህ ለሊቀ ካህኑ ብቻ ሳይሆን፣ በብሉይ ኪዳን ለነበሩ ከካህናት ሁሉ ይሠራል፡፡

ካህናት በእግዚአብሔር ከመሾማቸው ባሻገር፣ ለአገልግሎቱ ብቁ ይሆኑ ዘንድ ለእግዚአብሔር የታመኑ እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡

## ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን

ካህናት በመገናኛው ድንኳንና በመቅደሱ ውስጥ ለእግዚአብሔር ልዩ ጎላዌ ቅርብ ሆነው ስለሚያገለግሉ፣ እርሱን በማምለክና እርሱንም ብቻ በማገልገል፣ ሃላፊነቶቻቸውንም በጥንቃቄ በመፈፀም ለእግዚአብሔር የተለየ ታማኝነታቸውን ሊያሳዩ ይገባቸዋል፡፡ እነዚህንም ተግባራት ሲያከናውኑ የእግዚአብሔርም ህዝብ ወደ እግዚአብሔር ጎልውና የመግባትን እድል ያገኝ ዘንድ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሊሆን እንደሚገባው ተምሳሊት በሚሆን መንገድ ነው፡፡

*የብሉይ ኪዳን ካህናት ሊከተሏቸው የሚገቡ ልዩ ህግጋት እንዳሉ፣ የመስዋዕቱንም እሳት የሚያነድዱበት በጣም የተለየ መንገድ እንዳለ፣ ለመስዋዕት የሚቀርቡትም እንስሳት በእውነት እንከን የሌለባቸውና ፍፁም መሆናቸውን የሚመረምሩበትና የሚያረጋግጡበት የተረጋገጠ መንገድ መኖሩን፣ እንረዳለን፡፡ ይህም የሆነው እግዚአብሔር እንዲደረግ ስላዘዘ ነው፡፡ ካህኑ ሊለብሳቸው የሚገቡ የተወሰኑ ልብሶችም እንዳሉ፣ ሊያከናውናቸው የሚገቡ የተለያዩ የመታጠብ ሥርዓቶችም እንዳሉና የዕብራውያን መጽሐፍም የእነዚህን ነገሮች ዝርዝር የመገናኛውን ድንኳን ጨምሮ የሚገልፅልን ሲሆን፣ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የሚገኙ ነገሮች ሁሉ የተሰጡት ምክንያት፣ ስያሜያቸውን ያገኙበት ሰማያዊ ድንኳን፣ ማለትም የእግዚአብሔርን መገኛ የሚወክሉ በመሆናቸው መሆኑን ያስረዳናል፡፡ እንግዲያው ካህናቱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ይወክላሉ ማለት ነው፡፡ ውክልናቸውም፣ በክህነት ሥርዓቱ ውስጥ የሚከናወኑ ህግጋት ሁሉ የክርስቶስን ማንነትና እንከን አልባነቱን፣ የሕዝቡንም ኃጢአት ሊሸከም የተገባው መሆኑን በሚያመለክት ቅድስና፣ እኛንም ይቅር በማለት እግዚአብሔር የሚያገኘውን እርካታ በሚገልጥ መልክ ሊሆን ይገባዋል፡፡ የሚለብሷቸው ልብሶች፣ በላያቸውም የተጻፉት የየነገዱ ስሞች፣ የመስዋዕቶቹ እንከን አልባነት፣ እግዚአብሔር በጉዳዩ ላይ ምን ያህል ትኩረት እንደሰጠና የቅድስናውን ልክ የሚያመለክቱ ሲሆን፣ ወደ ነገሩ መደምደሚያም ስትመጡ ድነት የሚገኝበት መንገዱ አንድ ብቻ መሆኑንም እንደሚያመለክቱ ትገነዘባላችሁ፡፡ በዚያ አንድ ብቸኛ መንገድ ላይ ድርድር ቢኖርና እኛ የምናከናውነው ቢሆን ኖሮ እርካታ ቢስ በሆነ ነበር፡፡ ስለዚህ የክህነት ህግጋት የእግዚአብሔር ቅድስና እና ጽድቅ ጉዳይ ለድርድር የማይቀርብና ብቸኛውም መስዋዕት ክርስቶስ የመሆኑ ነገር በአዕምሯችን ውስጥ መስረፁ እጅግ ወሳኝነት አለው፡፡ [ዶ/ር ቶማስ ኔትለስ]*

ካህናት የተቀደሱ ሊሆኑ እንደሚገባቸው ከሚናገሩት መካከል እጅግ ድራማዊ በሆነ መንገድ ከተቀመጡት አንዱ በዘሌዋውያን ምእራፍ 10 ቁጥር 1 እና 2 ውስጥ ያለው

ነው፡፡ በዚያም፣ ካህናቱ ናዳብና አብዩድ ያልተቀደሰ መስዋዕት በማቅረባቸው ምክንያት እግዚአብሔር እንደቀሰፋቸው እንመለከታለን፡፡ በ1ኛ ሳሙኤል ምእራፍ 4 ደግሞ፣ ካህናቱ አፍኒንና ፊንሐስ ለእግዚአብሔር ክብርን ባለመስጠታቸው ሞተዋል፡፡

ከነዚህም ምሳሌዎች በተጨማሪ፣ መዝሙር 132 ቁር 9 እና ዕንባቆም ምዕራፍ 4 ከቁጥር 11 እስከ 13 የመሳሰሉት ክፍሎች ካህናት የእግዚአብሔር ህዝብ የእግዚአብሔርን በረከት ወደሚቀበልበት ኅልውናው ለመምራት የተገባቸው ይሆኑ ዘንድ ራሳቸው ለእግዚአብሔር የታመኑ ሊሆኑ እንደሚገባቸው ያሳዩናል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን፣ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አሰቃቂ ፍርድን ያስከትላል፡፡

በብሉይ ኪዳን ካህናት የሚሾሙባቸውን መመዘኛዎች ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ተግባራቸውን እንመልከት፡፡

## ተግባራት

የካህናትን ተግባራት ሦስት ገፅታዎች ቀጥለን እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የሚሰጡትን አመራር እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ የሚያስፈጽሟቸውን ስርዓቶች እንመረምራለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ በሌሎች ምትክ የሚያከናውኑትን ምልጃ እናያለን፡፡ አስቀድመን ካህናት በሚሰጡት አመራር እንጀምር፡፡

## አመራር

የብሉይ ኪዳን ካህናት ለእግዚአብሔር ህዝብ አመራር የሚሰጡት በተለያዩ መንገዶች ነው፡፡ ለአሁኑ ዓላማችን ግን እነዚህን በሦስት ከፍለን እንመለከታቸዋለን፡፡ አንደኛ፣ ካህናት አመራር ከሚሰጡባቸው ነገሮች ዋነኛው አምልኮ ነው፡፡

የእግዚአብሔርን ህዝብ ወደ እግዚአብሔር የተቀደሰ ኅልውና ለማስገባት የምናዘጋጅበትና የምንመራበት እጅግ አስፈላጊ ነገር አምልኮ ነው፡፡ በእስራኤል ውስጥ፣ የሚከናወነውን ብሔራዊ የአምልኮ በዓላት ማለትም ዓመታዊ በዓላቶችን የሚመሩት ካህናትና ሌዋውያን ናቸው፡፡ በመገናኛው ድንኳን እና በመቅደስ ውስጥ የሚከናወኑትን የየዕለት አምልኮዎች፣ እንዲሁም በሰንበት ዕለት የሚከናወነውን የተለየ አገልግሎትም ያከናውናሉ፡፡ ተሳታፊዎችንም በምስጋናና በዝማሬ ይመራሉ፡፡ እነዚህን የመሳሰሉ ዝርዝሮችን በ1ኛ ዜና ምዕራፍ 15፤ በ2ኛ ዜና ምዕራፍ 7፣8፣29 እና 30፤ በነህምያ ምዕራፍ 12 ውስጥ እናገኛቸዋለን፡፡

ሁለተኛ፣ ካህናት በህዝባዊና ልማዳዊ የፍርድ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ የተለያዩ አመራሮችን ይሰጣሉ፡፡ ይህንንም በተቀዳሚነት የሚያከናውኑት በሚጋፈጧቸው ሁኔታዎች ውስጥ የእግዚአብሔርን ህግጋት ተግባራዊ በማድረግ ነው፡፡ ይህም እውነታ፣ እንደ ዘፀአት ምዕራፍ 28 ቁር 29 እና 30፤ ዘኍልቁ ምዕራፍ 21 ቁር 27፤ ዘዳግም ምዕራፍ 21 ቁር 5 እና ሕዝቅኤል ምዕራፍ 44 ቁጥር 24 በመሳሰሉት ውስጥ ተጠቅሷል፡፡

ለምሳሌ፣ ሙሴ በዘዳግም ምዕራፍ 17 ቁጥር 8 እና 9 ላይ ካህናት የሚያከናውኗቸውን ማኅበራዊ የፍርድ ተግባራት የገለጠበትን መንገድ አድምጡ፡

> በደምና በደም፥ በፍርድና በፍርድ፥ በመቍሰልና በመቍሰል መካከል
> በአገርህ ደጅ ውስጥ ሰዎች ስለሚከራከሩበት ክርክር የሚሳንህ የፍርድ ነገር
> ቢነሣ፥ አንተ ተነሥተህ አምላክህ እግዚአብሔር ወደ መረጠው ስፍራ
> ትወጣለህ
> ወደ ሌዋውያን ካህናት በዚያም ዘመን ወደ ተሾመው ፈራጅ መጥተህ
> ትጠይቃለህ እነርሱም የፍርዱን ነገር ይነግሩሃል። (ዘዳ 17፥8-9)

ይህ ምንባብ እንደሚያመለክተው፣ ህጋዊ ጉዳዮች ይዳኙ የነበሩት በማኅበራዊ ሽንጎዎች ነበር፡፡ ለየት ያሉ አስቸጋሪ ጉዳዮች ሲመጡ ግን፣ ህዝቡ ልዩ ፍርድ ሊሰጡዋቸው ወደሚችሉት ካህናትና ዳኞች ዘንድ ይሄዳሉ፡፡

እንዲያውም፣ በዘፀአት ምዕራፍ 18 የምድያሙ ካህን ዮቶር ለእስራኤል ሽንጎዎችና ፈራጆች እውቅና እንዲሰጥ ሙሴን መክሮታል፡፡ የዮቶር ካህንነት እነዚህን ጉዮች አስመልክቶ ሥልጣን እንዲኖረው አድርጎታል፡፡

የካህናት ውሳኔዎችና አመራሮች በተጨማሪም ከጤናና ከቅድስና ጋር የተያያዙ ጉዳዮችንም የመመርመር፣ የመተርጎምና የመበየን ተግባራትንም ያካትቱ ነበር፡፡ ካህናት በቤት ውስጥ ለምፅ መኖሩን አለመኖሩን ያረጋግጣሉ፣ በሽታዎችን ይመረምራሉ፣ ከዚያም በእግዚአብሔር ህግ መሠረት ሰዎችን ወይንም ዕቃዎችን ንፁህ ወይም ርኩስ ብለው ይበይናሉ፡፡ እነዚህን የመሳሰሉ ካህናዊ ተግባራት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 11 እስከ 15 ባሉት ምንባቾች ውስጥ ተዘርዝረዋል፡፡

ማኅበራዊ የጤና ችግሮች ወደ ዓለም የገቡት እግዚአብሔር በአዳም ኃጢአት ላይ ያስተላለፈውን እርግማን ተከትለው በመሆኑና በዚህም አዳም በዔድን ገነት ከነበረው ከእግዚአብሔር ኅላዌ የተባረረ በመሆኑ እነዚህ ተግባራት የካህናት ተግባራት ናቸው፡፡ ዓለም አቀፋዊው የሞት እርግማን የተደነገገው በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ቁጥር

19 ላይ ነው፡፡ ዘሌዋውያን ምዕራፍ 26 ቁጥር 16 እና ዘዳግም ምዕራፍ 28 ከቁጥር 21 እስከ 28 ውስጥ እንደምንመለከተው፣ ይህ አጠቃላይ ፍርድ ከጤና ጋር የተያያዙ ሌሎች ፍርዶችንም አስከተለ፡፡ በዚህም ምክንያት፣ የጤና ጉዳዮች ህዝበ እስራኤልን ወደ እግዚአብሔር ኅልውና ለማቅረብና በረከቱን እንዲለምኑ ለማዘጋጀት ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል፡፡

በ2ኛ ዜና ምዕራፍ 35 ቁጥር 3 ፤ ነህምያ ምዕራፍ 8 እና ሚልክያስ ምእራፍ 2 እንደምናብበው፣ ካህናት አመራር የሚሰጡበት ሦስተኛ መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል ለህዝቡ ማስተማር ነው፡፡

> አንዱን ለምሳሌ ለመጥቀስ ያህል፣ በሚልክያስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 7 ላይ ጌታ የተናገረውን አድምጡ፡
>
> ካህኑ የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነውና ከንፈሮቹ እውቀትን ይጠብቁ ዘንድ ይገባቸዋል፥ ሰዎችም ሕግን ከአፉ ይፈልጉ ዘንድ ይገባቸዋል። (ሚልክያስ 2፥7)

የሃሰት ትምህርት በዓለም ላይ ኃጢአት ያመጣው ውጤት ሲሆን፣ የእግዚአብሔርን ህግ መተላለፍም ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ኅልውና የመግባት ብቃት እንዳይኖራቸው አድርጓል፡፡ ስለዚህም፣ ካህናት የእግዚአብሔርን ህዝብ ወደ እግዚአብሔር ኅልውና በመቅረብ በረከቱን መቀበል እንዲችል ለማዘጋጀትና ለመምራት ይችሉ ዘንድ የእግዚአብሔርን ቃል የማስተማር ሥራ ተሰጣቸው፡፡

ካህናት የሚሰጡትን አመራር ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ለህዝባቸው የሚያስፈፅሟቸውን ሥርዓቶች እንመልከት፡፡

## *ሥርዓቶች*

> *በብሉይ ኪዳን አማኞች መካከል፣ የሚከናወኑት የተለያዩ ክብረ በዓላት፣ የሰንበት በዓል፣ የሚቀርቡ መስዋዕቶች ሁሉ የሚጫወቱት ወሳኝ ሚና አላቸው፡፡ ከሁሉ የሚቀድመው፣ የእስራኤል ህዝብ እንደ እግዚአብሔር ህዝብ እንዲሆን የተሰጠው ሕይወት የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን ማሳሰብ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ፋሲካ የሚሳስባቸው በአንድ ወቅት በግብጽ ባርነት ውስጥ እንደነበሩና እግዚአብሔርና እግዚአብሔር ብቻ ነጻ እንዳወጣቸው ነው፡፡ ነፃ መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን፣ ከግብጽ ነፃ የወጡት እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን ወደ ገባበት ወደ ሲና ይወሰዱ ዘንድ መሆኑንም ጭምር ነው፡፡ ስለዚህ በእስራኤል*

*የሚከናወኑ በዓላት ሁሉ እግዚአብሔርና እግዚአብሔር ብቻ የራሱ ህዝብ ይሆኑለት ዘንድ እንደመረጣቸው እና እግዚአብሔር እነርሱን ለማዳን የሠራውን ሥራ እንዲያሳስቧቸው ነው፡፡ ሰንበታቶቹ፣ ዓለም የያህዌ መሆኗን እና ራሳቸውን እንዳልፈጠሩ እናም ራሳቸውን ከባርነት ነፃ ማውጣት እንደማይችሉ እነዚህን ሁለት ነገሮች ያሳስቧቸዋል፡፡ በዘፀአት፣ ሙሴ "ሰንበትን አክብሩ፣ በሰባተኛው ቀን እግዚአብሔር ከሥራው አርፏልና" በማለት ተናግሯል፡፡ በዘዳግም መጽሐፍ፣ ሙሴ ሰንበትን የምታከብሩት እግዚአብሔር ስላረፈበት ብቻ ሳይሆን፣ እናንተም በአንድ ወቅት በግብፅ ባሮች እንደነበራችሁ አስቡ በማለት ተናግሯል፡፡ ስለዚህም በዓላቶቹ በጠቅላላ እግዚአብሔር እነርሱን ለመቤዠት ምን እንደሠራ እና እነርሱ ብቻ የእግዚአብሔር ህዝብ መሆን የቻሉት በእነርሱ ላይ በተገለጠው በእግዚአብሔር የፀጋው መልካምነት ብቻ እንደሆነ እንዲያሳስቧቸው ሲሆን በእነዚህም ሥርዓቶች ሕይወታቸው እንዲቀረፅ፣ መረዳታቸውም እንዲቀረፅ እና ከዚህም የተነሳ እግዚአብሔርን የመታዘዝ፣ የመታመን፣ የመውደድና የማገልገን ሕይወት ለእግዚአብሔር በመታመን እንዲቀጥሉበት ለማስቻል ነው፡፡ [ዶ/ር ስቲቭ ብላከሞር]*

በሙሴ ዘመን፣ በኋላም በዳዊት ዘመን፣ የእግዚአብሔርን ህዝብ ወደ እግዚአብሔር ልዩ ኅልውና ይገባ ዘንድ ለማዘጋጀት ካህናት መጠነ ሰፊ የሆኑ ሥርዓቶችን እንዲያከናውኑ ተቀርፆ ነበር፡፡ በዘሌዋውያን ምዕራፍ 1 እስከ 7 እና 23፤ ዘኁልቁ ምዕራፍ 18 እና 19፤ 1ኛ ዜና ምዕራፍ 23 እና 2ኛ ዜና ምዕራፍ 8 ያሉትን ስንመለከት እነዚህ ሥርዓቶች የተቀደሱ ጊዜዎችን፣ ክስተቶችንና ዕቃዎችን ያካትቱ ነበር፡፡

በተደጋጋሚ ጊዜም እነዚህ ሥርዓቶች ማዕከል የሚያደርጉት፣ የእግዚአብሔር ቅዱስ ኅላዌ የሚገለጥባቸውንና ህዝቡም እርሱን የሚያመልኩባቸውን የተቀደሱ ስፍራዎችን ነው፡፡ ለምሳሌ፣ የመገናኛውን ድንኳንና መቅደሱን እግዚአብሔር ሊኖርበትና ክብሩንም ይገልፅበት ዘንድ በሚመጥን ውበትና ፍፅምና ልክ የማዘጋጀቱ ሥራ የካህናት ነው፡፡ ስለዚህም ነገር ዘሌዋውያን ምዕራፍ 24 ከቁጥር 1 እስከ 9፤ ዘኁልቁ ምዕራፍ 3 እና 4 እና 1ኛ ዜና ምዕራፍ 24 ከቁር 25 እስከ 32 ውስጥ እናነባለን፡፡

ከሁሉ የሚበልጠውና በካህናት ሥርዓት ውስጥ የሚታወቀው መስዋዕት የማቅረቡ አገልግሎት ነው፡፡ መስዋዕቶች የምስጋናን መስዋዕት ከማቅረብ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እስከ ማድረግ ከዚያም እስከ ኃጢአት ስርየት ይዘልቃሉ፡፡ አንዳንዶቹ በተለያዩ የጊዜ ገደቦች ማለትም፣ በየዕለቱ ማለዳና ምሽት የሚቀርቡ መስዋዕቶች እና በየዓመቱ የሚቀርብ የስርየት መስዋዕት ናቸው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ አንድ ሁኔታ ሲከሰት ለምሳሌ ሰው ኃጢአት ሲሠራ የሚከናወኑ ናቸው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ በአምላኪው በጎ

ፈቃድ ላይ የተመሠረቱ ሲሆኑ ለምሳሌ፣ የበጎ ፈቃድ መስዋዕት ይጠቀሳል፡፡ በርካታ የሆኑት መስዋዕቶች እንደ ዘሌዋውያን ምዕራፍ 1 እስከ 7 እና ምዕራፍ 16 በመሳሰሉት ውስጥ ተዘርዝረዋል፡፡

ከሌሎቹ የካህናት ሥርዓቶች ሁሉ የሚልቀውና በኢየሱስ አገልግሎትም ቀዳሚ የነበረው መስዋእትን በተለይም የስርየት መስዋዕትን ማቅረቡ ነው፡፡ እኛም በዚያው ላይ ትኩረት እናደርጋለን፡፡

ዛሬ እኛ ስለ መስዋዕት ስንናገር አንድን እጅግ የከበረ ነገር ለማግኘት ስንል ዛሬ የከበረ ያልነውን ነገር መስጠት እንደሆነ እንናገራለን፡፡ የስጦታ መስዋዕት የሚነግረን የከበረውን ነገር ለከበረ ነገር መስጠት የሚገባ መሆኑን ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ሰዎች ለእግዚአብሔር መስዋዕት የሚያቀርቡት መስዋዕቶቹ ስለሚያስፈልጉት አይደለም፡፡ መስዋዕቶች የእግዚአብሔር ህዝብ እጅግ ዋጋ ያለውን ነገር ለማግኘት ማለትም እንደ የኃጢአት ይቅርታ የመሳሰለውን የሚያቀርቡት የከበረ ነገር ነው፡፡ መስዋዕቶች አማኞች እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ፣ ለእርሱ ያላቸውን መሰጠት እንዲገልፁ እና ስለ መግቦቱም ያላቸውን ምስጋና የሚገልጡላቸው ናቸው፡፡ እርግጥ ነው፣ መስዋዕቶች ዘወትር የእምነት መግለጫ ሊሆኑ ደግሞም በትክክለኛው መነሳሳት ሊቀርቡ ይገባቸዋል፡፡ እግዚአብሔር እንዲያውም ከልብ ያልሆኑ መስዋዕቶችን ላይቀበል ይችላል፡፡ የመስዋዕቶቹ ውጤታማነት ዘወትር መስዋዕት ለእግዚአብሔር በሚያቀርበው በአቅራቢው ቅን ልብ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

የስርየት መስዋዕቶች በዝርዝር በሙሴ አማካይነት ከተሰጡት ህግጋትም አስቀድሞም በካህናት አገልግሎት ውስጥ ወሳኝ ሚና ነበራቸው፡፡ ለምሳሌ፣ በኢዮብ ምዕራፍ 1 ውስጥ፣ ልጆቹ በአንድነት ሆነው በሚዝናኑበት ወቅት ምናልባት እግዚአብሔርን በግድየለሽነት ይበድሉ ይሆናል በማለት ስለ ልጆቹ መስዋዕት ሲያቀርብ እንመለከታለን፡፡ እንዲያውም፣ የስርየት መስዋዕቶች የሰው ልጅ በኃጢአት የመውደቁን ያህል ረጅም ዕድሜ አላቸው፡፡ አዳምና ሔዋን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲበድሉ፣ እግዚአብሔር የስርየት መስዋዕትን በራሱ በማቅረብ ህዝቡን ወደ ራሱ የመመለሱን ሥራ ሠርቷል፡፡ ይህን መሳዩ መስዋዕት በዘሌዋውያን ምዕራፍ 4 እስከ 6 እና ዘኁልቁ ምዕራፍ 15 ከቁር 25 እስከ 28 ባሉት ስፍራዎች ተገልጠዋል፡፡

*የብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች የኃጢአት ዕዳችን ሊከፈል የሚችል እንደሆነ የሚያመለክቱ የእግዚአብሔር ምህረት መገለጫዎች ናቸው፡፡ እርግጥ ነው፣ የብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች የሚከናወኑት በየክፍልፋዩ ሲሆን አሁንም በኋላም ተደጋግመው የሚከናወኑ ናቸው፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ግን አንዴና ለዘላለም*

*ተፈፀመ፡፡ ያም ለሁሉም ኃጢአት የሚበቃ እዚህ ቀረሽ የማይባል ፍፁም መስዋዕት ነው፡፡ ሆኖም ግን ብሉይ ኪዳን የኃጢአት ስርየት የሚከናወንበትን ደግሞም ይቅርታ የሚገኝ መሆኑን ያረጋገጠ  መርህ በማያወላውል ሁኔታ አስቀምጦልናል፡፡[ዶ/ር ጌራልድ ብሬይ]*

ከስርየቱ በስተጀርባ ያለው ሃሳብ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ ያም በኃጢአታችን ምክንያት፣ የሰው ዘር በጠቅላላ ሊቀጣ ይገባዋል፡፡ እንግዲያው፣ ይህንን ፍትሃዊ ቅጣት ለማስወገድ፣ አምልኮ አቅራቢዎቹ ስለ እነርሱ ሆኖ የእግዚአብሔርን ቅጣት የሚቀጣላቸው መስዋዕት ሊያቀርቡ ይገባቸዋል፡፡ የነገረ መለኮት ምሁራኑ ይህንን “ምትካዊ ስርየት” በማለት ይጠቅሱታል ምክንያቱም መስዋዕቱ አምልኮ አቅራቢውን በማስተሰረዩ ሥርዓት ወቅት ተክቶት ስለሚቀርብ ነው፡፡

በብሉይ ኪዳን በየትኛውም ምክንያት የሚከናወኑ የማስተሰረይ መስዋዕቶች በጠቅላላ ተምሳሊታዊ ነበሩ፡፡ እግዚአብሔር በሚቀርቡት መስዋዕቶች ለህዝቡ ይቅርታን ያደርጋል፣ ይህ ማለት ግን በመስዋዕቶቹ ዋጋ ላይ ወይንም በመስዋዕቶቹ በራሳቸው ብቃት ላይ ተመስርቶ ነው ማለት አይደለም፡፡ ይልቁኑ፣ የብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች ውጤታማ የሚሆኑት በአዲስ ኪዳን በኢየሱስ ክርስቶስ ብቃት ላይ ተመስርቶ ወደሚቀርበው መስዋዕት ስለሚያመለክቱ ብቻ ነው፡፡

የእግዚአብሔር ህዝብ በብሉይ ኪዳን በሚቀርቡ መስዋዕቶች በራሳቸው ለዘላለም ከኃጢአታቸው ይቅር ሊባሉ እንደማይችሉ አዲስ ኪዳን ያብራራል፡፡ የኃጢአት መስዋእቶች የእግዚአብሔርን ፍርድ ለጊዜው የማቆየት ሥራ ብቻ ሲሠሩ፣ ደግመው ደጋግመው ሊታደሱ የሚገባቸውም ነበሩ፡፡ ዘላቂ የሆነ፣ ምሉዕነት ያለው እና እግዚአብሔርም የተቀበለው ብቸኛ የኃጢአት መስዋዕት የክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞት ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሔር የብሉይ ኪዳን መስዋዕታዊ ስርዓቶችን የሰጠው የብሉይ ኪዳን አማኞች በክርስቶስ ሞት ብቃት ላይ በሚመሠረተው ስርየት የጸጋው ተካፋዮች እንዲሆኑ ስለፈቀደ ነው፡፡

የስርየት መስዋዕቶች በታመኑ አማኞች ሕይወት ውስጥ በሚገለጡበት ጊዜ፣ ቢያንስ ሁለት ወሳኝ ውጤቶችን ያስገኛሉ፡፡ የሁለቱም ፍጽምና የሚረጋገጠው ግን ወደፊት በሚከናወነው የክርስቶስ መስዋዕትነት ነው፡፡ በመጀመሪያ የምንጠቅሰው ውጤት ማንፃት/መከለል ነው፡፡

ማንፃት (መከለል) የሚያመለክተው መስዋዕቱ በአምላኪው ሕይወት ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ነው፡፡ ያም ከአምላኪው ሕይወት ውስጥ የኃጢአትን ክስ

ማስወገዱ ነው፡፡ በዚያም እግዚአብሔር በላያቸው ላይ ከሚያፈስሰው ቁጣ ይጠበቃሉ፡፡ በማንፃት/በመከለል ስርዓት፣ የአምላኪው የኃጢአት ቅጣት በምትኩ ላይ ይሆናል፣ ስለዚህም እርሱ ከጌታ ፍርድ የተጠበቀ ይሆናል፡፡

ማንፃት ኃጢአት "መከለሉ" ወይንም "መሰወሩ" በተነገረባቸው እንደ ኢዮብ ምዕራፍ 14 ቁጥር 17 እና መዝሙር 32 ቁር 1 እና 5 ባሉት ክፍሎች ተጠቅሷል፡፡ በተጨማሪም ኃጢአት ወይንም ኩነኔ "መወገዱ" በተነገረባቸውም ዘሌዋውያን ምዕራፍ 10 ቁር 17፤ መዝሙር 25 ቁር 18 እና ኢሳያስ ምዕራፍ 6 ቁጥር 7 ውስጥ የተጠቀሰ ሲሆን፣ ኃጢአት ወደ ምትኩ "እንደተሸጋገረ" በሚናገሩ፣ እንደ ኢሳያስ ምዕራፍ 53 ቁጥር 6 ውስጥም እንመለከተዋለን፡፡

ሁለተኛው የስርየት መስዋዕት ለአማኞች የሚያመጣው ውጤት እርካታ/ከቁጣ መመለስ ነው፡፡ እርካታ በመስዋዕቱ ምክንያት እግዚአብሔር የሚረካውን የጽድቅ እርካታ ያመለክታል፡፡ እርካታ እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ያለው ፍትህና ቁጣ መርካቱን የሚያመለክት ነው፡፡ እርካታ እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ያለው ቁጣ የሚያርፍበት ስፍራ ማግኘቱንና መርካቱን የሚያሳይ ነው፡፡ በዚያም ምክንያት፣ እግዚአብሔር ፍትሁን ቸል ከማለት ይልቅ ለአምላኪው ርኅራኄንና ፍቅርን እንዲገልጥ ያስችለዋል ማለት ነው፡፡

እርካታ የእግዚአብሔር ቁጣ መብረዱን ወይንም መርካቱን በሚያመለክቱ እንደ ዘኍልቁ ምዕራፍ 25 ከቁጥር 11 እስከ 13 እና ዘዳግም ምዕራፍ 13 ቁጥር 16 እና 17 ባሉት ክፍሎች ውስጥ ተመልክቷል፡፡

> *የብሉይ ኪዳን የመስዋዕት ስርዓቶች ስለ እግዚአብሔር በርካታ እውነቶችን የሚያንፀባርቁ ሲሆኑ፣ ከሁሉ ይልቅ ግን ምህረቱን ይገልጣሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የምናስበው የእግዚአብሔርን ሐዘን ለማጥፋት ስለ ሰዎች ከሚሰዉት እንስሶች አቅርቦት አንፃር ብቻ ነው፡፡ ሆኖም ግን እነዚህ መስዋዕቶች የሚነሳሱት በእግዚአብሔር ፍቅርና ምህረት መሆኑንም ልብ ልንል ይገባል፡፡ ስለ ምህረት ስናስብ ስለ እኛ ያለውን ርኅራኄ የሚያመለክት ሲሆን ያም የማይገባንን እንድናገኝ ካስቻለን ከፀጋው ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ዘሌዋውያን ምዕራፍ 17 ቁጥር 11 በጣም በጣም አስፈላጊ ቁም ነገር ይዟል፡፡ ያም የእስራኤል መንግሥት በምታከናውነው የመስዋዕቶች ስርዓት አማካይነት እግዚአብሔርን የእርሷ ወገን እንዳደረገችው ሊቆጠር እንደማይገባ የሚያመለክተው ነው፡፡ እግዚአብሔር በራሱ ፍቅር ተነሳስቶ በዘረጋው መስመር አማካይነት በእነርሱ መካከል ሊያድር ወደደ እንጂ ከእነርሱ የተነሳ አይደለም፡፡ ስለዚህም በእርሱ*

*ኀልውና ዘሪያ ያድራሉ፡፡ ህዝቡም ይሆናሉ፤ እርሱም አምላካቸው ይሆናል፡፡ ሁሉም ነገር የእርሱ ምህረት፣ የእርሱ ፍቅር እና የእርሱ ጸጋ መገለጫ ነው፡፡ ሁሉም ነገር በስተመጨረሻው ሙላቱ ወደ ሆነው በክርስቶስ ወደ ሚገልጠው ስጦታው የሚያመለክት ነው፡፡ በእርሱም በኩል እነዚህ መስዋዕቶች በጥላነት ሲያመለክቱ የነበረው ሁሉ እውን ሆኗል ስለዚህም እኛ አሁን እግዚአብሔርን በአዲሱ ኪዳን መሠረት እናውቀዋለን፡፡ እኛ አሁን በታላቁ መስዋዕታችን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ወደ እርሱ በቀጥታ መግባትን አግኝተናል፡፡ [ዶ/ር ስቴፈን ዌሉም]*

*የብሉይ ኪዳኑ የመስዋዕቶች ስርዓት ስለ እግዚአብሔር ያም ምህረቱን በበርካታ መንገዶች ይገልጣሉ፡፡ ከሁሉ የሚያስደንቀው ግን የማስተሰረይ ቀን ነው፡፡ በዚያም የመገናኛው ድንኳን ወይንም መቅደሱ አለ፣ ከዚያም ቅድስተ ቅዱሳኑ አለ፣ ዐሥርቱን ትዕዛዛት ያሉበት የቃል ኪዳኑ ታቦት አለ፣ በዚያም ሳጥን አናት ላይ የምህረቱ መቀመጫ አለ፡፡ በማስተሰረይም ቀን፣ ሊቀ ካህኑ የመስዋዕቱን በግ ከመቅደሱ ወይም ከመገናኛው ድንኳን ውጪ ባለው መሰዊያ ላይ ያርደውና ደሙን ይዞ በመጋረጃው አልፎ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በመግባት በሳጥኑ አናት ላይ ይረጨዋል፡፡ ሃሳቡም ሰዎች የተላለፉትን ህግ ደሙ ሲሸፍነው እግዚአብሔር በምህረት ይገለጣል የሚል ነው፡፡ በእርግጥም፣ የእኛን የህግ መተላለፍ የሸፈነውንና እውነተኛውን የእግዚአብሔር በግ የኢየሱስ ክርስቶስን ደም የሚያመለክት ነው፡፡ ግን፣ ልብ ማለት የሚገባን የእግዚአብሔር ምህረት የተገኘው መተላለፋችንን በሸፈነው በደሙ ውስጥ መሆኑን ነው፡፡ [ዶ/ር ፍራንክ ባርከር]*

ይህንን የካህናትን አመራርና ስርዓቶች በልቡናችን ይዘን፣ የሚወክሏቸው ሰዎች ምትክ በመሆን ወደሚፈፅሙት የምልጃ አገልግሎት እንሸጋገራለን፡፡

## ምልጃ

ምልጃን መካከለኛ መሆን፤ ወይንም በአንድ ሰው ምትክ በጎ እንዲደረግለት መለመን ብለን ልንፈታው እንችላለን፡፡ ማላጅ በችግር ውስጥ በምትሆኑ ወቅት ከእናንተ ወገን ሆኖ ስለ ጉዳያችሁ የሚማፀን ወይንም በእናንተና በሌላኛው ወገን ያሉ ክርክሮችን ለማስታረቅ የሚሞክር ሰው ነው፡፡

የብሉይ ኪዳን ካህናት በሚሰጧቸው አመራሮች ወይንም እግዚአብሔር እንዲፈፅሟቸው በሰጣቸው ሥርዓቶች አማካይነት በተደጋጋሚ ጊዜ ይማልዳሉ፡፡

ለምሳሌ፣ በሰዎች መካከል የሚነሱ ህጋዊ ክርክሮችን በሚዳኙበት ጊዜ እና በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከልም ሆነው የማስተሰርያ መስዋዕት በሚያቀርቡበት ወቅት ይማልዳሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር ካህናት የተለያዩ ምልጃዎችን ያከናውናሉ፡፡

አንደኛው የምልጃ አይነት ለእርዳታ መማፀን ነው፡፡ ካህናት እግዚአብሔር ህዝቡን እንዲፈውስ፣ እንዲታደግና ወይም በሆነ መንገድ ህዝቡን እንዲደግፍ ይጸልያሉ፡፡ የዚህንም ምሳሌ በ1ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 1 ቁጥር 17 እና 1ኛ ዜና ምዕራፍ 16 ቁጥር 4 ላይ እናገኛለን፡፡

> አንዱን ለምሳሌ ብንወስድ፣ በኢዮብ ምዕራፍ 1 ቁጥር 5 ላይ ኢዮብ ለልጆቹ ያቀረበውን ምልጃ እናድምጥ፡
>
> የግብዣውም ቀኖች ባለፉ ጊዜ ኢዮብ። ምናልባት ልጆቼ በድለው፥ እግዚአብሔርንም በልባቸው ሰድበው ይሆናል ብሎ ይልክና ይቀድሳቸው ነበር ኢዮብም ማልዶ ተነሣ፥ እንደ ቍጥራቸውም ሁሉ የሚቃጠል መሥዋዕት አቀረበ። እንዲሁ ኢዮብ ሁልጊዜ ያደርግ ነበር። (ኢዮብ 1፥5)

በቤቱ ላይ እንደ ተሾመ ካህን፣ ኢዮብ ልጆቹን በኃጢአታቸው ምክንያት ከሚመጣባቸው ጣጣ ለመሸፈን ይማልድላቸዋል፡፡

ሌላኛው የተለመደ የምልጃ አይነት የበረከትን ቃል ማወጅ ነው፡፡ ካህናት ህዝቡን ሲባርኩ፣ ለህዝቡ ሞገስን እንዲሰጥ እግዚአብሔርን ይለምናሉ፡፡ ይህንንም መልከጼዴቅ አብርሃምን በባረከበት መንገድ በዘፍጥረት ምዕራፍ 14 ቁጥር 19 እና 20 ውስጥ የምናየው ሲሆን፣ ደግሞም በዘኍልቁ ምዕራፍ 6 ከቁጥር 22 እስከ 27 ካህናት ህዝቡን በሚባርኩበት በረከት ውስጥ እናገኘዋለን፡፡

> ለአብነት ያህል፣ በ2ኛ ዜና ምዕራፍ 30 ቁጥር 27 የተመዘገበውን አድምጡ፡
>
> *ካህናቱና ሌዋውያኑም ተነሥተው ሕዝቡን ባረኩ ድምፃቸውም ተሰማ፥ ጸሎታቸውም ወደ ቅዱስ መኖሪያው ወደ ሰማይ ዐረገ። (2ኛ ዜና 30፥27)*

ምንባቡ እግዚአብሔር ሰማቸው ካለ፣ ካህናቱ ለባረኩት ህዝብ ሞገስን በመስጠት የካህናትን ምልጃ አከበረው ማለት ነው፡፡ የዚህ የክህነት አገልግሎት ነፀብራቅ በእኛም ዘመን ካህናት በጋራ አምልኮዎቻችን ማብቂያ ላይ በሚሰጡት ቡራኬም ውስጥ ይስተጋባል፡፡ በርካታ አብያተ ክርስቲያናትም በዘኍልቁ ምእራፍ 6 ለአሮን የተሰጠውን የበረከት ቃል ይደግሙታል፡፡

እንደተመለከትነው የካህናት አገልግሎት የተለያየ ነው፡፡ አመራር ይሰጣሉ፣ ስርዓቶችን ያስፈፅማሉ ደግሞም ይማልዳሉ፡፡ እነዚህ እንቅስቃሴዎች የተለያዩ ቢሆኑም በአንድ ዓላማ በዘላቂነት የተሳሰሩ ናቸው፡፡ ሁሉም የተቀረፁት የእግዚአብሔር ህዝብ በእግዚአብሔር ኅላዌ ውስጥ ለመኖር በሚያስችለው የሕይወት ጥራት ልክ እንዲኖር እና የቃል ኪዳኑንም በረከት እንዲቀበል ለማድረግ ነው፡፡

የክህነትን አገልግሎት መመዘኛዎች እና ተግባራት ከተመለከትን፣ ቀጥለን ደግሞ ወደፊት ከሚመጣው የክህነት አገልግሎት ብሉይ ኪዳን የሚጠብቀውን እንመለከታለን፡፡

## ጥበቃ

በብሉይ ኪዳን ዘመን፣ የክህነት አገልግሎት የተለዋዋጭነት ባህርይ ነበረው፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ውስን ተግባራቱ ይለዋወጡ ነበር፡፡ የመልከፄዴቁ ክህነት ከኢዮቡ ጋር አንድ ዓይነት አልነበረም፡፡ የኢዮብ ደግሞ ከዮቶሩ ይለያል፡፡ የዮቶር ደግሞ ከአሮንና ከልጆቹ የተለየ ነበር፡፡ ከዚህም ባሻገር ብሉ ኪዳን ወደፊት በሚመጣውም ክህነት ውስጥ ብዙ ለውጦች እንደሚኖሩ ያመለክታል፡፡

ብሉይ ኪዳን ወደፊት ከሚመጣው የክህነት አገልግሎት የሚጠብቀውን ለመረዳት፣ በሁለት አቅጣጫዎች እንመለከተዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የአገልግሎቱን እድገት በብሉይ ኪዳን የታሪክ ሂደት ውስጥ እናየዋለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ ወደፊት ስለሚመጣው የክህነት አገልግሎት በተነገሩ ጥቂት ውሱን ትንቢቶች ላይ ትኩረት እናደርጋለን፡፡ አስቀድመን በክህነት አገልግሎት ታሪካዊ እድገት እንጀምር፡፡

## ታሪካዊ እድገት

የሰው ዘር ዘወትር በእግዚአብሔር ልዩ የተቀደሰ ኅልውና ውስጥ እንዲገኝ የሚያስችለውን ብቃት ማግኘት የሚያስፈልገው በመሆኑ ምክንያት፣ የክህነት አገልግሎት ዘወትር አስፈላጊ ይሆናል ማለት ነው፡፡ በእርግጥም ካህናት፣ እግዚአብሔር ለሰው ዘርና ለፍጥረቱ ባለው የረጅም ጊዜ እቅድ ውስጥ ቁልፍ ሚና አላቸው፡፡ ታሪክን ስንመለከት ግን፣ በሚለዋወጠው የእግዚአብሔር ህዝብ ሁኔታ ምክንያት የካህናትም ሃላፊነት ሲለዋወጥ እንመለከተዋለን፡፡

ስለዚህም የካህናትን ተለዋዋጭ ሃላፊነት በአራት የታሪክ እርከኖች ከፋፍለን እንመለከተዋለን፣ አስቀድመንም በፍጥረት ዘመን እንጀምራለን፡፡ ይህም ጊዜ እግዚአብሔር ከአዳም ጋር ከገባው ኪዳን ጋር ይገጥማል፡፡

## ፍጥረት

የሰው ዘር ተቀምጦበት የነበረው የዔድን ገነት፣ እግዚአብሔር በህዝቡ መካከል ይመላለስና ይነጋገርበት የነበረ መቅደሱ ነበር፡፡ በዚህ አውድ መሠረት፣ አዳምና ሔዋንም በመገናኛው ድንኳን ወይንም በመቅደሱ ውስጥ አሮናዊው የክህነት አገልግሎት ይፈፀምበት በነበረው ዐይነት እግዚአብሔርን ያገለግሉ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት፣ የክህነት አገልግሎት የሰውን ዘር ያህል ረጅም ዕድሜ አለው ማለት ነው፡፡

እስኪ ሙሴ በዘፍጥረት ምዕራፍ 2 ቁጥር 15 ላይ የጻፈውን አድምጡ፡

*እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔድን ገነት አኖረው። (ዘፍ 2፥15)*

በዚህ ምንባብ፣ ሙሴ አዳምና ሔዋን በገነት ውስጥ ያከናውኑ የነበረውን ተግባር የገለጠው በዕብራይስጡ “አቫድ” ፍቺውም *ሥራ* ማለት የሆነ፣ ደግሞም “ሻማር” ፍቺውም መንከባከብ በሆኑ ቃላት ነበር፡፡ በዘኍልቁ ምዕራፍ 3 ቁጥር 7 እና 8 ውስጥም ሙሴ ሌዋውያን በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የሚያከናውኑትን ተግባር ሲገልጥ እነዚህኑ ተመሳሳይ ቃላት አጣምሮ ተጠቅሞባቸዋል፡፡ በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ቁጥር 8 እና 2ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 7 ቁጥር 6 ውስጥም ተዛማጅ ቃሎችን እናገኛለን፡፡

በኤድን ገነት ውስጥ የሰውን ዘር *ሥራ*ና በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የካህናትን *ሥራ*፣ በተመሳሳይ ቋንቋ ሲገልጣቸው አዳምና ሔዋን የመጀመሪያዎቹ ካህናት እንደነበሩ፣ የመገናኛው ድንኳን ወይንም መቅደሱ ደግሞ በኤድን ገነት የነበረውን ተግባር የማሟላት ዓላማ እንደነበራቸው ሙሴ እያመለከተ ነበር ማለት ነው፡፡ በእርግጥም፣ በርካታ የነገረ መለኮት ምሁራን እንደሚናገሩት የመገናኛው ድንኳንና የመቅደሱ ውበትና ጌጣ ጌጦች በኤድን ገነት ውስጥ የነበረውን ውበት ለትውስታ የሚያመለክት ነበር፡፡

በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ፣ በኤድን ገነት የነበረው የሰው ዘር የክህነት አገልግሎት በገነት ውስጥ በነበረው ማደሪያው ውስጥ እግዚአብሔርን የማገልገል፣ ለእርሱ የተቀደሱ ነገሮች እንክብካቤ የማድረግ፣ ስፍራውም ለእርሱ ማደሪያነት እንዲመጥን የማድረግ ተግባራትን ያካተተ ነበር፡፡ ከዚህም በላይ፣ አዳምና ሔዋን ከነዘርያዎቻቸው ለእግዚአብሔር የካህናት መንግሥት እንዲሆኑ፣ ተግባራቸውንም በተቀረው ዓለም እንዲያስፋፉ እግዚአብሔር አዝዟቸው ነበር፡፡

እግዚአብሔር በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 28 ለሰው ዘር የተናገረውን አድምጡ፡

> *እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፡- ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው። (ዘፍ 1፥28)*

ምድርን የመሙላትና የመግዛት የእግዚአብሔር ትዕዛዝ በተደጋጋሚ ጊዜ "ባህላዊ ሥልጣን" ተብሎ ይጠራል፣ ምክንያቱም የሰው ዘር መላው ዓለም ኤድን ገነትን እስከትመስል ድረስ የማልማትና የማሳደግ ግዴታ እንዳለበት ያመለክታልና ነው፡፡ የሰው ልጅ ተግባር ከክህነት አገልግሎት አንፃር ሲታይ፣ መላውን ዓለም ወደ እርሱ መቅደስነት መለወጥና እርሱንም ለዘላለም ማገልገል ነው፡፡

> *እግዚአብሔር የሰውን ዘር በአምሳሉ ሲፈጥር፣ "የፍጥረት ባህላዊ ሥልጣን" ተብሎ የሚጠቀሰውን ሥልጣንም አብሮ ሰጥቶናል፡፡ ስለዚህ ጉዳዩን ከዚያ አንፃር መመልከቱ አግባብነት አለው፣ ማለትም ሃላፊነታችን በንግሥና ሥልጣን ምድርን ከመግዛት ጋር ብቻ ሳይሆን ከክህነትም ጋር የተያያዘ መሆኑን መረዳት አለብን፡፡ መፈጠራችንም ሌላ ምንም ምክንያት የለውም፡፡ ምንም እንኳን ኃጢአት ወደ ዓለም ገና ባይገባም፣ በዘፍጥረት ምዕራፍ 2 ውስጥ እንደተመዘገበው በኤድን ውስጥ የመቅደስና የአትክልት ስፍራ የእግዚአብሔር መገኛ ዓይነት ምስል እንመለከታለን፡፡ እንግዲያው፣ በፍጥረት ወቅት የነበረን ሃላፊነት የኤድንን ድንበር እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ማስፋፋት ነበር፡፡ በስተመጨረሻው፣ በአዲሲቷ ሰማይና ምድር በክርስቶስ ውስጥ ይከናወናል፡፡ እንግዲህ በዚህ የክህነት አገልግሎት ማዕከል ውስጥ አምልኮም ይገኛል፡፡ ስለዚህም በዚህ የፍጥረት ባህላዊ ሥልጣናችን የምናደርገውን ሁሉ የምናደርገው ለእግዚአብሔር ክብር ነው፡፡ አገልግሎትና እነዚህ ሁለት ሃሳቦች ከክህነት ሥራና ከንግሥና ሥራ ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡ እንግዲያው፣ የፍጥረት ባህላዊ ሥልጣናችን ባለአደራነትን፣ ከእርሱ ጋር ባለ ጥብቅ ቁርኝት የእግዚአብሔር*

*ፍጥረት መሆንን፣ የገነትን ድንበር ማስፋፋትን፣ ማምለክን፣ ከእርሱ ጋር በጥምና መገናኘትን፣ መታዘዝን፣ በፍጥረቱ ውስጥ ያለውን ግብዓት ሙጥጥ አድርጎ ማውጣትን የሚያካትት ሲሆን፣ ምልዓቱም በአዲሲቷ ሰማይና ምድር ይገለጣል፡፡ [ዶ/ር ስቴፈን ዌሉም]*

*በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ ስለ ባህላዊ ሥልጣን የምንረዳው ነገር አለ፡፡ የተሰጠንን ሕይወት ስንኖረው፣ እግዚአብሔር ልንሆንለት የሚፈልገውን ዓይነት ሰው ሆነን በእርሱ መታየት የተግባራችን ወሳኝ ክፍል ነው፡፡ ስለዚህም ይህ ባህላዊ ሥልጣናችን በምንም ምክንያት የወንጌል ተልዕኮ ሥልጣናችንን ቸል እንድንል ሊያደርገን አይችልም፡፡ ሁለቱም ከእግዚአብሔር ናቸው፣ ሁለቱም አግባብነት አላቸው፣ ሁለቱም አስፈላጊ ናቸው፡፡ በመሠረቱ፣ ባህላዊ ሥልጣን ትልቅ ስጦታና ዕድል ነው፡፡ የመግቦት አምላክ በአምሳሉ የፈጠረውን ህዝቡን፣ የውክልና ሃላፊነት ሊሰጠው፣  እንዲንከባከብ፣ ባለአደራ እንዲሆን፣ በፍጥረት ስርዓት ውስጥ ያለውን እምቅ ሀብት እንዲያጎለብት፣ እና እንደ እግዚአብሔር ታማኝ አምባሳደር ወይንም የመጋቢው የእግዚአብሔር ወኪል እንዲሆን የጋበዘበትን ግብዣ ያመለክታል፡፡ እንግዲያው፣ በፈጣሪያቸው አምሳል እንደተፈጠሩ ፍጡራን፣ ቻሮች፣ደጎች ልንሆን የፍጥረት ሥልጣናችንንም ከግብ ለማድረስ በሃላፊነት ስሜት ሰዎችን ልንመግብ ይገባናል፡፡ [ዶ/ር ግሌን ስኮርጂ]*

## ውድቀት

ከክህነት አገልግሎት አንፃር የመጀመሪያው ለውጥ የታየው፣ በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 የሰው ዘር መልካምና ክፉውን ከምታስታውቀው ዛፍ እንዳይበላ የታዘዘውን ፍሬ በመተላለፍ በበላ ወቅት ነበር፡፡

በዚህ ወቅት፣ አዳምና ሔዋን ከኤድን ገነት ተባረሩ ለበደላቸው ስርየት የሚሆን መስዋዕትም ማቅረብ ተጀመረ፡፡ የዚህንም ተግባር መግለጫ ገና በጠዋቱ በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ቁጥር 21 ውስጥ፣ እግዚአብሔር የአዳምንና የሔዋንን እርቃን በእንስሳት ቆዳ በሸፈነበት ስፍራ ውስጥ ይገኛል፡፡ የዚህንም ልምምድ ልዩ መግለጫ በዘፍጥረት ምዕራፍ 4 ቁጥር 4፣ አቤል ባቀረበው የእንስሳት መስዋዕት ውስጥ እንመለከተዋለን፡፡ ሌሎችም ተመሳሳይ መገለጫዎች በየወቅቱ እናገኛለን፡፡ ለምሳሌ፣ በዘፍጥረት ምዕራፍ 8 ቁጥር 20 ከጥፋት ውሃ በኋላ ኖህ ባቀረበው መስዋዕት፤ በዘፍጥረት ምዕራፍ 22 ቁጥር 13 አብርሃም በሰዋው ጠቦት፤ በዘፍጥረት ምዕራፍ 31 ቁጥር 54 ደግሞ ያዕቆብ ባቀረበው መስዋዕት ውስጥ እናገኛለን፡፡ በዚህ ወቅት፣ የቤተሰቡ

አባወራዎች የዝርያዎቻቸው ካህናት በመሆን ያገለግሉ የነበረ ሲሆን፣ ከዚያ በሰፋ ሁኔታ እንዲያገለግሉ የሚጠሩት በጣም ጥቂት ብቻ ነበሩ፡፡

በዚህ ወቅት የምናየው ለውጥ የክህነት አገልግሎት ማከናወኛ ስፍራ ነው፡፡ ከውድቀት በፊት፣ አገልግሎቱ ይሰጥ የነበረው በኤድን ገነት ውስጥ በነበረው የእግዚአብሔር የአትክልት ስፍራ ውስጥ ነው፡፡ በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 የሰው ዘር ከኤድን ገነት ከተባረረ በኋላ ግን፣ ህዝቡ እርሱን የሚያመልክበትን ስፍራ ለይተው እንዲሠሩና እግዚአብሔርም ከእነርሱ ጋር የተገናኘባቸው ስፍራዎች መታሰቢያ የሚሆኑ ደንጋዮችን እንዲተክሉ ካህናትን አዘዛቸው፡፡ በፍጥረት ጅማሬ ከነበረው በተቃራኒ በዚህ የታሪክ ዘመን ውስጥ በምድር ላይ የእግዚአብሔር ማደሪያ እንዲሆን የተለየ ስፍራ አልነበረም፡፡

## ዘፀአት

ቀጣዩ ዐቢይ ለውጥ የተከናወነው እስራኤል ከግብፅ ባርነት በወጣበት ዘመን የተከሰተው ነው፡፡ የእስራኤል መንግሥት በግብጽ ፈርዖን ከ400 ዓመታት ለበለጠ ጊዜ በባርነት ከቆዩ በኋላ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፣ እርሱም በታላላቅ ተዓምራቶቹ ነፃ አወጣቸው፡፡ ይህም ሁነት በመጽሐፍ ቅዱስ ሁለተኛ መጽሐፍ በዘፀአት ውስጥ ተገልጧል፡፡

በዚህ ወቅት፣ እግዚአብሔር ለሰው ዘር ሁሉ የነበረውን የክህነት ጥሪ ወደ እስራኤል አጠበበው፡፡ በዘፀአት ምዕራፍ 19 ቁጥር 6 ውስጥ እንደተናገረው፣ እስራኤል የካህናት መንግሥት ተብላ ተጠርታለች፡፡ በተጨማሪም የሌዊ ነገድ የእርሱ ልዩ አገልጋይ እንዲሆን ለየው፡፡ አብዛኛው ነገድ በአገሪቱ በጠቅላላ የክህነት አገልግሎት የሚሰጡትን ቁጥራቸው ጥቂት የሆኑ ሌዋውያንን በሚደግፉ ተግባራት ውስጥ ይሳተፍ ነበር፡፡ ከሌዋውያን መካከልም፣ አሮንና ልጆቹ ብቻ ለክህነት አገልግሎት ተለዩ፣ ሊቀ ካህን የሚሆንም አንድ ሰው ለአንድ ወቅት ይሾማል፡፡ ለአሮናዊው ክህነት ከእግዚአብሔር የተሰጡ አዳዲስ ሃላፊነቶችንና መመሪያዎችን በዘሌዋውያን መጽሐፍ በጠቅላላ እና በዘኍልቁ መጽሐፍ የተወሰኑ ክፍሎች ውስጥ እናገኛለን፡፡

እግዚአብሔር በተጨማሪም በዚህ ወቅት የመገናኛውን ድንኳን መጀመርና አሰራር ይፋ አድርጓል፡፡ የመገናኛው ድንኳን ትልቅ፣ እጅግ የተዋበና እስራኤላውያን በሚጓዙበት ወቅት ይዘውት የሚጓዙት አይነት ድንኳን ነበር፡፡ አገልግሎቱም፣ ቀደም ብሎ በኤድን ገነት እንደነበረው ሁሉ ተመሳሳይ ነበር፤ ያም ማለት እግዚአብሔር የሚመላለስበትና ከህዝቡ ጋር የሚነጋገርበት ስፍራ በመሆን የሚያገለግል መቅደስ

ነበር፡፡ ከውድቀት በኋላ፣ በተለያዩ ስፍራዎች በተለያዩ ጊዜያት እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ይገናኝ ነበር፡፡ የመገናኛው ድንኳን ከተመሠረተ በኋላ ግን፣ እርሱ የሚመለከበት ስፍራ አንድ እንዲሆን እግዚአብሔር እንደገና ወሰነ፡፡ በዚህ ስፍራ የሚከናወነው አምልኮ የሚመራው በእግዚአብሔር በተመረጡ አገልጋዮች፣ በካህናት ነበር፡፡ የመገናኛው ድንኳን መመሥረትና አጠቃላይ አመራሩ፣ በዘፀአት ምዕራፍ 25 እስከ 40 ውስጥ ይገኛል፡፡

በዘፀአት እንዲከናወን ያደረገው የክህነት አገልግሎት ለውጥ ለሰው ዘር እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን ዕቅድ ወደ ፍፃሜ እንዲያመጣ አልሞ ነው፡፡ ዕቅዱም ከአሮን ቤተሰብ የሆኑት ካህናት አስቀድመው እስራኤልን ወደ እርሱ መንግሥትነት እንዲለውጡ፣ በመቀጠልም በዚህች ልዩ መንግሥት ታማኝነት እና አገልግሎት አማካይነት መንግሥቱ መላውን ዓለም እንድትሸፍን ማድረግ ነው፡፡

## የነገሥታት ዘመን

በብሉይ ኪዳን በክህነት አገልግሎት ውስጥ የታየው የመጨረሻ ለውጥ የተከሰተው ህዝበ እስራኤል በተስፋዪቱ ምድር ውስጥ በተቀመጠበትና በንጉሣዊ አገዛዝ ውስጥ ይተዳደር በነበረበት በእስራኤል የነገሥታት ዘመን ውስጥ ነበር፡፡ የነገሥታቱ ዘመን የተጀመረው በእስራኤሉ ንጉሥ በሳዖል፣ የተሳሳተ ንግሥና ነው፡፡ በትክክለኛ መንገድ የጀመረው ግን በሳዖል ተከታይ በዳዊትና በዘሩ ነው፡፡

የእስራኤል ነገሥታት ሲነግሡ፣ በክህነት አገልግሎት ውስጥ በቅርበት ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ዳዊት መቅደሱን ለመሥራት አቅዶ ነበር፡፡ የክህነት አገልግሎትም በአግባቡ መሰጠቱን ያረጋግጥ ነበር፡፡ የተወሰኑ የካህናት ቤተሰቦችንም በማደራጀት የተወሰነ ሃላፊነትም ይሰጣቸው ነበር፡፡ እነዚህን እድገቶች እንደ 1ኛ ዜና ምዕራፍ 15፣ 16 እና ከ23 እስከ 28 በመሳሰሉት ምንባቦች ውስጥ እናገኛቸዋለን፡፡ ዳዊት በተጨማሪም ሌሎቹ የሌዊ ቤተሰቦች በረኞችና ሙዚቀኞች እንዲሆኑ ሃላፊነት ሰጥቶ ነበር፡፡ በ2ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 6 ቁጥር 17 እና 18 ውስጥ እንደምንመለከተው፣ ከካህናት ጋር በመሆን መስዋዕት ያቀርብ ህዝቡንም ይባርክ ነበር፡፡ በአንድ ወቅትም፣ በ1ኛ ዜና ምዕራፍ 15 ቁጥር 27 እንደተመዘገበው የንግሥና ካባውን በካህናት ኤፉድ ለውጦ ነበር፡፡ በዕዝራ ምዕራፍ 8 ቁጥር 20 ውስጥ እንደምንመለከተውም ከዳዊትም ዘመን በኋላም እነዚህ ዕድገቶች ተመዝግበው እናገኛቸዋለን፡፡

በዳዊት ዘመን፣ እንደ ሊቀ ካህን ለማገልገል የሚፈቀድላቸው ቤተሰቦች ሁለት ብቻ እንዲሆኑ ተደርጎ ነበር፡፡ እነርሱም የአሮን ዘር የሆኑት ሳዶቅና አብያታር ናቸው፡፡ ይህ መረጃ በ1ኛ ዜና ምዕራፍ 18 ቁር 16 ላይ ተመዝግቧል፡፡

ከዳዊትም በኋላ፣ ልጁ ሰሎሞን በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ ነገሠ፣ ከዳዊትም በላቀ ሁኔታ በክህነት አገልግሎት ውስጥ ተሳታፊ ነበር፡፡ ሰሎሞን የመቅደሱን ሥራ በበላይነት ይቆጣጠር ነበር፡፡ መጠነ ሰፊ መስዋእቶችንም ይቆጣጠር ነበር፡፡ አባቱ ያደርግ እንደነበረው ሁሉ፣ በመቅደሱ ውስጥ ህዝቡን በጸሎት ይመራና ይባርክ ነበር፡፡ እነዚህም ዝርዝሮች በ1ኛ ዜና ምዕራፍ 21 ቁጥር 28፤ በ2ኛ ዜና ምዕራፍ 3 እስከ 6 እና በ1ኛ ነገሥት ምዕራፍ 8 እና 9 ውስጥ ተጠቅሰዋል፡፡ ዳዊት በጻፋቸው በአብዛኞቹ መዝሙሮቹም ውስጥ የተጠቀሱ ሲሆን መዝሙር 5፣ 11፣ 18፣ 27፣ 65፣ 66 እና 68 ይገኙባቸዋል፡፡

ሰሎሞንም የሊቀካህንነቱን መስመር ወደ አንድ አጠበበው፡፡ አብያታር ክህደትን በመፈፀሙ ምክንያት፣ በ1ኛ ነገሥት ምዕራፍ 2 ቁጥር 26፣ 27 እና 35 ውስጥ እንደምናየው ሰሎሞን አብያታርንና ቤተሰቡን ከክህነት አገልግሎት እንዲወገዱ አደረጋቸው፡፡ ይህም በ1ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 2 ከቁጥር 27 እስከ 36 እንደተመዘገበው በመሳፍንት ዘመን ካህን ሆኖ ያገለግል በነበረውና ከታማኝነት በጎደለው በኤሊ ቤት ላይ የተላለፈው ፍርድ እንዲፈፀም አደረገ፡፡

በመቅደስ ውስጥ የሚከናወኑ ውሱን አገልግሎቶች ለካህናት ብቻ የተለዩ ሆነው ሳሉ፣ የይሁዳ ነገሥታት ግን የዳዊትንና የሰሎሞንን ተምሳሊት በመከተል ክህነት አገልግሎት ላይ ይሳተፉ ነበር፡፡ በሰሎሞን መቅደስ ውስጥ፣ ንጉሣዊ ካህናት ነበሩ፡፡

የነገሥታቱ ዘመን ያከተመው በ587 ወይንም 586 ዓ.ዓ. ባቢሎናውያን ኢየሩሳሌምንና የሰሎሞንን ቤተመቅደስ ሲያፈርሱና ህዝቡንም ማርከው ሲወስዱት ነው፡፡ ሆኖም ከምርኮው ዘመን በኋላ በ515 ዓ.ዓ. አካባቢ በተደረገው የተሃድሶ እንቅስቃሴ፣ ከምርኮ በተመለሱ እስራኤላውያን መቅደሱ ተገነባ፡፡ በዚያም ወቅት፣ ነቢያቱ ሕዝቅኤልና ዘካርያስ የሳዶቅ ዘር የሆነው ኢያሱ፣ ሊቀ ካህን ሆኖ እንዲያገለግል በእግዚአብሔር የተሾመ መሆኑን ተናገሩ፡፡ በተጨማሪም ከዳዊት ዘር የሆነው ዘሩባቤል የኀዳሴውን እንቅስቃሴ እንደሚመራና ኢያሱም ከእርሱ ጋር አብሮ እንደሚሠራ አወጁ፡፡ በሚያሳዝን ሁኔታ ግን፣ የዘሩባቤልና የኢያሱ ጥረት ብዙ ርቀት ሊሄድ አልቻለም፡፡ በዚያው ዘመን፣ አብዛኞቹ ካህናትና ሌዋውያን ከእግዚአብሔር ራቁ፣ የምድሪቱም አብዛኛ ህዝብ ይህንኑ ፈለግ ተከተለ፡፡ የእስራኤል አምልኮ ረከሰ፣ በምድሪቱም ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ በመቶዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት ዘለቀ፡፡

ይህም ሆኖ፣ በዚህም ወቅት የእስራኤል ህዝብ የዳዊትንና የሰሎሞንን ዘመን መለስ ብሎ ማሰቡን ቀጥሎ ነበር፡፡ ከመካከላቸውም የታመኑ የነበሩት ነገሥታትና ካህናት እንደሚገባቸው እግዚአብሔርን ያገለግሉ በነበረበት ዘመን ሁኔታው ምን ይመስል እንደነበረ ያስታውሱ ነበር፡፡ ከዚህ ቀደም ሆኖ በማያውቅ ሁኔታ የንግሥናና የክህነት አገልግሎት ጉልህ በሆነ መንገድ የሚሰጥበትንና እግዚአብሔርም በንስሓ ወደ እርሱ የሚመለሱትን ህዝብ የጎልውናውን በረከት ይካፈሉ ዘንድ የሚቀበልበትን አዲስ ቀን ተስፋ ያደርጉ ነበር፡፡

በክህነት አገልግሎት ታሪካዊ እድገት የተፈጠሩትን ጥበቃዎች መርምረናል፣ አሁን ደግሞ የተወሰኑ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ከወደፊቱ ካህናት የሚጠብቁትን እንመለከታለን፡፡

## ውሱን ትንቢቶች

በዚህ ክፍል፣ ስለ ክህነት አገልግሎት በሚናገሩ ሦስት ውሱን ትንቢቶች ላይ እናተኩራለን፡፡ የመጀመሪያው ጥበቃ በስተመጨረሻ ለአገልግሎቱ ፍጻሜ የሌለው ሊቀ ካህን የሚነሳ መሆኑ ነው፡፡

አንድ ቀን የክህነት አገልግሎት ዘላለማዊ ወደ ሆነው ብቸኛ ሊቀ ካህን እጅ እንደሚገባ ብሉይ ኪዳን በብዙ መንገዶች ያመለክታል፡፡ በሙሴ ዘመን የሊቀ ካህንነትን አገልግሎት እንዲሰጥ እግዚአብሔር አሮንን ሾሞት ነበር፣ ሆኖም ግን ከእርሱ ክህነት የሚልቅ ክህነት አንድ ቀን እንደሚመጣ ብሉይ ኪዳን በተስፋ ይጠባበቅ ነበር፡፡ ስለዚህ የአሮን ክህነት ታላቁ ሊቀ ካህን እስከሚመጣበት ቀን ድረስ ብቻ የሚቆይ ጊዜያዊ ክህነት ነበር ማለት ነው፡፡ እንዲያውም፣ ብሉይ ኪዳን ተስፋ የሚያደርገው ሁለቱም ቢሮዎች በታላቁ ሊቀ ካህንና በመሲሃዊ ንጉሥ ስር በአንድነት እንደሚጠቃለሉ ነው፡፡

የዚህ ሃሳብ ግልፅ ሃረግ በመዝሙር 110 ቁጥር 4 ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ እንዲህ ይነበባል፡

> እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት አንተ ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ፥ እግዚአብሔር ማለ አይጸጸትም። (መዝ 110፥4)

በዚህ መዝሙር አውድ መሠረት፣ የመሲሁ የክህነት አገልግሎት የማያበቃና ለዘላለም እንደሚሆን እግዚአብሔር ተስፋ ሰጥቷል፡፡

ዕብራውያን ምዕራፍ 7 ይህንን ሃሳብ ያነሳና በእግዚአብሔር ህዝብ ላይ ሊቀ ካህናት ሆኖ ከሚያገለግለው ከኢየሱስ ጋር በቀጥታ ያገናኘዋል፡፡ በዚያው ምዕራፍ ውስጥ የኢየሱስ የዘላለም ክህነት ከአዲሱ ኪዳን እውነታ ጋር እንደሚገናኝ፣ ይህም በነቢዩ በኤርምያስ በምዕራፍ 31 ቁር 31 ላይ በተነገረው ትንቢት መሠረት እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ በዚያ ምንባብ፣ በአዲሱ ኪዳን ሕይወት ፍፁምና አስደናቂ እንደሚሆን ኤርምያስ አመልክቷል፡፡ የዕብራውያን ፀሐፊ ነገሩን ከዚህ ጋር በማያያዝ፣ ይህ የተሻለ ኪዳን የተሻለ ክህነት እንደሚያስፈልገው፣ ያም ለዘላለም ሊሆን እንደሚገባው ሙግቱን ያቀርባል፡፡

የዕብራውያን ፀሐፊ መዝሙር 110 ቁጥር 4 በመጥቀስ፣ በዕብራውያን ምዕራፍ 7 ቁጥር 21 እና 22 ላይ እንዲህ ያስቀምጠዋል፡

> ... እርሱ ግን፦ ጌታ። አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ ማለ አይጸጸትም ብሎ በተናገረለት ከመሐላ ጋር ካህን ሆኖአልና ያለ መሐላ ካህን እንዳልሆነ መጠን፥
>
> እንዲሁ ኢየሱስ ለሚሻል ኪዳን ዋስ ሆኖአል። (ዕብ 7፥21 -22)

ስናጠቃልለው፣ በአዲሱ ኪዳን፣ እግዚአብሔር ክህነቱ ለዘላለም የሆነ ታላቅ ሊቀ ካህን እንደሚሾም ብሉይ ኪዳን በግልፅ አመልክቷል ማለት ነው፡፡

ታላቁ ሊቀ ካህን ንጉሥ ሆኖም እንደሚገዛ በግልፅ የተተነበየው ትንቢት ሁለተኛው ብሉይ ኪዳን ከክህነት አገልግሎት የሚጠብቀው ተግባር ነው፡፡

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፣ በኤድን ገነት ውስጥ የሰው ዘር ካህንም ንጉሥም ሆኖ ያገለግል ነበር፡፡ መልከጼዴቅም በሁለቱም ያገለግል ነበር፡፡ ጥቂት ከቆየ በኋላ የተለያዩ ቢሆንም አንኳን፣ በመሲሁ አማካይነት መልሰው አንድ እንደሚሆኑ ብሉይ ኪዳን ተንብዮአል፡፡

አንድ ጊዜ መልሰን መዝሙር 110ን እንመልከተው፣ አሁን ግን ከቁጥር 2 እስከ 4 ያለውንና ስለሚመጣው መሲህ ጌታ የሰጠውን ተስፋ እናያለን፡

> እግዚአብሔር የኃይልን በትር ከጽዮን ይልክልሃል በጠላቶችህም መካከል ግዛ። ከአንተ ጋር ቀድሞ በኃይልህ ቀን፥ በቅዱሳን ብርሃን፥ ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድሁህ።

> እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት አንተ ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ፥ እግዚአብሔር ማለ አይጸጸትም። (መዝሙር 110፥2-4)

በዚህ ስፍራ፣ መሲሁ ከዳዊት ዘር እንደሚሆን፣ እንደ ንጉሥ እንደሚገዛ እንደ ካህንም እንደሚያገለግል እግዚአብሔር ተስፋ ይሰጣል፡፡

ይኸው ተመሳሳይ ሃሳብ በዘካርያስ ምዕራፍ 6 ቁጥር 13 ላይ ስለ ሚመጣው መሲህ በተነገረው ትንቢት ውስጥ ይገኛል፡-

> በዙፋኑም ላይ ተቀምጦ ይነግሣል በዙፋኑም ላይ ካህን ይሆናል (ዘካ 6፥13)

እንደ ብሉይ ኪዳን አገላለጥ፣ ከክህነት አገልግሎት የሚጠበቀው ነገር መሲሁ ከንግሥና አገልግሎት ጋር የሚያቀናጀው የመሆኑ ነገር ነው፡፡

ሦስተኛው ከክህነት አገልግሎት የሚጠበቀው ግልፅ ትንቢት ደግሞ የእግዚአብሔር ህዝብ ራሱ የካህናት መንግሥት እንደሚሆኑ የተነገረው ነው፡፡

በዘፍጥረት ምዕራፍ 2 ቁጥር 15 እንደምንመለከተው፣ የሰው ዘር በኤድን ገነት የጀመረው በክህነት ሥልጣን በማገልገል ነው፡፡ እንግዲያው፣ በኃጢአት ከወደቅን በኋላ፣ በእግዚአብሔር ቤዝዎት ባገኘነው ኅዳሴ የተዋጀው የሰው ዘር እግዚአብሔርን እንደ ካህን መልሶ ማገልገሉ አያስገርምም ማለት ነው፡፡ እናም፣ ይህ ግልፅ ትንቢት በዘፀአት ምዕራፍ 19 ቁጥር 6 እና በኢሳያስ ምዕራፍ 61 ቁጥር 6 ውስጥም ተቀምጧል፡፡ መሲሁ እንደ ንጉሥ ሲነግሥ፣ የእግዚአብሔር ህዝብ እንደ ታማኝ ካህናት እንደሚያገለግል እና እንደ አንድ መንግሥት እንደሚተባበር ወይንም የካህናት መንግሥት እንደሚሆን ሁለቱም ምንባቦች ያመለክታሉ፡፡ የነገረ መለኮት ምሁራኑም ይህንን አማኞች ሁሉ ካህናት ከሚሆኑበት ጋር ያጣቅሱታል፡፡ ሐዋርያው ጴጥሮስም ይህ እውነት በእርሱ ዘመን እንደተከናወነ አመልክቷል፡፡

> *በ1ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 2ቁጥር 5 ምን እንደ ጻፈ እድምጡ፡*
>
> *እናንተ ደግሞ እንደ ሕያዋን ድንጋዮች ሆናችሁ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ። (1ጴጥ 2፥5)*

እንደ ኪዳን አስማሚዎች፣ የብሉይ ኪዳን ኪህናት ከእግዚአብሔር ጋር ስላላቸው የቃል ኪዳን ግንኙነት ህዝባቸውን ያለማቋረጥ ያሳስቡ ነበር፡፡ ኃጢአት በፍጥረት

ላይ ያመጣው ውድመት እስካለ ድረስ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት በዘላቂነት ከማስፋፋትና ዓላማውንም ከማሳካት አንፃር የክህነት አገልግሎት እጅግ ወሳኝና አስፈላጊ ነው፡፡ ግን ዓላማዎቹ በታሪክ ዘመናት ሁሉ የክህነት አገልግሎት ማዕከል የሆነውና ብሉይ ኪዳን ተስፋ የሚያደርገው መሲህ በሌለበት ሊከናወን አይችልም፡፡

የክህነትን አገልግሎት ብሉይ ኪዳናዊ ዳራ ከተመለከትን፣ አሁን ወደ ቀጣዩ ዐቢይ ርዕሳችን፡ የክህነት አገልግሎት በኢየሱስ ያገኘውን ፍፃሜ ወደምንመለከትበት ዘወር እንላለን፡፡

## 3. ምልዓት በኢየሱስ

ብሉይ ኪዳን ከክህነት አገልግሎት የሚጠብቀውን ሁሉ ኢየሱስ እንደፈፀመ ወንጌላትና የአዲስ ኪዳን መልእክቶች በግልፅ እንዳስቀመጡት በመግለፅ እንጀምራለን፡፡

ለምሳሌ፣ በዕብራውያን ምዕራፍ 3 ቁጥር 1 ውስጥ ስለ ኢየሱስ የክህነት አገልግሎት ይህን ግልፅ ማረጋገጫ እናነባለን፡

> ስለዚህ፥ ከሰማያዊው ጥሪ ተካፋዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ፥ የሃይማኖታችንን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ፤ (ዕብ 3፥1)

ዕብራውያን ምዕራፍ 4 ቁጥር 14 ደግሞ በዚህ መንገድ ያስቀምጠዋል፡

> እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን፥...

እንደ ታላቅ ሊቀ ካህናችን፣ በእኛና በእግዚአብሔር መካከል መካከለኛ የሆነው ኢየሱስ ነው፣ ስለዚህም እኛ በእግዚአብሔር የተቀደሰ ኅላዌ ውስጥ መገኘት ችለናል፡፡ እኛ ቅዱሳንና ለእግዚአብሔር የተቀደስን መሆናችንን የሚያረጋግጥልን እርሱ ነው፣ ስለዚህም በእርሱ ኅልውና ውስጥ ልንኖርና የቃል ኪዳኑንም በረከት ልንቀበል እንችላለን፡፡

የክህነት አገልግሎት በኢየሱስ ያገኘውን ፍፃሜ ብሉይ ኪዳናዊ ዳራውን በተመለከትንባቸው ተመሳሳይ ጎራዎች እንመለከተዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ኢየሱስ እንዴት የአገልግሎቱን መመዘኛ እንዳሟላ እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ እንዴት ተግባሩን እንደፈፀመ እናያለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ከክህነት አገልግሎት የሚጠበቀውን እንዴት እንደፈፀመ እንመለከታለን፡፡ አስቀድመን ኢየሱስ እንዴት የክህነትን አገልግሎት መመዘኛዎች እንዳሟላ እንመለከታለን፡፡

## መመዘኛዎች

ብዙ ሰዎች ኢየሱስ በመቅደስ አገልግሎ እንደማያውቅ ወይንም ስርዓቶችን አስፈፅሞ እንደማያውቅና የአሮን ዘርም እንዳልሆነ ይጠቅሳሉ፡፡ ታዲያ፣ የአዲስ ኪዳን ጸሐፍት ኢየሱስ የክህነትን ተግባርና አገልግሎት ፈፅሟል ብለው እንዴት ሊጠቅሱ ቻሉ? እንዴትስ ለክህነት አገልግሎት ብቁ ሆነ? በቀላሉ ለማስቀመጥ፣ ኢየሱስ ለአገልግሎቱ ብቁ የሆነው ለንጉሣዊ ክህነት ብሉይ ኪዳን ተስፋ ያደርግ የነበረውን ሁሉ ስላሟላ እና እግዚአብሔር ራሱ በክህነት አገልግሎት ሁሉ ላይ ስለሾመው ነው፡፡

ኢየሱስ ለክህነት አገልግሎት ብቁ መሆኑን ለብሉይ ኪዳን የክህነት አገልግሎት ብቁ የሚኮንባቸውን ታሪካዊ ዳራዎች በተመለከትንበት ተመሳሳይ መንገድ እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ኢየሱስ ለክህነት የተሾመው በእግዚአብሔር መሆኑን እንጠቅሳለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ ለእግዚአብሔርም ታማኝ መሆኑን እናያለን፡፡ እስኪ በመጀመሪያ ኢየሱስ በእግዚአብሔር የመሾሙን እውነት እንመልከት፡፡

## በእግዚአብሔር መሾም

ዕብራውያን ምዕራፍ 5 ከቁጥር 4 እስከ 10 በግልፅ እንደሚናገረው እግዚአብሔር ኢየሱስን እንደ ሊቀ ካህን ሾሞታል፡፡ እስኪ የሚናገረውን አድምጡ፡

> እንደ አሮንም በእግዚአብሔር ከተጠራ በቀር ማንም ክብሩን ለራሱ የሚወስድ የለም።
> እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ ሊቀ ካህናት ሊሆን ራሱን አላከበረም ነገር ግን። አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ ያለው እርሱ ነው፤
> እንደዚህም በሌላ ስፍራ ደግሞ። አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ ይላል።
> እርሱም በስጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፥ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት፤
> ምንም ልጅ ቢሆን፥ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ፤
> ከተፈጸመም በኋላ በእግዚአብሔር እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ሊቀ ካህናት ተብሎ ስለ ተጠራ፥ ለሚታዘዙለት ሁሉ የዘላለም መዳን ምክንያት ሆነላቸው።
> (ዕብ 5፥4-10)

እግዚአብሔር እስከ ሾመው ድረስ፣ ኢየሱስ በእርግጥም መመዘኛዎቹን ያሟላል፡፡ በተመሳሳይም፣ ኢየሱስ የሌዋውያን ዝርያ የሌለው በመሆኑ ምክንያት ይህ ሹመት ያልተለመደ መሆኑን ልንቀበለው ይገባል፡፡ በብሉይ ኪዳን ጅማሬ ላይ፣ የተለያዩ

ሰዎች ካህናት እንዲሆኑ እግዚአብሔር መፍቀዱን መለስ ብላችሁ ተመልከቱ፡፡ በብሉይ ኪዳን ፍጻሜ ግን፣ የክህነትን አገልግሎት ለሳዶቅ ዝርያ ብቻ ሰጥቷል፡፡ እንዲያውም፣ የኢየሱስ ሹመት በመጀመሪያ ጊዜ ሲገለጥ እንደነበረው ዐይነት ያልተለመደ አይመስልም ነበር፡፡

በኤድን ገነት ውስጥ፣ አዳም የእግዚአብሔር ቫሳል ንጉሥ ሆኖ በምድር ላይ እንዲያገለግል ተሾሞ ነበር፡፡ አገዛዙ መላው ዓለም ለእግዚአብሔር ክቡር ጎላዌ ምቹ ስፍራ እንዲሆን ለማድረግ በሚያስችል መልክ የተነደፈና የክህነት ተግባር የሚከናወንበትም ነው፡፡ በነገሥታቱ ዘመን ደግሞ የክህነትና የንግሥና ቢሮ በጥብቅ የተሳሰሩ ነበሩ፡፡

በተመሳሳይ መንገድም፣ ኢየሱስ ንጉሣዊ ካህን ነው፡፡ እንደ እግዚአብሔር ቫሳል ንጉሥ ይገዛል፡፡ አገዛዙ ግን እኛንና ምድርን ለእግዚአብሔር ልዩና ክቡር ጎላዌ በሚያዘጋጅ መልኩ የክህነት አገልግሎትንም የሚያካትት ነው፡፡ በዚህ መንገድ፣ አዳምና ዝርያዎቹ ሁሉ ማድረግ የተሳናቸውን ክርስቶስ ይፈፅማል ማለት ነው፡፡

እስኪ አንድ ጊዜ እንደገና ዳዊት በመዝሙር 110 ከቁጥር 1 እስከ 4 ስለ ታላቁ መሲህ የተናገረውን እናድምጥ፡

> እግዚአብሔር ጌታዬን፦ ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው።
> እግዚአብሔር የኃይልን በትር ከጽዮን ይልክልሃል በጠላቶችህም መካከል ግዛ።
> ከአንተ ጋር ቀድሞ በኃይልህ ቀን፥ በቅዱሳን ብርሃን፥ ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድሁህ።
> እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት አንተ ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ፥ እግዚአብሔር ማለ አይጸጸትም። (መዝ 110፥1-4)

በዚህ ምንባብ፣ ዳዊት "ጌታዬ" ብሎ የሚጠራው መሲህ፣ በንጉሣዊ ኃያልነቱና ብርቱ አገዛዙ፣ ደግሞም በካህንነቱ ተገልጧል፡፡

የዳዊት ትንቢት ከዘሩ መካከል አንዱ አንድ ቀን ወደዚህ ግርማዊ መንበረ ንግሥና እንደሚወጣ፣ ንጉሣዊ አገልግሎት ብቻ ሳይሆን የክህነትንም አገልግሎት ልክ እንደ መልከ ጼዴቅ እንደሚሰጥ በሩቁ የሚያመለክት ነው፡፡ ዕብራውያን ምዕራፍ 7 ቁጥር 14 ኢየሱስ ከይሁዳ ስርወ-መንግሥት እንጂ፣ ከሌዊ የክህነት ወገን እንደማይሆን አፅንዖት ሰጥቶ የሚናገረው ለዚህ ነው፡፡ ኢየሱስ ከይሁዳ ነገድ የሆነው ንጉሥና

ታላቁ ሊቀ ካህን የመሆኑ እውነታ ሲጠበቅ የኖረው የዳዊት ልጅ፣ መሲሁ መሆኑን ያመለክታል፡፡

*ይህ ነገር በአብዛኛው ወደ ዘፍጥረት ምዕራፍ 14 አንደ ንጉሥና እንደ ካህን ወደ ተገለጠው መልከፄዴቅ፣ ይመልሰናል ምክንያቱም እርሱ አብርሃም መስዋዕትን ባቀረበለት ወቅት መልከፄዴቅም እንደ ካህን ተቀብሎት ነበርና ነው፡፡ እርሱ በተጨማሪም በግልፅ የሳሌም ንጉሥ ነው፡፡ እንግዲያው በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች በጠቅላላ ነገሥታትና ካህናት አንዳንድ ጊዜ አንድና ተመሳሳይ ሆነው የሚታዩበት ነገር የሚያጠነጥነው በዚህ ዙሪያ ነው፡፡ ንጉሥ ልክ እንደ ጽድቅ የበላይ ጠባቂ የተገለጠበት ክፍል መዝሙር 110 ነው፡፡ አዎን፣ በዚህ አባባል ውስጥ መንግሥታዊ ገፅታዎች ተገልፀውበታል፣ የጽድቅ የበላይ ጠባቂ ሲኮን ግን፣ የክህነት አገልግሎትንም መካፈል ይመጣል፣ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ጽድቁ መላው ዓለም የእርሱ ጽድቅ ተካፋይ ይሆን ዘንድ ፈቃዱ መሆኑ ነውና፡፡ አንግዲያው ንጉሡ በዚህ ውስጥ ሲሳተፍ፣ ምንም እንኳን ለክህነት አገልግሎት የተለዩ ካህናት ቢኖሩም፣ ንጉሡ አሁንም በክህነታዊ መንገድ ይሳተፋል፡፡ እናም፣ ወደ ኢየሱስ ስንመጣ፣ እነዚህ ምንጮች አንድ ላይ ይጋጠማሉ፣ ስለዚህም እርሱ ነቢይ፣ ካህንና ንጉሥ ነው፡፡ በእርግጥም በዕብራውያን መጽሐፍ እንደተገለጠው፣ እርሱ አዲሱ መልከፄዴቅ ነው፡፡ እርሱ በቀደመው ኪዳን የነበረውን እግዚአብሔርን የገለጠ የአዲሱ ኪዳን ሰብዕና ነው፡፡ [ዶ/ር ስቲቭ ሃርፐር]*

ኢየሱስ በእግዚአብሔር የተሾመ መሆኑን ከተመለከትን፣ እርሱ ለእግዚአብሔር ታማኝ የመሆንን መመዘኛ እንዳሟላ ለመመልከት ዝግጁ እንሆናለን ማለት ነው፡፡

## ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን

ቀደም ብለን እንደጠቀስነው፣ ክህናት በከፍተኛ መጠን እግዚአብሔርን ሊያመልኩና እርሱንም ብቻ ሊያገለግሉ፣ እግዚአብሔርም የሰጣቸውን ሃላፊነት በጥንቃቄ በመፈፀም ለእግዚአብሔር ያላቸውን ታማኝነት ሊገልጡ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የሃላፊነታቸውም ተቀዳሚ ምክንያት የእግዚአብሔር ህዝብም ለእግዚአብሔር ታማኝ ማለትም በግብረገብም፣ በስርዓትም የታመነ እንዲሆን ለማድረግና ወደ እግዚአብሔር ልዩ ኀላዌ ያለ ፍርሃት እንዲገባ ማድረግ ነው፡፡ ካህናት ከሚሰጡት አገልግሎት ዋነኛው ይህ ነው፡፡

ኢየሱስም እነዚህን ተመሳሳይ መመዘኛዎች በፍፁምነት አሟልቷቸዋል፡፡ እርሱ ዘወትር እግዚአብሔርን ብቻ ያገለግላል እርሱንም ብቻ ያመልካል፡፡ የአብንም

ትእዛዛት ዘወትር ይፈፅማል፡፡ እናም በክህነት አገልግሎቱ፣ እኛ ወደ እግዚአብሔር ልዩ ኅላዌ መግባት እንችል ዘንድ ኢየሱስ አዘጋጅቶናል፡፡

በጥቅሉ፣ የአራቱም ወንጌላት ሙሉ ይዘታቸው ኢየሱስ ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆኑን የሚያረጋግጥ እንደሆነ መመልከት እንችላለን፡፡ አብ የሰጠውን ተልዕኮ ይፈጽም ነበር፤ አብ እንዲናገር የሰጠውን ብቻ ይናገር ነበር፤ አባቱ ሲያደርግ ያየውን ብቻ ያደርግ ነበር፡፡ ይህንን ሃሳብ ጠቅለል አድርገው የሚያቀርቡ በርካታ የአዲሰ ኪዳን ግልፅ ምንባቦችም በተጨማሪ አሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ማቴዎስ ምዕራፍ 26 ቁጥር 42፤ ዮሐንስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 19፣ ምዕራፍ 14 ቁጥር 31 እና ምዕራፍ 17 ቁጥር 4 ደግሞም ዕብራውያን ምዕራፍ 7 ከቁጥር 5 እስከ 7 ይጠቀሳሉ፡፡

የኢየሱስ ለአብ ፍፁም መታዘዝ እንደ ታላቅ ሊቀ ካህናችን ለሚያከናውነው ተግባር እጅግ ወሳኝነት አለው፡፡ ለእግዚአብሔር ፍፁም ታማኝ በመሆን ብቻ ተከታዮቹም ፍፁም ቅዱሳን እንዲሆኑና ለዘላለምም በእግዚአብሔር ልዩ የተቀደሰ ኅላዌ ውስጥ መግባት እንዲችሉ ማብቃት ይችላል፡፡ ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን በርካታ የቅዱሳት መጻሕፍ ምሳሌዎች አሉ፡፡ ለአብነት ያህል፣ በዮሐንስ ምዕራፍ 17 ቁጥር 19 በጸለየው ክህነታዊ ፀሎት ውስጥ ስለ መቀደሳችን ጸልዮአል፡፡ ሮሜ ምዕራፍ 15 ቁጥር 16 እና 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 6 ቁጥር 11 የመሳሰሉትን ምንባቦች ስንመለከት፣ እኛን በፊቱ ቅዱሳን እንድንሆን በማድረግ እግዚአብሔር ይህንን ፀሎት መልሷል፡፡

ኢየሱስ የክህነትን አገልግሎት መመዘኛ ማሟላቱን ከተመለከትን፣ የክህነትን አገልግሎት ተግባራት ያሟላበትን መንገድ ወደ መመልከቱ እንሸጋገራለን፡፡

## ተግባራት

የኢሱስን የክህነት አገልግሎት ተግባር የብሉይ ኪዳንን የክህነት አገልግሎት ተግባር በተመለከትንበት ሁኔታ እንመለከተዋለን፡ በመጀመሪያ፣ ለእግዚአብሔር ህዝብ ክህነታዊ አመራር መስጠት፤ ሁለተኛ፣ ክህነታዊ ስርዓቶች፤ ሦስተኛ ደግሞ፣ ካህናዊ ምልጃ ናቸው፡፡ ኢየሱስ ካህናዊ አመራርን እንዴት እንደሰጠ አስቀድመን እንመልከት፡፡

## አመራር

ስለ ኢየሱስ አመራር ትኩረት ልንሰጣቸው የሚችሉ በርካታ ሁኔታዎች ቢኖሩም፣ ስለ ኢየሱስ ክህነታዊ አገልግሎት በተመለከትናቸው ብሉይ ኪዳናዊ ዳራዎች

በተጠቀሱት በሦስቱ ላይ ብቻ እናተኩራለን፡፡ በአምልኮ ወቅት የሚሰጠውን አመራር በመመልከት እንጀምራለን፡፡

ከፍ ሊልና ሊከብር እንደተገባው እንደ አንድ ታላቅ ሊቀ ካህን፣ በእስራኤልና በአመኑትም መካከል እውነተኛና መንፈሳዊ አምልኮ ይኖር ዘንድ ኢየሱስ በርካታ ነገሮችን አድርጓል፡፡ ለምሳሌ፣ በማቴዎስ ምዕራፍ 21 ቁጥር 12 እና 13 ውስጥ ከመቅደስ ውስጥ ነጋዴዎችንና ገንዘብ ለዋጮችን አስወጥቷል ምክንያቱም የእግዚአብሔርን የጸሎት ቤት ወደ ወንበዴዎች ዋሻነት ለውጠው ነበርና ነው፡፡

ከሁሉ እጅግ የሚልቀው ግን፣ የእግዚአብሔር ህዝብ በሰማያት ወዳለው ቅዱስ መቅደስ በመግባት ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርብ ማስቻሉ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን፣ የመገናኛው ድንኳን በኋላም ደግሞ መቅደሱ ሰማይና ምድር የሚገናኙባቸው ስፍራዎች ነበሩ፡፡ አምልኮ የሚያቀርቡ ሰዎች በምድር ደግሞም በሰማይ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት በተደጋጋሚ የሚቀርቡባቸው ልዩ ስፍራዎች ነበሩ፡፡ በአዲስ ኪዳን ግን፣ ኢየሱስ ራሱ እነዚህን ተግባራት ተረከባቸው፡፡ ስለዚህም፣ ወደ እግዚአብሔር ሰማያዊ መንበር ለመግባት ወደ አንድ ልዩ ሕንፃ ከመሄድ ይልቅ፣ ኢየሱስ ራሱ ወደዚያ ወሰደን፡፡ በእርሱም አማካይነት፣ ከእርሱ ጋር በመሆን የሚገኘውን በረከት ወደምናገኝበት ወደ እግዚአብሔር ልዩና ቅዱስ ኀላዌ መግባት ቻልን፡፡

> ዕብራውያን ምዕራፍ 10 ከቁጥር 19 እስከ 22 ስለዚህ ነገር የሚናገረውን እናድምጥ፡
>
> እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት
> በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት ስላለን፥
> በእግዚአብሔርም ቤት ላይ የሆነ ታላቅ ካህን ስላለን፥
> ከክፉ ሕሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን ሰውነታችንንም በጥሩ ውኃ ታጥበን
> በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ፤ (ዕብ 10፥19-22)

ኢየሱስ በተጨማሪም በህዝባዊና በትውፊታዊ የፍርድ ስርዓቶችም ክህነታዊ አመራር ሰጥቷል፡፡

ለምሳሌ፣ በማቴዎስ ምዕራፍ 12 ከቁጥር 1 እስከ 8፣ ደቀመዛሙርቱ ሰንበትን ባለማክበር በተከሰሱበት ወቅት ኢየሱስ ክህነታዊ ብይን ሰጥቷል፡፡ በማርቆስ ምዕራፍ 7 ቁጥር 19 ላይ፣ ስለ ልማዳዊው የምግብ ንፅሕና ጉዳይ ፍርድ ሰጥቷል፡፡ በማቴዎስ ምዕራፍ 8 ለምፃሙን ካነፃ በኋላ፣ ሰውየው በወጉ መሠረት ንፁህ መሆኑን

ያወጀ ሲሆን ሰውየውንም ወደ መቅደስ በመሄድ ተገቢ መስዋዕት እንዲያቀርብ አዝዞታል፡፡ በተጨማሪም ኢየሱስ ሰውየው ራሱን ለካህን እንዲያሳይ ያዘዘው ሲሆን፣ ዓላማውም በሁኔታው ላይ እንዲፈርዱ አልነበረም፡፡ ማቴዎስ ምዕራፍ 8 ቁር 4 እንደሚነግረን ግን፣ የኢየሱስ ሥልጣንና ኃይል ምስክር እንዲሆን ነበር፡፡

ሦስተኛውና የምንጠቅሰው ካህናዊ አመራር ማስተማር ነው፡፡ ኢየሱስም ይህንን ተግባር ፈፅሟል፡፡

እስራኤል የተለያዩ አስተማሪዎች እንደነበሯት እውን ነው፡፡ ነቢያትም የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳንና ፈቃድ የሚያውጁ አስተማሪዎች ነበሩ፡፡ ወላጆች ልጆቻቸውን ያስተምራሉ፡፡ ራቢዎች (የህግ መምህራን) እና ሽማግሌዎችም ማኅበረሰባቸውን ያስተምራሉ፡፡ ካህናት ግን፣ በአብዛኛው የሚያተኩሩት ስለ ንስሓና ተኣማኒነት በማስተማሩና የእግዚአብሔር ህዝብ በእግዚአብሔር ልዩ ኅልውና ውስጥ ተቀባይነት እንዲያገኝ በማድረጉ ላይ ነው፡፡ የዚህንም ምሳሌ በነህምያ ምዕራፍ 8 ውስጥ እንመለከተዋለን፡፡ የኢየሱስም አገልግሎት በተደጋጋሚ ጊዜ ይህንኑ የክህነት ተግባር የሚያካትት ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ ከማቴዎስ ምዕራፍ 5 እስከ 7 በሚገኘው የተራራው ስብከት ውስጥ፣ የሚሰሙት ሰዎች ለቃል ኪዳኑ ታማኝ እንዲሆኑ ለማስቻል ኢየሱስ የእግዚአብሔር ህግ በተግባር የማዋልን እውነተኛ መነሳሳት አብራርቷል፡፡ በማቴዎስ ምዕራፍ 4 ቁጥር 17፤ ሉቃስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 32 እና በዮሐንስ ምዕራፍ 14 ከቁጥር 15 እስከ 24 ባሉት ምንባቦች እንደምናየው፣ ንስሓና ታማኝነት የትምህርቱ የማይቀሩ አዝማቾች ነበሩ፡፡

ኢየሱስ የክህነታዊ አመራርን ሃላፊነት የተወጣ መሆኑን ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ስርዓትን ከማስፈፀም አንፃር የክህነትን ተግባር ያከናወነበትን መንገድ እንመለከታለን፡፡

## ስርዓቶች

የኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞት ያለ ጥርጥር፣ የክህነት አገልግሎቱ ታላቅ ሥነ-ሥርዓት ነው፡፡

ኢየሱስ ራሱ በእሥራኤል ሥነ-ስርዓቶች ውስጥ ተሳትፏል፡፡ እንዲያውም፣ አብዛኞቹ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ተጠቅሰዋል፡፡ በመስቀል ላይ ኢየሱስ ከከፈለው መስዋዕትነት ውጪ አንዳቸውም ለእግዚአብሔር ህዝብ ቤዛነትን ሊያስገኙ አልቻሉም፡፡ የኢየሱስ መሰቀል፣ ያለጥርጥር የክህነት አገልግሎቱ ታላቅ ሥነ-ስርዓት ነው፡፡ የሙሴ ህግ ከእስራኤል መታዘዝን ይጠይቃል፣ እስራኤል ግን ባለመታዘዝ

እንደሚቀጥሉ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ፣ ለኃጢአታቸው ማስተሰረያ ይሆን ዘንድ እስራኤል መስዋዕትን ለእግዚአብሔር እንዲያቀርቡም አዝዟቸዋል፡፡ እነዚህ መስዋዕቶች አስፈላጊ ቢሆኑም፣ በየዓመቱም ደጋግመው ሊቀርቡ ይገባቸዋል፣ አንዳቸውም የእስራኤልን ኃጢአት ሙሉ በሙሉ ሊያስወግዱ አይችሉም፡፡ ስለዚህም ኢየሱስ ራሱን ፍፁም የሆነ የኃጢአት መስዋዕት አድርጎ ለማቅረብ መጣ፡፡ የእርሱም የስርየት መስዋዕት የእስራኤል መስዋዕቶች ሊያሟሉ በማይችሉ መጠን ቤዝዎትን አስገኝቷል፡፡ እናም ኢየሱስ አንዴና ለዘላለም ባቀረበው መስዋዕት እስራኤል ከክህነት አገልግሎት የምትጠብቀውን አሟልቷል፡፡

*የብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች ኃጢአትን አንዴና ለዘላለም የሚያስወግድ ፍፁም መስዋዕት እንደሚመጣ ያመለክቱ ነበር፡፡ ኢየሱስ በመስቀል ላይ የፈፀመው ተግባር በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠው ለኃጢአት መስዋዕት ደግሞም መስዋዕቱን የሚያቀርበው ካህን ራሱ እንደሆነ ነው፡፡ ማለትም ሁለቱንም ተግባራት በጣምራ አከናውኗል ማለት ነው፡፡ የዓለምን ኃጢአት ያስወገደውን የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ራሱን ሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም ደግሞ ኢየሱስ እስከዚያን ድረስ የነበሩትን መስዋዕቶች ሁሉ መደምደሚያ ሊያደርጋቸው እርሱ ራሱ መስዋዕቱን የሚያቀርበው ካህንም ሆኖ ተገልጧል፡፡ [ዶ/ር ሲሞን ቫይበርት]*

*በኢየሱስ ሞትና በብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች መካከል ያለው ግንኙነት በተሟሉ በርካታ መንገዶች ሊገነባ ይገባዋል፡፡ ወደ ማዕከላዊው ነጥብ ስንመጣ፣ የብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች እግዚአብሔር ለእስራኤል ህዝብ በሰጠው የቀደመ ኪዳን ውስጥ ሊቀመጡ ይገባቸዋል፡፡ የመስዋዕት ስርዓቶቹ የህዝቡ ኃጢአት የሚወገድበትንና የእግዚአብሔርም ቁጣ የሚመለስበትን፤ በዚያም በእግዚአብሔርና በህዝቡ መካከል ግንኙነት መኖሩን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ እነዚያ መስዋዕቶች፣ የበለጠው እንደሚመጣ በርቀት የሚያመለክቱ ተምሳሊቶች ነበሩ፡፡ በብሉይ ኪዳንም እንኳን የእንስሳት መስዋዕት ኃጢአትን ሊያስወግድ እንደማይችል የሚጠቁሙ በርካታ ፍንጮች ነበሩ፡፡ አስቀድሞውንም በዚያ መንገድ ኃጢአት ሊወገድ ይችላል በሚል ዓላማ አልተሰጡም ነበር፡፡ ይልቁንም የሚመጣውን የሚበልጥ ነገር የሚያመለክቱ ተምሳሊቶች ነበሩ፡፡ ያም እንደ እንደ መስዋዕቶቹ ሁሉ፣ ምትካችን የሚሆነው የክርስቶስ መስዋዕትነት ነው፡፡ እርሱ የእኛ ምትክ ነው፡፡ እርሱም ሰው በመሆኑ እጅግ የላቀ ነገር ሊያደርግ ተችሎታል፡፡ የእኛን ሰውነት ወስዷል፡፡ እንስሳቶቹ ግን ይህን ማድረግ አይችሉም፡፡ እርሱ በሥጋ የተገለጠው እግዚአብሔር ወልድ ነው፡፡ ስለዚህም የእኛን ኃጢአት በማስወገድ፣ ወኪላችን ሆኖ በመቆም፣ ምትካችን በመሆን፣*

*ካህናችን በመሆን የራሱን የጽድቅ መመዘኛ አሟልቷል፡፡ በዚህም መስዋዕቶቹ ሁሉ ያመለክቱለት የነበረውን መመዘኛ አሟልቷል፣ ከእግዚአብሔር ጋር ወደ ነበረን የቀደመ ግንኙነትም መልሶናል፣ አስቀድሞም እንድንሆን የተፈጠርንበትን እንድንሆን ማለትም ህዝቡ እንድንሆን፣ ለእርሱ እንድንኖር፣ በዚህም ዓለም የእርሱ አምሳል መገለጫዎች የመሆን ድርሻችንን እንድንወጣ አስችሎናል፡፡ [ዶ/ር ስቴፋን ዌሉም]*

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፣ የብሉይ ኪዳን ካህናት የኃጢአትን መስዋዕት፣ ምስጋናና የኅብረት መስዋዕትን ጨምሮ የተለያዩ መስዋዕቶችን የማቅረብ ሃላፊነት ነበረባቸው፡፡ ኢየሱስም በመስቀል ላይ ሞቱ፣ በታሪክ ዘመናት ሁሉ ያቀረቡትን መስዋዕቶች ሁሉ የሚያስመሰግን ብቸኛ መስዋዕት አቅርቧል፡፡ ለበደል ስርየት የሚቀርቡ ቀደምት መስዋዕቶች ሁሉ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞት የሚያቀርበውን መስዋዕት በጥላነት የሚያመለክቱ ነበሩ፡፡ ይህ እውነት በሮሜ ምዕራፍ 3 ቁጥር 25፣ ምዕራፍ 8 ቁጥር 3፤ 1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 2 እና ምዕራፍ 4 ቁጥር 10 በመሳሰሉት ውስጥ ተቀምጧል፡፡

አንዱን ለምሳሌ ለመጥቀስ፣ ዕብራውያን ምዕራፍ 10 ከቁጥር 1 እስከ 4 የሚናገረውን እናድምጥ፡

> ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና፥
> ስለዚህም በየዓመቱ ዘወትር በሚያቀርቡት በዚያ መሥዋዕት የሚቀርቡትን ሊፈጽም
> ከቶ አይችልም።
> እንደዚህማ ባይሆን፥ የሚያመልኩት አንድ ጊዜ ነጽተው ከዚያ በኋላ በሕሊናቸው
> ኃጢአትን ስላላወቁ ማቅረብን በተዉ አልነበረምን?
> ነገር ግን በዚያ መሥዋዕት በየዓመቱ የኃጢአት መታሰቢያ አለ፤
> የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን እንዲያስወግድ የማይቻል ነውና።
> (ዕብ 10፥1-4)

የብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች አቅራቢውን የሚጠቅሙት በመስዋዕታቸው በራሳቸው ብቁነት ላይ ተመሥርቶ ሳይሆን፣ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሚያቀርበውን ልዩ መስዋእት በተምሳሊትነት በሚያሳይ መንገድ ነው፡፡ ከዚያም ባሻገር፣ የሚያስገኙትም ጥቅም ሁሉም በአንድነት የሚያመለክቱት የኢየሱስ መስዋዕት እስኪቀርብ ድረስ ፍፁምነት አልነበረውም፡፡ የዚህም ምክንያቱ የብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች ኃጢአትን ለዘላለም የማስወገድ ብቃት የሌላቸው መሆኑ ነው፡፡ የእነርሱ ተግባር ኢየሱስ መጥቶ በመስቀል ላይ እስኪሞት ድረስ የእግዚአብሔርን ቁጣ ማስታገስ ነበር፡፡

በዚህ ረገድ፣ ኢየሱስ የቀደሙት የስርየት መስዋዕቶች ያመለከቱት የነበረው አካሉ ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁኑ እርሱ የመጨረሻው የኃጢአት ስርየት ነው፡፡ የስርየት መስዋዕቶች ሁሉ ሙላታቸው በኢየሱስ እውን የሆነ ሲሆን፣ ከዚያም ወዲያ ዳግም ጥላዎቹን ማቅረብ አስፈላጊ አይሆንም፡፡ ክርስቲያኖች በብሉይ ኪዳን የተገለጡ መስዋዕቶችን ማቅረብ የማያስፈልጋቸው በዚህ ምክንያት ነው እንጂ የስርየት መስዋዕቶች አላስፈላጊ እንደሆኑ ስለምናን አይደለም፡፡ ይልቁኑ እኛ መስዋዕት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ እናውቃለን፡፡ መስዋዕት ማቅረብ የማያስፈልገን የኢየሱስ ብቸኛ መስዋዕትነት በዘመናት ሁሉ የሚኖሩትን የእግዚአብሔርን ታማኝ ህዝብ በደል አንዴና ለዘላለም እንዳስወገደና የእግዚአብሔርን መሻት እንዳሟላ ስለምናምን ነው፡፡ በዚህም ብቸኛ ተግባር፣ ቅድስናን አስገኘልን፣ በእግዚአብሔርም ልዩና የተቀደሰ ኅላዌ ውስጥ ለመገኘት ብቁ እንድንሆን አስችሎናል፡፡

በዕብራውያን ምዕራፍ 10 ቁጥር 10 እንደምናነብበው፡

*በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል። (ዕብ 10፥10)*

የኢየሱስ መስዋዕት የቀረበው በእግዚአብሔር መንግሥት አዲስ ዘመን ውስጥ ነው፤ ማለትም የምርኮው ዘመን ማከተሚያ እና በእግዚአብሔር ህዝብ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ በሚገለጥበት ጅማሬ ላይ ነበር፡፡ ስለዚህም የኢየሱስ ብቸኛ መስዋዕት በምድር ያለ ህዝብ ሁሉ የእግዚአብሔርን ይቅርታ እንዲቀበል አስችሎታል፡፡ ግን በሌላም ወገን በበርካቶች በማያምኑት ላይ  የእግዚአብሔር ትዕግሥት የማብቃቱ ደወልም  ጭምር ነው፡፡

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 17 ቁጥር 30 ውስጥ እንደምናነበው፣ ከክርስቶስ መስዋዕትነትም ቀደም ብሎ እግዚአብሔር እውነቱን ቸል ባሉትም ላይ ከመፍረድ ይልቅ መታገስን መርጦ ነበር፡፡  የክርስቶስ መስዋዕትነት ግን እውነት ቸል እየተባለ የመቆየቱ ነገር ብዙም ዕድሜ እንደማይኖረው በግልፅ አስታወቀ፡፡ በውጤቱም፣ ወንጌል ሲሰበክ እውነቱን ከመቀበልና ንስሓ ከመግባት በሚዘገዩት ላይ በታላቅ ፍጥነት እና ጭካኔ ፍርዱን ያስተላልፍ ጀመር፡፡

*አንዳንድ ከሃዲዎች የኢየሱስን ሞት አሳዛኝና በተሳሳተ ዓላማ የተፈፀመ እንጂ ከዚያ የዘለለ ነገር የሌለው እንደሆነ አድርገው ይመለከቱታል፡፡ ለሚያምኑት ግን፣ የክርስቶስ ሞት የታሰበበት፣ ወሳኝና ቤዝዎታዊ ዓላማ ያለው ነው፡፡ ያም የመስቀሉን ምሥጢር የመረዳታችን አካል ነው፡፡ ያም መረዳታችን፣ የብሉይ*

*ኪዳን መስዋዕቶች ፍፃሜ የማግኘታቸውና የታሰበበት ዓላማ ያለው መሆኑን መገንዘባችን ነው፡፡ በእኛ ዘመን የደም መስዋዕትነት የሚያስፈልግ የመሆኑ ጉዳይ የማይመቻቸው ብዙ ሰዎች አሉ፡፡ እጅግ በዘመነና በእውቀት በመጠቀ የሰለጠነ ዓለም፣ ኋላ ቀርና ተቀባይነት የሌለው ይመስላል፡፡ በመሠረቱ እግዚአብሔር የደም ጥማት ያለበት ጥማቱንም ለማርካት ደም የሚፈልግ ደም መጣጭ ኣጋንንት እንዳልሆነ ልናውቅ ያስፈልጋል፡፡ የብሉይ ኪዳን መስዋዕት፣ የብሉይ ኪዳን የመስዋዕቶች ሥርዓት በጠቅላላ የሚቀርቡበትን ምክንያት የኃጢአትን ክፋት የሚያመለክቱና የማያወላውሉ፣ ጭክን ያሉ እና የሚያነቃቁ ናቸው፡፡ የብሉይ ኪዳን መስዋዕታዊ ሥርዓቶች እግዚአብሔር ለፍጥረተ ዓለሙ ወዳዘጋጀው ሞራላዊ መጠነ ልክ ለመድረስ ይቻል ዘንድ ኃጢአት መፍትሄ ሊሰጠው የሚገባ እንደሆነ ለቀደመው ህዝብ የሚያሳስቡ ነበሩ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስም የመጣው የእግዚአብሔርን የፍትህና የሞራል ደረጃ ለማሟላት በሚያስችል መጠን በማይገደበው መስዋዕታዊ ፍቅር የእነዚያ ሁሉ ሙላት ለመሆን ነበር፡፡ ብሉይ ኪዳን ያመለከተው፣ በኢየሱስም የተፈፀመው መስዋዕት ከጥንት መስዋዕታዊ ስርዓቶች ጋር በዝርዝር የተገናኘ ነው፡፡ [ዶ/ር ግሌን ስኮርጂ]*

ኢየሱስ በአመራርና ሥርዓቶችን በማስፈፀም እንዴት አድርጎ የክህነት ሃላፊነቱን እንደተወጣ ከተመለከትን፣ ከዚህ ጋር የሚዛመደውን የምልጃ ካህናዊ ሃላፊነት እንዴት እንደተወጣ መመልከት ይገባናል፡፡

## ምልጃ

በዚህ ትምህርት ጅማሬ ላይ፣ ምልጃ መካከለኛነት ነው ወይንም በሌላ ሰው ምትክ ሆኖ ልመና ማቅረብ ነው ብለን ተነጋግረን ነበር፡፡ ይህም የኢየሱስን ምድራዊ አገልግሎት የሚገልፅ ሲሆን በሰማይም የሚዘልቅ አገልግሎት ነው፡፡

*አንድ ጓደኛዬ፣ "መልካም፣ ኢየሱስ አንዴ ወደ እግዚአብሔር ካቀረበን፣ ታዲያ አሁን ኢየሱስ ለምን ያስፈልገናል? እርሱ ወደ እግዚአብሔር አቅርቦናልና ለምን በቀጥታ ወደ አብ ብቻ አንጸልይም? ኢየሱስ ዳግመኛ አያስፈልገንም" ሲል ጠየቀኝ፡፡ ይህ ጥያቄ የኢየሱስን ቀጣይ ተግባር የሳተ ነው፡፡ ምክንያቱም አዲስ ኪዳን እንደሚናገረው፣ ኢየሱስ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለ መካከለኛ ነው፣ ይህም የአሁን ጊዜ አመልካች ነው፣ ሰው የሆነው ኢየሱስ፣ ስለ እኛ ሊያማልድ ዘላለምም የሚኖር ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ኢየሱስ በመስቀል ላይ ያከናወነው የስርየት ተግባር በአንድ በኩል ብቃት ይጎድለዋል ማለት አይደለም፡፡*

*በእርግጠኝነት፣ የኢየሱስ የማስተሰረይ ሥራ ለአንዴና ለዘላለም ነው፣ ፍፁምም ነው፤ ምንም ነገር አይጨመርበትም፡፡ አሁን ግን ኢየሱስ ጠበቃችን፣ አማላጃችን፣ እና ምትካችን በመሆን በሕይወታችን የሚያከናውነው ቀጣይና ግለሰባዊ የወዳጅነት ተግባር አለው፡፡ በየዕለቱም፣ በታላቁ ዳኛ ፊት በመቅረብ ስለጉዳያችን የሚሟገትልን ጠበቃችን ነው፡፡ ታላቁም የምሥራች ከማስተሰረይ ተግባሩ የተነሳ አንዳችም ጉዳይ አያመልጠውም፡፡ ዘወትርም እንከን የማይገኝበትንና የተጠናቀቀ ሥራውን በማሳየት በእኛ ምትክ በመሆን የታላቅ ሊቀ ካህንነት ተግባሩን ያከናውናል፣ ሥራውም ዘወትር ስኬታማ እና ውጤት የሚያመጣ ነው፡፡ ደግሞም ዘላቂ፣ ወዳጃዊና ብርቱ ነው፡፡ አንግዲያው ኢየሱስ በተጠናቀቀ የማስተሰረይ ሥራው ላይ በመመሥረት፣ መካከለኛችን፣ ማላጃችንና ታላቅ ሊቀካህናችን ሆኖ ይኖራል፡፡ [ዶ/ር ኬ. ኤሪክ ቶኔስ]*

በመጽሐፍ ቅዱስ ከተመዘገቡትና የኢየሱስን ማላጅነት በግልፅ ከሚያመለክቱ ምሳሌዎች መካከል በዮሐንስ ምዕራፍ 17 ውስጥ የተመዘገበውና በተያዘባትና ለመከራ አልፎ በተሰጠባት ሌሊት ለደቀመዛሙርቱ የጸለየው ጸሎት ነው፡፡ በመሠረቱ፣ ይህ ጸሎት “ሊቀ ካህናዊ ጸሎት” ተብሎ ይጠራል፡፡ በዚህ ጸሎት፣ ለሐዋርያቱ በርካታ ነገሮችን ለምኗል፡፡ በዮሐንስ ምዕራፍ 17 ቁጥር 20 እና 21 ውስጥ፣ በደቀመዛሙርቱ የወንጌል አገልግሎት የእርሱ ደቀመዛሙርት ስለሚሆኑትም የጸለየው ተቀምጧል፡፡

በመስቀል ላይ ሞቱም በሰውና በእግዚአብሔር መካከል እጅግ ውጤታማ በሆነ መንገድ ባከናወነው ተግባሩም ኢየሱስ የምልጃ ሥራውን ቀጥሏል፡፡ አሁንም ወደ ሰማይ አርጎ፣ በሰማያዊቷ መቅደስም የራሱን ደም በመሰዊያው ላይ በማቅረብ በአብም ፊት ስለኛ መማለዱን ቀጥሏል፡፡

በዕብራውያን ምዕራፍ 7 ቁጥር 24 እና 25 ውስጥ እንደምናነብበው፡

> እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው፤
> ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል። (ዕብ 7፥24-25)

ድነታችንም ለዘላለም የፀና ነው፣ ምክንያቱም ታላቁ ሊቀ ካህናችን ኢየሱስ፣ ዘወትር በአብ ፊት በእኛ ምትክ ሆኖ ስለሚማልድና፣ እኛ የሠራናቸውን በደሎች ሁሉ ስለ ልጁ ሞት ሲል ይቅር እንዲለን አብን ስለሚለምንልን ነው፡፡

ኢየሱስ የብሉይ ኪዳንን የክህነት አገልግሎት በፍፁምነት አሟልቷል፡፡ አመራርን ሰጥቷል፣ ሥርዓቶችን አስፈፅሟል እርሱም፣ በየትኛውም ዘመን ሁሉ እጅግ አስፈላጊ የሆነውን በመስቀል ላይ መስዋዕት መሆኑን ጨምሮ ለህዝቡ ሁሉ መማለድን ያካትታል፡፡ በመሠረቱ፣ ዛሬም ቢሆን እነዚህን መሠረታዊ ተግባራቱን በቤተክርስቲያኑ በኩልና በሰማያዊ ችሎት ፊት በሚያከናውነው ሊቀ ካህናዊ ሥራው አማካይነት ማከናወኑን ቀጥሏል፡፡ እንግዲያው፣ እንደ እርሱ ተከታዮች፣ ወደ አብ የምንገባበት ብቸኛው መንገድ ኢየሱስ መሆኑን እውቅና ልንሰጥና ልንደገፍበት ደግሞም ወደ እግዚአብሔር ልዩ ቅዱስ ኅላዌ ለማስገባት ለሚያከናውነው አገልግሎት ራሳችንን ልናስገዛ ይገባናል፡፡

ኢየሱስ እንደ ካህን መመዘኛዎቹን ማሟላቱንና ተግባራቱን በልቡናችን ይዘን፣ ብሉይ ኪዳን ከካህን አገልግሎት የሚጠብቀውን እንዴት እንዳሟላ እንመለከታለን፡፡

## ጥበቃዎች

ቀደም ብለን በዚህ ትምህርት እንደተመለከትነው፣ የካህናት አገልግሎት ታሪካዊ እድገት ወደፊት የሚመጣው የክህነት አገልግሎት፣ የእግዚአብሔርን ህዝብ ወደ እግዚአብሔር የተቀደሰ ኅላዌ ለማስጋበት በሚያስችል መጠን በእግዚአብሔርና በህዝቡ መካከለኛ የመሆንን አገልግሎት ማከናወኑን እንደሚገፋበት፣ ህዘቡም በዚያ ምክንያት ወደ እግዚአብሔር እንደሚቀርብ የሚጠበቅ መሆኑን አመልክቷል፡፡ ኢየሱስም የክህነትን አገልግሎት በመስጠት ይህንን ጥበቃ ማሟላቱን ተመልክተናል፡፡ ስለዚህ፣ በዚህኛው ትምህርታችን፣ ብሉይ ኪዳን ከወደፊቱ የክህነት አገልግሎት የሚጠብቃቸው ነገሮች የተገለጡባቸውን ለየት ያሉ ትንቢቶች በመመልከቱ ላይ ትኩረት እናደርጋለን፡፡

ውይይታችን በሦስት ክፍሎች የተከፈለ ነው፡፡ በመጀመሪያ፣ ስለ ታላቁ ሊቀ ካህን የተነገሩትን እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ ይህ ታላቅ ካህን እንደ ንጉሥ የሚያገለግል መሆኑን የሚናገሩ ትንቢቶችን እንዳስሳለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ የእግዚአብሔር ህዝብ የካህናት መንግሥት ስለመሆናቸው የሚናገረውን ትንቢት እንመለከታለን፡፡ አሁን ኢየሱስ ታላቅ ሊቀ ካህን የመሆኑን ትንቢት እንዴት እንደፈፀመው በመመልከት እንጀምር፡፡

## ታላቅ ሊቀ ካህን

ብሉይ ኪዳን ወደ ፊት በመሲሁ ዘመን የሚያገለግል አንድ ታላቅ ሊቀ ካህን እንደሚነሳና ራሱም መሲሁ እንደሚሆን በብዙ መንገዶች ለየት አድርጎ ይናገራል፡፡

እንደ መዝሙር 110 አገላለጥ፣ ይህ ታላቅ ካህን “እንደ መልከጼዴቅ ሹመት” እንደሚሆን ማለትም ከአሮን ዘር እንደማይሆን ይናገራል፡፡ አገልግሎቱም ለዘላለም እንደሚሆን፣ ማለትም ሞት ተግባሩን እንዳይፈፅም ሊያቆመው እንደማይችል ይናገራል፡፡ እንደ ዕብራውያን ፀሐፊ አገላለጥም፣ እነዚህ ሁሉ ትንቢቶች በኢየሱስ መፈፀማቸውን እናያለን፡፡

ዕብራውያን ምዕራፍ 7 ቁጥር 21 እና 22 ከመዝሙር 110 በመጥቀስ በዚህ መንገድ ያቀርበዋል፡፡

> እርሱ ግን፦ ጌታ። አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ ማለ አይጸጸትም ብሎ በተናገረለት ከመሐላ ጋር ካህን ሆኖአልና ያለ መሐላ ካህን እንዳልሆነ መጠን፥
> እንዲሁ ኢየሱስ ለሚሻል ኪዳን ዋስ ሆኖአል። (ዕብ 7፥21-22)

የዕብራውያን ፀሐፊ እንደሚናገረው መሲሁ ለዘላለም ካህን እንደሚሆን እግዚአብሔር ሲምል፣ ወደፊት የሚመጣው ታላቅ ሊቀ ካህን መሲሁ እንደሚሆንና በአዲሱም ኪዳን እንደሚያገለግል ነገሩ የተረጋገጠ መሆኑን ያስታውቀናል፡፡ በዚሁ በዕብራውያን በተመለከትነው ጥቅስም ውስጥ ታላቁ ሊቀ ካህን ኢየሱስ ነው፡፡

እንዲያውም፣ የዕብራውያን መጽሐፍ ኢየሱስን ትንቢት እንደ ተነገረለት ታላቅ ሊቀ ካህን 10 ጊዜ ጠቅሶታል፡፡ ኢየሱስንም አዘውትሮ “ክርስቶስ” ወይም “መሲህ” በማለት የሚጠቅሰው ሲሆን፣ በምዕራፍ 8፣ 9 እና 12 ውስጥም አዲሱን ኪዳን እንደሚያመጣም በግልፅ ያመለክታል፡፡ ከየትኞቹም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ይልቅ፣ የዕብራውያን መጽሐፍ ኢየሱስ ከታላቁ ሊቀ ካህን ብሉይ ኪዳን የሚጠብቃቸውን ሁሉ ማሟላቱን በማያጠራጥር ሁኔታ ይገልጥልናል፡፡

ብሉይ ኪዳን የሚጠብቀውና ኢየሱስም ያሟላው ሁለተኛው ነጥብ ታላቁ ሊቀ ካህን እንደ ንጉሥ የሚያገለግል መሆኑ ነው፡፡

## ካህን እንደ ንጉሥ

ከአዳም ዘመን አንስቶ እስከ አብርሃም ዘመን ድረስ፣ የክህነትና የንግሥና ቢሮዎች በአንድ ሰው ተጣምረው ይከናወኑ እንደነበር ተመልክተናል፡፡ ምንም እንኳን በእስራኤል የነገሥታት ዘመን ተለያይተው ቢከናወኑም፣ በመሲሁ ግን ተመልሰው እንደቀደመው በጣምራ እንደሚከናወኑ ብሉይ ኪዳን ይተነብያል፡፡ ይህም ነጥብ

በመዝሙር 110 ከቁጥር 2 እስከ 4 እና በዘካርያስ ምዕራፍ 6 ቁጥር 13 ውስጥ ተቀምጧል፡፡

በዚህና ቀደም ባሉትም ትምህርቶች እንዳየነው፣ ኢየሱስ እንደ መሲህ ሲመጣ፣ እርሱ የክህነቱንም የንጉሥነትንም ቢሮዎች በአንድነት አጣምሮ ነበር የመጣው፡፡ ይህም በማርቆስ ምዕራፍ 8 ቁጥር 29፤ በሉቃስ ምዕራፍ 23 ቁጥር 3 እና በዕብራውያን ምዕራፍ 8 ቁጥር 9 ውስጥ ተጠቅሷል፡፡

ኢየሱስ ከመምጣቱ አስቀድሞ፣ የአሮን ክህነት ከ1000 ዓመታት በላይ የእግዚአብሔርን ህዝብ ሲያገለግል ቆይቷል፡፡ አገልግሎታቸው ግን ከራሱ አሻግሮ ካህንም ንጉሥም ሆኖ የሚመጣውን መሲህ የሚያመለክት ነበር፡፡ እንዲያውም፣ እንደ ሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 6 ቁጥር 7 አገላለጥ በኢየሩሳሌምና በእስራኤል የሚገኙ በርካታ ካህናት ኢየሱስን እንደ መሲህ በመቀበል ተከታዮቹ መሆናቸውን እንረዳለን፡፡ ኢየሱስ የራሱ የሆነን የክህነት አገልግሎት እስካልመሰረተና የመቅደሱን የማያቋርጥ አሮናዊ የክህነት አገልግሎት እስካላረጋገጠ ድረስ፣ ከእስራኤላውያን ካህናት ያገኘው ድጋፍ መሲሁ ሲመጣ፣ የክህነትንና የንግሥናን ቢሮዎች አጣምሮ እንደሚመጣ ብሉይ ኪዳን የሚያስተምረውን ካህናቱ መረዳታቸውን ያመለክታል፡፡ እንዳየነውም ኢየሱስም ያደረገው ይህንኑ ነው፡፡

ሦስተኛውና የኢየሱስ ክህነት ያሟላዋል ተብሎ በብሉይ ኪዳን የሚጠበቀው ትንቢት ታላቁ ሊቀ ካህን የእግዚአብሔርን ህዝብ ወደ ካህናት መንግሥትነት የሚመራ መሆኑ ነው፡፡

## የካህናት መንግሥት

በዘፀአት ምዕራፍ 19 ቁጥር 6 እና ኢሳያስ ምዕራፍ 61 ቁጥር 6 እንደተመለከትነው፣ የእግዚአብሔር ህዝብ የካህናት መንግሥት የሚሆኑበት ጊዜ እንደሚመጣ ሁለቱም ተናግረዋል፡፡ እግዚአብሔር እንደሰጣቸውም መጠን በእግዚአብሔር የተቀደሰ ጎላዌ ውስጥ የምስጋናንና የመታዘዝን መስዋዕቶች ደግሞም ሌሎችን ክህነታዊ ተግባራት በማከናወን ያገለግሉታል፡፡ ጉልህ በሆነ መንገድም፣ በሉቃስ ምዕራፍ 4 ውስጥ በተመዘገበው የኢየሱስ ስብከት፣ ኢየሱስ ከኢሳያስ 61 በመጥቀስ ያንንም እርሱ እንደሚፈፅመው ተናግሯል፡፡ በዚህ መንገድ፣ ኢየሱስ ራሱ የእግዚአብሔርን ህዝብ ወደ ካህናት መንግሥትነት እንደሚለውጥ ተናግሯል፡፡ ሌሎችንም የብሉይ ኪዳን ምንባባት ስንመለከት ኢየሱስ የፈፀመው ይህንኑ ነው፡፡

ለምሳሌ፣ በ1ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 5 ውስጥ፣ ጴጥሮስ ቤተክርስቲያንን “ቅዱሳን ካህናት” ብሎ ጠቅሷታል፡፡ በቁጥር 9 ደግሞ “የንጉሥ ካህናት” ብሏታል፡፡ በራዕይ ምዕራፍ 1 ቁጥር 6፤ ምዕራፍ 5 ቁጥር 10 እና ምዕራፍ 20 ቁጥር 6 ውስጥም ተመሳሳይ ሃሳብ እናገኛለን፡፡

አንዱን ለምሳሌ ለመጥቀስ፣ በራዕይ ምዕራፍ 1 ቁጥር 6 ስለ ኢየሱስ የተነገረውን ቃል እስኪ አድምጡ፡

> መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ፥ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን፤ አሜን። (ራዕይ 1፥6)

እንደ መሲህ፣ ኢየሱስ እንደ ንጉሥ የሚገዛ ሊቀ ካህን ሲሆን፣ ተከታዮቹም በመንግሥቱ ውስጥ ካህናት ሆነው እንዲያገለግሉ ሾሚቸዋል፡፡

> *ከብሉይ ኪዳን ከምንገነዘባቸው ትልልቅ ነገሮች አንዱ ካህናት ቁልፍ ሰዎች መሆናቸውን ነው፡፡ በአዲስ ኪዳን ደግሞ የተወሰኑ የካህናት ስብስቦች ብቻ ሳይሆኑ፣ ሁሉም አማኞች ካህናት ናቸው፡፡ ይህም እውነት በተደጋጋሚ ጊዜ፣ የአማኞች ክህነት ተብሎ በሚጠቀሰው ሐረግ ውስጥ ተቀምጧል፡፡ ሁሉም ክርስቲያኖች የተጠሩትና ኃይልን የተቀበሉት፣ የኢየሱስና የክርስቶስ አካል እጆች፣ ልቦችና እግሮች እንዲሆኑ መሆኑ ሊሰመርበት እንደሚገባ ነጥቡ ያመለክታል፡፡ ይህም አስደናቂ በሆነ መንገድ የሚያበረታታ እውነት ነው፡፡ በታሪክ ውስጥ ከተከናወኑት ድራማዊ ክስተቶች መካከል አንዱ በሰው ልጅና በእግዚአብሔር መካከል ከዚህ በኋላ መካከለኛ የሚሆን ሰው የማያስፈልግ የመሆኑን እውነት አጥብቆ መያዝ ነው፡፡ በእናንተና በእግዚአብሔር መካከል የሚገባ ሰው የመሻቱ አዝማሚያ አግባብነት የሌለውና ወደ ማኅበራዊ እስራት ውስጥ የሚያስገባ ንቀት የተላበሰ ድርጊት ነው፡፡ አዎን ይህ አስደናቂና የሚያበረታታ እውነት ነው ሆኖም ግን፣ ይኸው እውነት እግዚአብሔር በአካሏ ውስጥ እንዲገለጡ የሰጣቸውን የጸጋ ስጦታዎች የማቅለልና ማንም እንዲያገለግለኝ አልሻም የሚል አዝማሚያ እንዲፈጠር የሚፈታተን ይመስላል፡፡ ነገር ግን ልብ የምንለው ነገር ሌሎች እንዲያገለግሉኝ ከምፈቅድባቸውና ላደንቃቸው ከሚገቡኝ አንዱ የእረኝነት አገልግሎት ነው፡፡ የእረኝነት አገልግሎት ለየት ያለ ልብ ይጠይቃል፡፡ የእረኛ ልብና ክህሎትንም ይጠይቃል፡፡ አቅጣጫ ለማሳየት፣ ለማበረታታትና ለማፅናናት የሚሆን ማለት ነው፡፡ ይህ ግን በየትኛውም ሰውና በእግዚአብሔር መካከል መግባት ማለት አይደለም፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል በራሳቸው ፈትተው ለመረዳትና ሊያከናውኑ የተገባቸውን መልካም ሥራ ለመሥራት እንዳይችሉ*

*የሚያዳክም ሊሆን አይገባውም፡፡ በዚህ ጎዳና ላይ ይረዳን ዘንድ፣ እንደ ካህናትም እንኖር ዘንድ ጸጋ ተሰጥቶናል፣ ሆኖም እነዚህ ካህናት የእረኝነትን አገልግሎት የሚሰጡና የሚቀበሉ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ [ዶ/ር ግሌን ስኮርጂ]*

ኢየሱስ የክህነትን አገልግሎት የማሟላቱ ነገር አንድ በጣም አስፈላጊ ነገርን ያሳስበናል፡፡ እግዚአብሔር በፍጥረት ላይ ያቀደው ዕቅድ በኃጢአት ምክንያት ተወሳስቧል፣ ሆኖም በኃጢአት ተውጦ የሚቀር ግን አይደለም፡፡ የኢየሱስ መገለጥና ከካህናት የሚጠበቀውን ሁሉ የማሟላቱ ነገር የእግዚአብሔርን ዕቅድ መልካምነት ለማሳየት ያለውን ታማኝነት የሚያሳይ ነው፡፡ አገልግሎቱንና ላዕላይ ፍቺውን ማጠናከሩ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ከማስፈፀም አንፃር ማዕከላዊ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ንጉሥ ሆኖ እንደሚገዛ ታላቅ ሊቀ ካህን፣ የካህናትን አገልግሎት ተቀዳሚና የሚጠበቁ ገፅታዎች ኢየሱስ አሟልቷል፡፡ ስለዚህም እኛ እንደ እርሱ ህዝቦች፣ ኢየሱስን ልናከብረው ልናመልከው፣ ልንታመነውና እንደ መንግሥቱም ካህናት ልናገለግለው የሚገባን ስለ መሆኑ ከበቂ በላይ ምክንያቶች አሉን፡፡

እስካሁን ድረስ፣ የክህነትን አገልግሎት ብሉይ ኪዳናዊ ዳራ እና በኢየሱስ ያገኙትን ፍፃሜ ተመልክተናል፡፡ እንግዲያው፣ በዚህ ነጥብ ላይ፣ የኢየሱስን ክህነት ዘመናዊ ተዛምዶ እንመለከታለን፡፡ የኢየሱስ ታላቅ ሊቀ ካህንነት ዛሬ ለምንኖረው ኑሮ ምን እንድምታ አለው?

## 4. ዘመናዊ ተዛምዶ

የክርስቶስን ክህነታዊ ሥራ በዘመናችን ለማዛመድ የሚጠቅመን ዐይነተኛ መንገድ በዌስት ሚኒስትሩ አጭር ካቴኪዝም መልስ ቁጥር 25 ውስጥ ይገኛል፣ እንዲህም ይነበባል፡

*መለኮታዊውን ፍትህ ያሟላ ዘንድ ያቀረበው ብቸኛ መስዋዕትነቱ፣ ክርስቶስ የክህነትን አገልግሎት መፈፀሙን፣ እኛን ከእግዚአብሔር ጋር ማስታረቁንና ስለ እኛም የማያቋርጥ ምልጃን እንዲያደርግ አስችሎታል፡፡*

በዚህ መልስ ውስጥ፣ ካቴኪዝሙ የክርስቶስን የክህነት አገልግሎት ለአማኞች ከሚሰጠው አገልግሎት አንፃር አጠቃሎ አቅርቦታል፡፡ ቢያንስ ሦስት የሥራውን ገፅታዎችም ጠቅሷል፡፡ አንደኛ፣ ስለ ክርስቶስ ራስን መስዋዕት የማድረግ አገልግሎት ይናገራል፡፡ ሁለተኛ፣ አንዴና ለዘላለም ያቀረበው መስዋዕታዊ አገልግሎት በአማኞችና በእግዚአብሔር መካከል እርቅን አስገኝቷል፡፡ ሦስተኛ፣ በእግዚአብሔርና በአማኞች መካከል የማይቋረጠውን ምልጃውን ይዘረዝራል፡፡

የኢየሱስን የክህነት አገልግሎት ዘመናዊ ተዛምዶ የምንመለከተው የዌስት ሚኒስትሩ አጭር ካቴኪዝም ያስቀመጠውን በመከተል ነው፡፡ በመጀመሪያ፣ የክርስቶስን መስዋዕትነት እናያለን፡፡ ሁለተኛ፣ በማስታረቁ ሥራው ላይ እናተኩራለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ የክርስቶስ ምልጃ ያለውን ተዛምዶ እናያለን፡፡ አስቀድመን መስዋዕትነቱን እንመልከት፡፡

## መስዋዕት

የክርስቶስን መስዋዕትነት እኛ ልንሰጠው ስለሚገባ ምላሽ በሚናገሩ ሦስተ ነገሮች ዙሪያ ማለትም፡ ለድነት በእርሱ መታመን፤ ለእርሱና እርሱ ለሚወዳቸው የታመነ አገልግሎት ማቅረብ እና ማምለክ ናቸው፡፡ አስቀድመን የመታመኑን ነገር እንይ፡፡

### *መታመን*

ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያስተምሩን ኢየሱስ በመስቀል ላይ የከፈለው መስዋዕትነት ከእግዚአብሔር ለምንቀበለው የድነት ስጦታ ብቸኛና ውጤታማ መሠረት ነው፡፡ በዚህ ትምህርት ቀደም ብለን የተመለከትነውን ቃል ለመጠቀም ያህል፣ በእርሱ ያመኑትን ሁሉ ኩነኔ ጨርሶ ለማስወገድ፣ ለመደምሰስ የእግዚአብሔርን ቁጣ ለማብረድና ፍትሁን ለማርካት እግዚአብሔርን ይማፀናል፡፡

ይህን ለመቀበል ግን እምነት ወሳኝ ነው፡፡ ክርስቶስ ያስገኘውን የኃጢአት ስርየት ለመቀበል፣ በእርሱና በእርሱ ብቻ ልንታመን ይገባናል፡፡ ስለ እኛ ኃጢአት የሞተ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን፣ ይቅርም የምንባለው ስለ እኛ ባቀረበው መስዋዕትነት ምክንያት ብቻ መሆኑን ልናምን ይገባናል፡፡ ስለዚህም መታመን እንደ ዮሐንስ ምዕራፍ 20 ቁጥር 31፤ ሮሜ ምዕራፍ 10 ቁጥር 9 እና 10 እና 1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 4 ከቁጥር 14 እስከ 16 ባሉት ክፍሎች እናነባለን፡፡

መዳናችን የተመሠረተው በኢየሱስ መስዋዕትነት ብቻ መሆኑን፣ ያም ውጤታማ የሆነው በእርሱ ሥራ ብቻ መሆኑን የክርስቶስ አማኞች ሊታመኑበት ይገባል፡፡ ማንም ሊያድነን አይችልም፡፡

ጴጥሮስ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 4 ቁጥር 12 እንደሰበከው፡

> *መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።* (ሐሥ 4፥12)

ድነትን በራሳችን ልናገኘው አንችልም፡፡ የትኛዋም ቤተክርስቲያን ወይንም ቅዱስ ሰውም ሊያስገኙልን አይችሉም፡፡ ስለዚህ ክርስቶስ እኛን ለማዳን በሠራው ሥራና በመስዋዕትነቱ ላይ ብቻ ልንታመን ይገባናል፡፡

እምነታችንን በኢየሱስ ላይ ብቻ ስናደርግ፣ በእግዚአብሔር ፊት ድፍረትና ደስታ ይኖረናል፡፡ አብ ያዘዘውን ሁሉ ኢየሱስ በታማኝነት ፈፅሟል፡፡ ስለዚህም አደርግላችኋለሁ ብሎ የገባውን ተስፋ ሁሉ እንደሚፈፅምልንም እርግጠኞች እንሆናለን፡፡

በዕብራውያን ምዕራፍ 10 ከቁጥር 19 እስከ 22 እንዲህ እናነባለን፡

> እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት
> በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት ስላለን፥
> በእግዚአብሔርም ቤት ላይ የሆነ ታላቅ ካህን ስላለን፥
> ከክፉ ሕሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን ሰውነታችንንም በጥሩ ውኃ ታጥበን
> በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ፤

በዚህ ስፍራ መተማመን ተብሎ የተጠቀሰው ቃል መታመን ሊባልም ይችላል፡፡ ያም የኢየሱስ መስዋዕትነት ኃጢአታችንን ለማስተሰረይ በቂ መሆኑንና እርሱ ሊያድነን የማይችለበት ምንም ነገር እንደሌለ ፅኑ የእምነት አቋም የምንይዝበት ነው፡፡

> *መዳናችንን ከምናረጋግጥባቸው ምልክቶች አንዱ በውስጣችን ያለው የመዳን ስሜት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል የመሆን ስሜት ይሰማናል፡፡ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን መንፈስ ቅዱስ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክርልናል፡፡ እናም ስለዚህ፣ እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች ይህ የልጅነት መንፈስ አላቸው፡፡ ይህ ማለት ግን ስለ መዳናችን ከሚሰማን እርግጠኝነት እና ዋስትና አንፃር ከፍ ዝቅ የሚል ነገር አይገጥመንም ማለት አይደለም፡፡ በዚህ ዋስትና አንፃር ልናድግ ያስፈልገናል፣ በእርግጠኝነትም ሄደት መጣ እንደሚል እናውቃለን፡፡ ወንጌልን በየዕለቱ ለመረዳት፣ በየዕለቱም ለራሳችን ልንሰብከውና ከዚያም የተነሳ ኢየሱስ የእኛን ስፍራ ሲወስድ ሥራችንን እንደሠራልን እና እኛም እርስ በርስ ልንደጋገፍ እንደሚገባን ልንሻ ይገባናል፡፡ በኅብረት ውስጥ የምናከናውነው ይህንን ሲሆን፣ ስለ ልጅነታችን፣ ስለ ድነታችን እና ይቅር ስለ መባላችን ይበልጥ እርግጠኛ እናሆናለን፡፡ መንፈስ ቅዱስም በቃሉ ስብከት አማካይነት በክርስቶስና እርሱ ለእኛ በሠራው ሥራ ባለን መተማመን እያደግን የምንሄድበትን ብቃት ያጎናፅፈናል፡፡ ስለዚህ፣ አማኞች የሚሰማቸው የድነት*

*እርግጠኝነት በየዕለቱ ሄደት መጣ የሚል ሲሆን፣ ሆኖም ግን ጥቅል የሆነና ቀጣይ የሆነ ዕድገት በጊዜ ርዝመት ይገለጣል፡፡ [ዶ/ር ኬ. ኤሪክ ቶኔስ]*

*እውነተኛ አማኞች መዳናቸውን ይጠራጠራሉን? በእርግጥ፡፡ የዚህ ምሳሌ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እናያለን፡፡ ይህንንም ኤልያስ በክትክታ ዛፍ ስር በተቀመጠበት ወቅት፣ ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር ስላለው ግንኙነት በርካታ ሰቆቃዎችን ባሰማበትና ጥያቄዎችን በጠየቀበት መዝሙር ውስጥ እንመለከታለን፡፡ ጴጥሮስ ክህደትን ከፈፀመ በኋላ ወዲያውኑ ወጥቶ ባለቀሰበት የጴጥሮስ ታሪክ ውስጥም የምናየው ይመስለኛል፡፡ አዎን እውነተኛ አማኞችም ድነታቸውን ይጠራጠራሉ፡፡ ታውቃላችሁ፣ የእኛ መዳን ግን ባለን እርግጠኝነት መጠን ላይ የሚመሠረት አይደለም፡፡ አንዳንድ ጊዜ በአብያተ ክርስቲያናቱ ክልል ውስጥ፣ ወደዚያ የሚጋደል አዝማሚያ አለ፡፡ ሰዎች ምስክርነታቸውን እንዲያቀርቡ እንጠይቃለን፡ እኔም የጳውሎስን ለውጥ የሚመስል ድንገተኛና ድራማዊ ለውጥ አይቻለሁ፡፡ ግድ ካላችሁኝ አንድ ሰዓትና ደቂቃዎችን ጨምሮ ልመሰክር እችላለሁ፡፡ ኢየሱስ መኖሩ ወይንም አለመኖሩ ለእኔ ምንም ደንታ የማያሰጠኝ ቀን ነበር፣ ግን በ24 ሰዓት ውስጥ፣ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅና አዳኜ መሆኑን አመንሁ፡፡ የዳንኩት ግን ክርስቶስ ብቻውን በሠራው የተጠናቀቀ ሥራና ድል ብቻ መሆኑን በማመኔ በፀጋ ብቻ ነው እንጂ ባለኝ እርግጠኝነት መጠን አይደለም፡፡ እርግጠኝነታችሁን የሚሠርቁ በርካታ ነገሮች አሉ፡፡ ለምሳሌ በምድር ላይ እጅግ የምትወድዷቸውን ወንዶች ወይንም ሴቶች ጌታ ሲወስዳቸው፣ ጨለማ ሲከብባችሁ፣ ያ ያናውጣችኋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አካላዊና አዕምሯዊ ምክንያቶችም ይኖራሉ፡፡ገሚስ ነገር ብቻ ማየት የሚቀናቸው አንዳንድ ሰዎች አሉ፡፡ እነዚያም ሰዎች የጥያቄ ማኀደሮች ናቸው፡፡ ሁላችንም ዓለምን በጨለምተኝነት ስለሚያዩ ሰዎች እናውቃለን እኔም በዚያ መንገድ ጥያቄዎችን የመጠየቅ ተፈጥሮ አለኝ፡፡ አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ምክንያቶች ይኖራሉ፣ እነዚያም መለኮታዊ ምክንያቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ በ17ኛው ክፍለ ዘመን የነበረው የዌስት ሚኒስቴሩ የእምነት መግለጫ እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ እርሱን የበለጠ እንፈልገው ዘንድ የፊቱን ብርሃን ይሰውርብናል፣ ያንንም የሚያደርገው እርሱን ማጣታችን እንዲያሳድገንና በስተመጨረሻውም እምነታችንን እንዲያረጋግጥልን ነው፡፡ ያ ግን በሕይወታችን እጅግ ደስ የማያሰኝ ልምምድ ነው፡፡ ወላጆች ግን አንዳንድ ጊዜ ተመሳሳይ ነገር ያደርጋሉ፡፡ ገና መራመድ ከጀመረ ልጃቸው ላይ እጃቸውን ያርቃሉ፡፡ ድንገት ቢወድቁ ለማንሳት በአጠገባቸው አሉ፣ ለሰከንድ ግን ብቻቸውን ይቆማሉ፡፡ ያንንም የሚመስል ነገር*

*እግዚአብሔርም በእኛ ላይ ያደርጋል፣ ማለትም እርሱን እንድንናፍቅ እና በውጤቱም እንድናድግ ያደርጋል ማለት ነው፡፡ [ዶ/ር ኤሪክ ቶኔስ]*

ክርስቶስ ለከፈለው መስዋዕትነት መታመንን ምላሻችን ማድረግን በተመለከተ ተነጋግረናል፣ አሁን ደግሞ የእርሱ መስዋዕትነት እንድናገለግል እንደሚያነሳሳን እንመለከታለን፡፡

## አገልግሎት

ኢየሱስ ስለ እኛ የከፈለው መስዋዕትነት እርሱን በታማኝነት እንድናገለግለው ሊያነቃቃን ይገባል፡፡ በሮሜ ምዕራፍ 6 ውስጥ፣ ኢየሱስ እኛን ለማዳን በመሞቱ ምክንያት እኛም ልንወደውና ልንታዘዘው ግዴታ ያለብን መሆኑን ጳውሎስ በግልጽ አስቀምጦታል፡፡ አዲስ ሕይወት ሊሰጠን ሞተልን፡፡ ይህም ሕይወት ከኃጢአት ባርነት ነፃ የወጣ ነው፡፡ ስለዚህ መዳን ምሥጋናችንን ልናቀርብባቸው ከሚገቡን መንገዶች አንዱ በሕይወታችን ከሚመላለስ ኃጢአት ጋር መጋደል፣ ዳግመኛም ራሳችንን ለእርሱ ላናስገዛ መቃወም ነው፡፡

ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ 6 ከቁጥር 2 እስከ 4 እንዲህ ጽፏል፡

> ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን?
> ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን?
> እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን።

ኢየሱስ ስለ እኛ ሞቷል ስለዚህ እኛም ከኃጢአት ባርነት ልንላቀቅ ይገባናል፡፡ ለዚህ መስዋዕትነት ተገቢ የሆነው ምላሽ እርሱን ደስ በሚያሰኝ መንገድ መኖር ነው፡፡

ቅዱሳት መጻሕፍት በተጨማሪም ክርስቶስን ከመስዋዕትነቱ አንፃር ልናገለግልባቸው የምንችልባቸውን በርካታ መንገዶች ይጠቅሱልናል፡፡ የእርሱ ዓላማ ይፈፀም ዘንድ በመከራ ውስጥ ለማለፍና ለመሞትም ጭምር የክርስቶስን ምሳሌነት ልንከተል እንደሚገባ ግልፅ ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነም፣ ሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 5 ቁጥር 41 እና ፊልጵስዩስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 29 እንደሚያመለክቱት፣ ስለ ክርስቶስ መከራን መቀበል ትልቅ ክብርና መታደል ነው፡፡

በተጨማሪም ኢየሱስ ሊያድናቸው ለሞተላቸው ሰዎች እኛም መስዋዕት በመሆን ክርስቶስን እንድናገለግል መጽሐፍ ቅዱስ ያበረታታናል፡፡ በኤፌሶን ምዕራፍ 4 ከቁጥር 32 እስከ ምዕራፍ 5 ቁጥር 2 ውስጥም እርስ በርሳችን ርኅሩኅዎችና ታጋሾች እንድንሆንም ያስተምረናል፡፡ በሮሜ ምዕራፍ 14 እና በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 8 ውስጥ ደግሞ በእምነታቸው ስለ ደከሙት ስንል ነፃነታችን አሳልፈን ልንሰጥ እንደሚገባን ያመለክታል፡፡ እንዲያውም ስለሌሎች አማኞች ስንል ክርስቶስ እንዳደረገው ሕይወታችንን አሳልፈን እንድንሰጥም ያዝዘናል፡፡

ዮሐንስ በ1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 16 ውስጥ እንደፃፈው፡

> እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና በዚህ ፍቅርን አውቀናል፤ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል። (1ዮሐ 3፥16)

ኢየሱስ በመስቀል ላይ ስለ ኃጢአት ስርየት የከፈለው የአንዴና የዘላለም መስዋዕት ዓላማውን ለማስፈፀም፣ ለመጥቀስም፣ ስለ ኃጢአት የእግዚአብሔርን ፍርድ በራሱ ላይ መሸከሙ በራሱ ፍፁም ብቁ ነው፡፡ እንኳን የሌሎችን ሰዎች ቀርቶ፣ የራሳችንን እንኳን ልናስተሰርይ አንችልም፡፡ ነገር ግን ስለሌሎች ሕይወታችንን አሳልፈን በመስጠት የኢየሱስን ምሳሌነት ልንከተል እንችላለን፡፡

ስለ እነርሱ ለመሞት ከፈቀድንም፣ ከዚያ ያነሰ መስዋእትን ለእነርሱ ለመክፈልም ፈቃደኞች እንሆናለን፣ ማለትም፣ ከጊዜያችን፣ ከገንዘባችን፣ ከምቾቶቻችን እና ከጥሪቶቻችን ሁሉ በመክፈል እነርሱን ለማገልገል እንፈቅዳለን፡፡

ሌሎችን መውደድና ስለ እነርሱም መስዋዕትነት መክፈል ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ መናገር ቀላል ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ግን አባባሉን በተግባር ማዋል ከባድ ነው፡፡ ሰዎችን በአግባቡ ለመውደድ፣ ለእኛ የከበሩ የምንላቸውን ማለትም፣ ጊዜ፣ ገንዘብ እና ምቾቶቻችንን መሰዋት ይጠይቀናል፡፡ ሌሎችን ለመውደድ ልንሰዋቸው ከሚገቡ ጥቂቶቹ እነዚህ ናቸው፡፡ ከእኛ ምቾቶች ይልቅ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን መፈለግ እጅግ ከባድ ነው፡፡ ይህን ማድረግ ሲሳነን ግን፣ ከምንሰዋው ይልቅ የምናገኘውን የበለጠ ነገር እናጣዋለን፡፡ ስለሌሎች ስንል ሕይወታችንን ስንሰጥ በዚህ ዓለም ላይ የእግዚአብሔር ግዛት ሲሰፋ በማየት እግዚአብሔርን የምናመልከበትን ዕድል እናገኛለን፡፡

መታመንና አገልግሎት የክርስቶስ መስዋዕትነት ሁለቱ ዘመናዊ ተዛምዶዎች መሆናቸውን ተመልክተናል፣ አሁን ደግሞ ትኩረታችንን በአምልኮ ላይ እናድርግ፡፡

## አምልኮ

እንደ ክርስቲያኖች፣ በመስቀል ላይ ስለ እኛ መሞቱን ስናስብ ኢየሱስን ለማምለክ ውስጣችን ሲነሳሳ እናገኘዋለን፡፡ ከራስ ወዳድነት የነፃው መስዋዕትነቱ ለእኛ ስላሳየው ድንቅ ፍቅር እንድናመሰግነው ልባችንን ያነቃቃዋል፡፡ ለእኛም ስላስገኘልን ድንቅ መዳን ደግመን ደጋግመን እንድናመሰግነው ይገፋፋናል፡፡

የኢየሱስ መስዋዕትነት በተጨማሪም አብንና መንፈስ ቅዱስንም እንድናመልከ ሊያበረታታን ይገባል፡፡ በመሠረቱም፣ እንደ ዮሐንስ ምዕራፍ 14 ቁጥር 31 አገላለጥ፣ የኢየሱስ መስዋዕትነት የአብ ዕቅድ ነው፡፡ ዕብራውያን ምዕራፍ 9 ቁጥር 14 እንደሚያስተምረን ደግሞ፣ ኢየሱስ መስዋዕቱን ያቀረበው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው፡፡ ስለዚህ፣ አብና መንፈስ ቅዱስ ለኢየሱስ የምናቀርበውን ተመሳሳይ ምሥጋናና አምልኮ ሊቀበሉ ይገባቸዋል፡፡

የኢየሱስ መስዋዕትነት እንድናመልከው ከማነሳሳቱ ባሻገር፣ የአምልኮ ናሙና ሆኖም ያገለግለናል፡፡

እስኪ ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ 12 ቁጥር 1 የጻፈውን አድምጡ፡

> *እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው።* (ሮሜ 12፥1)

ይህ ምንባብ ሁለት ጥያቄዎችን ያስነሳል፡፡ በመጀመሪያ፣ የኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞት እንዴት የአምልኮ መግለጫ ይሆናል? ሁለተኛ፣ የእኛንስ አምልኮ የዚያን ፈለግ እንዲከተል እንዴት እናደርጋለን?

ለመጀመሪያው ጥያቄ መልስ ለመስጠት፣ የኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞት የአምልኮ መግለጫ የሚሆንበት ምክንያት የብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች በጥላነት የሚያመለክቱትን ስላሟላ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን፣ የእግዚአብሔር አምልኮ መስዋዕቶችን ማእከል ያደረገ ነው፡፡ ዕብራውያን ምዕራፍ 9 እንደሚያስተምረንም የኢየሱስ መስዋዕት የብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች ሁሉ ያመለክቱት የነበረው ጭብጥ ነው፡፡ በተጨማሪም ኢየሱስ በሌሎች ተገድዶ ሳይሆን ወድዶና ፈቅዶ ራሱን እንደሰጠ ይናገራል፡፡ የአሮጌውን ኪዳን የአምልኮ ህግጋት የሚከተልና የመስዋዕታዊ አምልኮ መገለጫ የሆነውን ራሱን ለእግዚአብሔር በማቅረብ የሚያገለግል ሊቀ ካህን

ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት፣ የእኛ መስዋዕታዊ ተግባራት አምልኮን ያካተቱ ሊሆን ይገባል፡፡

ታዲያ የእኛ አምልኮ የኢየሱስን መስዋዕትነት እንዲከተል የምናደርገው እንዴት ነው? የምናቀርበውስ ምን ዓይነት መስዋዕት ነው? እግዚአብሔር እንደ አምልኮ የሚቀበላቸውና ልናቀርባቸው የሚገቡ በርካታ ነገሮች እንዳሉ ቅዱሳት መጻሕፍት ያመለክቱናል፡፡ እንደተመለከትነው፣ ሮሜ ምዕራፍ 12 ቁጥር 1 እንደሚናገረው የኢየሱስን መስዋዕትነት የምንከተልበት አንድ መንገድ ሰውነታችንን ለእግዚአብሔር መስዋዕት በማድረግ ነው፡፡ ቁጥር 2 ደግሞ ትርጉሙን ይሰጠናል፡፡ ያም፡ ራሳችንን ከዚህ ዓለም ባህርይ ጋር ልናመሳስል አይገባም፤ ይልቁኑ፣ በክርስቶስ የታደሰው አዕምሯችን ወደ አዲሱ ባህርይ እንዲመራን ልንፈቅድለት ይገባል፡፡ ሰውነታችንንም የኃጢአት መሣሪያ ከማድረግ ልናቅበውና እግዚአብሔርንም በሚያከብር መንገድ ልናስለምደው ይገባል፡፡

ኤፌሶን ምዕራፍ 5 ቁጥር 1 እና 2 እንደሚያስተምረንም የክርስቶስን መስዋዕትነት የምንከተልበት ሁለተኛ መንገድ የፍቅርን ሕይወት መኖር ነው፡፡ የኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞት ከፍተኛው የፍቅር ተግባር ነው፡፡ ስለዚህ፣ አንዳችን ለሌላችን ርኅሩኆችና ገሮች ስንሆን፣ ሕይወታችንን ከክርስቶስ የፍቅር መስዋዕትነት ጋር እንዲመሳሰል ማድረጋችን ነው፡፡

ፊልጵስዩስ ምዕራፍ 4 ቁጥር 18 እንደሚናገረው በመስዋዕት እግዚአብሔርን የምናመልክበት ሦስተኛ መንገድ፤ ለሌሎች አማኞች ከገንዘባችን፣ ከጥሪቶቻችንና ከጊዜያችን ማካፈል ነው፡፡ የፊልጵስዩስ ሰዎች የላኩለት ስጦታ ለእግዚአብሔር የቀረቡ መባና መስዋዕቶች ናቸው፣ ምክንያቱም ለፊልጵስዩስ ሰዎች እጅግ ውድ የሆኑ ደግሞም እግዚአብሔር የሚወዳቸውና የሚጠቅሙ ነበሩና፡፡

በእርግጥ እነዚህ የጠቀስናቸው፣ እግዚአብሔርን በመስዋዕትነት የምናመልክባቸውን አማራጮች ሁሉ ያካተቱ አይደሉም፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔርን ከፍቅር በመነጨ መስዋዕት ከማምለክ አንፃር የክርስቶስን ዱካ ለመከተል በምናደርገው ሂደት መነሻ ይሆኑልናል፡፡

ከኢየሱስ መስዋዕትነት የምንወስዳቸውን ተግባራዊ ተዛምዶዎች ተመልክተናል፣ አሁን ደግሞ የእርሱ ካህናዊ የማስታረቅ አገልግሎት ሕይወታችንን እንዴት ተፅዕኖ እንደሚያሳድርበት ለመመልከት እንዘጋጃለን፡፡

## ማስታረቅ

የኢየሱስን ክህነታዊ የማስታረቅ አገልግሎት ዘመናዊ ተዛምዶ በሦስት መንገዶች እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምን እንደሚያመጣልን እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ የሚያስገኘውን አንድነት እንመለከታለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ለእኛ የሰጠንን ተልዕኮ እንመለከታለን፡፡ አስቀድመንም ከእግዚአብሔር ጋር ያገኘነውን ሰላም እንመልከት፡፡

## ሰላም

ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር ሲያስታርቀን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም እንዲኖረን አደረገ፡፡ ሮሜ ምዕራፍ 5 ቁጥር 10 እና ኤፌሶን ምዕራፍ 2 ቁጥር 2 የመሳሰሉትን ስናብብ፣ ከዚህ እርቅ በፊት፣ አመፃችን የእግዚአብሔር ጠላቶች አድርጎናል፡፡ በዚያን ወቅት፣ የእግዚአብሔርን ቁጣና ፍርድ ልንቀበል ይገባን ነበር፡፡ ሆኖም ኢየሱስ እኛን ከእግዚአብሔር ጋር በማስታረቁ፣ ይህ ጠላትነት እንዲያበቃ አደረገ፡፡ የእግዚአብሔርን ቁጣ በማብረድ፣ በመካከላችን እርቅ እንዲሆን አደረገ፡፡

አሁን፣ የእግዚአብሔር ጠላቶች መሆናችን ቀረና፣ የሚወዳቸው ልጆቹ እና የመንግሥቱ ታማኝ ዜጎች ሆንን፡፡ ይህም ማለት ጠላቶቻችንን በምንፈራበት መንገድ እግዚአብሔርን ልንፈራ አያስፈልግም፡፡ እኛን ሊያጠፋን እንደሚፈልግ ልናስብም አይገባም፡፡ ሕይወታችንም በክርስቶስ ተሰውሯል፣ ስለዚህም በእግዚአብሔር አብና በእግዚአብሔር ወልድ መካከል ያለው ሰላም በእኛና በእግዚአብሔር መካከል እንዲኖር ሆኗል፡፡ ይህንን የሚመስለውም ሰላም ልባችንን ለምስጋና፣ እጃችንን ለተግባር እና አዕምሯችንም ታላቁን አምላካችንን ይበልጥ እንድናውቀው የሚያነሳሳን ይሆናል፡፡

ጳውሎስ በቆላስይስ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 19 እስከ 22 ስለዚህ ነገር የተናገረበትን መንገድ አድምጡ፡

> እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር፥ በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአልና።
> እናንተንም ነውርና ነቀፋ የሌላችሁና ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ያቀርባችሁ ዘንድ፥ በፊት የተለያችሁትን ከፉ ሥራችሁንም በማድረግ በአሳባችሁ ጠላቶች የነበራችሁትን አሁን በሥጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ። (ቆላስ 1፥ 19-22)

*“ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለን” የሚለው ሃሳብ የልጆቹ የአማኞች ሥነ-ስርዓት የሚሆነው እንዴት ነው? የሚለውን ጥያቄ ማስነሳቱ በጣም በጣም ግልፅ ነው፡፡ እንደማስበው ቀላሉ መልስ ሰለሚወደን ነው የሚል ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለን ማለት ከእርሱ ጋር ወደነበረን ግንኙነት ተመልሰናል ማለት ነው፡፡ የተፈጠርነው፣ እግዚአብሔርን ለማወቅ፣ እንድናገለግለው፣ እንድንወድደው፣ እንድንታዘዘው እና እጅግ ቅርብ በሆነ መንገድ እንድናውቀውም ነው፡፡ ኃጢአት ግን ከዚያ እንድንወገድ አደረገን፡፡ መዳናችን ግን ሰላምን፣ ዕርቅንና ድነት ምን ማለት እንደሆነ የሚያመለክቱንን ምስሎች ሁሉ ወደ እኛ መልሶ አመጣልን፡፡ ስለዚህም አሁን እኛ ከእርሱ ጋር የቅርብ ዝምድና አለን፡፡ ኃጢአትንም ስናደርግ፣ ከፍቅሩ የተነሳ በገዛ መንገዳችን እንድንሄድ አልተወንም፡፡ ወደ ራሱም ይመልሰናል፡፡ ይቀጣናልም፡፡ ቅጣቱም፣ ቅዱሳት መጻሕፍት የገለጡትን ወላጅ ልጆቹን የሚቀጣበትን መንገድ ዓይነት ማለት ነው፡፡ ልጆቹ የሚጎዳቸውን ሲያደርጉና እኔ ካዘዝኳቸው ነገር ሲያፈነግጡ ዝም የምላቸው ከሆነ፣ ስለ እነርሱ ግድ የለኝም፣ አልወዳቸውምም ማለት ነው፡፡ በሰማይ ያለውም አባታችን፣ በልጁ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ይቀጣናል፣ ስለዚህም እኛ ክርስቶስን እንመስላለን፡፡ ቅጣቱ ለእኛ ለመልካም ነውና የእግዚአብሔርን ቅጣት ያልለመድን ከሆነ ነገሩ አስጊ ነው፡፡ ቅጣት ክፉ አይደለም፤ መልካም ነው፣ እግዚአብሔር ለልጆቹ ያለውን ፍቅር ይገልጣል፡፡ [ዶ/ር ስቴፋን ዌሉም]*

ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ሰላም ታላቅ የሆነውን በጎነቱን በማወጅና እርሱንም በማመስገን እንድናወድሰው ልባችንን ያነሳሳዋል፡፡ በጸሎትም ስለ ባህርያቱና ስለ ማንነቱ ቃልን እንድናወጣ አብርሆትን ይሰጠናል፡፡ በእኛ ሕይወት ውስጥ ስላደረጋቸው ታላላቅ ነገሮች እንድናሰላስል፣ እርሱን የምንወድበትንና የምንታዘዝበትን አዳዲስ መንገዶች እንድንረዳም ሊያበረታታን ይገባል፡፡ እናም አማኞች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ሰላም በዙሪያችን ላሉት ሁሉ በማሳሰብ እንድናበረታታ እና የማያምኑትም ከእርሱ ጋር ከታረቁ ሰላም እንደሚኖራቸው እንድናስገነዝብ ይቀሰቅሰናል፡፡

ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ሰላም እጃችንንም ለሥራ ሊያነሳሳው ይገባል፡፡ ከሰው ልጆችም ጋር ሰላምን ልንፈጥር ይገባናል፡፡ ለተቸገሩ በመርዳት እና በማኅበራዊ ፍትህና ግብረገባዊነት በመሳተፍ የእግዚአብሔርን ሰላማዊ መንግሥት በረከቶች ሁሉ ልንገልጥ ይገባል፡፡ ልባቸው የተሰበረባቸውንና ሰላምንና በረከትን በሕይወታቸው ያጡትን ልናፅናናና ልናማክር ይገባናል፡፡

ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ሰላም በተጨማሪም ስለ ታላቁ አምላካችንና አዳኛችን የበለጠ እንድናውቅና እንድንረዳ ሊያነሳሳን ይገባል፡፡ እርሱ የሚያስበውን በማሰብ ልቡናችን ከእግዚአብሔር መንገድ ጋር መስማማት እንዳለበት ቃሉ ይነግረናል፡፡ በእርሱ ብቁነት ላይ በሰላም ልናርፍ፣ በዚህ ዓለምም ላይ ብቻችንን እንደማይተወን በማወቅ ላለመጨነቅ ይልቁኑ እርሱ እንደሚወደንና እንደሚንከባከበንም በመረዳት በመተማመን ልንቀመጥ ይገባናል፡፡

የኢየሱስ ክህነታዊ የማስታረቅ አገልግሎት በሕይወታችን ተግባራዊ የሚሆንበት ሁለተኛ መንገድ በእግዚአብሔር ህዝብ መካከል በሚገለጠው ኅብረት ነው፡፡

## ኅብረት

በአዲስ ኪዳን ደጋግመው ከተገለጡት መሪ ጥቅሶች መካከል አንዱ እግዚአብሔርን የሚወድዱ ሁሉ እግዚአብሔር የሚወዳቸውን ሰዎች ይወዳሉ፡፡

ይህንንም በ1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 4 ቁጥር 21 ውስጥ እንዲህ እናነበዋለን፡

> እግዚአብሔርንም የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከእርሱ አለችን። (1ዮሐ 4፥21)

እግዚአብሔር ከአንድ ሰው ጋር ከታረቀ፣ እኛም ከዚያ ሰው ጋር ልንታረቅ ይገባናል፡፡

ከእግዚአብሔር ጋር የተቀበሉትን እርቅ እውቅና እንዲሰጡትና ከሌሎችም አማኞች ጋር በሚኖራቸው ኅብረት እንዲገልጡት ጳውሎስ አንባቢዎቹን ግድ የሚለው ለዚህ ነው፡፡ በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን፣ በአይሁድና በአህዛብ መካከል ያለውን ጥብቅ ግንኙነት ለማመልከት ይህንን ሃሳብ በተደጋጋሚ ይጠቀምበታል፡፡

በኤፌሶን ምዕራፍ 2 ከቁጥር 13 እስከ 16 የተናገረውን አድምጡ፡

> አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል።
> እርሱ ሰላማችን ነውና፤ ሁለቱን ያዋሐደ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰ፤ ይህም ከሁለታቸው አንድን አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ፥
> ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው። (ኤፌ 2፥13-16)

ተመሳሳይ የሆነውን በአንድነት ላይ የተፃፈውን ትኩረት ዮሐንስ ምዕራፍ 17 ቁጥር 23፤ ሮሜ ምዕራፍ 15 ቁጥር 5 እና በኤፌሶን ምዕራፍ 4 ከቁጥር 3 እስከ 13 ባሉት ስፍራዎችም ውስጥ እናገኘዋለን፡፡

የዘመናችን ቤተ ክርስቲያን በአይሁድና በአህዛብ መካከል ትክክለኛ ግንኙነት ከማድረግ አንፃር ችግር የሚገጥማት አልፎ አልፎ ነው፡፡ ከዚህ ጋር የሚመሳሰሉ በርካታ ችግሮች ግን አሉባት፡፡ ከብሔርተኝነት፣ ከጎሰኝነት፣ እና ከብሔራዊ ጠላትነት ጋር እንታገላለን፡፡ የኢየሱስም የማስታረቅ አገልግሎት በእነዚህ ነገሮች ዙሪያ ኅብረትን መመሥረትን እንድንከታተል ያግዘናል፡፡ ከክርስቶስ ጋር ባለን አንድነትም አማካይነት ከእግዚአብሔርና ከሌሎች ጋር እንታረቃለን፡፡ ይህም አንድነት በቤተክርስቲያን ውስጥ ባለን የእርስ በርስ ግንኙነት ይገለጣል፡፡ ይህም ማለት አንዳንድ ጊዜ እርስ በርስ የሚለያዩንን ነገሮች ወደ ጎን በማድረግ ቤተክርስቲያንን ወደ አንድነት ለማምጣት እግዚአብሔር ያለውን ግብ እንድንናፍቅና እንድንከታተለው ያደርገናል ማለት ነው፡፡

ከሰላምና ከአንድነት ባሻገር፣ ከክርስቶስ ክህነታዊ የማስታረቅ አገልግሎት የምንወስደው ሦስተኛ ተዛምዶ፣ በዓለም ውስጥ እኛም የማስታረቅን አገልግሎት እንድንፈፅም ተልዕኮ የተሰጠን መሆኑ ነው፡፡

## ተልዕኮ

የክርስቶስ ክህነታዊ የማስታረቅ አገልግሎት ገና አልተጠናቀቀም፡፡ መስዋዕትነቱ እርቅን አስገኝቷል አረጋግጧልም፡፡ ያ እርቅ ግን በመላው ዓለም ውስጥ ገና አልተፈፀመም፡፡ እንግዲያው፣ በዚህ የታሪክ እርከን ላይ፣ የእርሱን የማስታረቅ አገልግሎት እንድትፈፅም ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንን ሾሟታል፡፡ እኛ የእርሱ የማስታረቅ አምባሳደሮች ነን፡፡ ኃጢአተኞችን ከእግዚአብሔር ጋር ያስታረቀውን ወንጌል ማወጅ ሥራችን ነው፡፡

በ2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 5 ከቁጥር 18 እስከ 20 ጳውሎስ ተልዕኳችንን እንዴት እንደገለጠው አድምጡ፡

> ነገር ግን የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው፤
> እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ።
> እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልክተኞች ነን፤
> ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን። (2ቆሮ 5፥18-20)

የማስታረቅን አገልግሎት ለእግዚአብሔር የማቅረቡ ሥራ የቤተክርስቲያን ወሳኝ አገልግሎት ነው፡፡ እግዚአብሔር በክርስቶስ አማካይነት እኛን ካራሱ ጋር እንዳስታረቀንና አሁንም ዓለምን ከራሱ ጋር የማስታረቁን ሥራ እንደቀጠለ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ይነግራቸዋል፡፡ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ይታረቁ ዘንድ እንደ ክርስቶስ ተከታዮች ይህንን መልዕክት ለሌሎች መስበክ የእኛ ሃላፊነት ነው፡፡ ይህንንም በተቀዳሚነት የምናከናውነው፣ በክርስቶስ ሕይወት፣ ሞት፣ ትንሣኤና እርገት ኃጢአተኞች ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም እንደሚያገኙ መልካሙን የምሥራች በማወጅ ነው፡፡

የክርስቶስን ክህነታዊ የማስታረቅ አገልግሎት ከመስዋዕትነት እና ከማስታረቅ አንፃር ተመልክተናል፣ አሁን ደግሞ ወደ ኢየሱስ ክህነታዊ ምልጃ ዘመናዊ ተዛምዶ እንሸጋገራለን፡፡

## ምልጃ

የኢየሱስን ካህናዊ ምልጃ ዘመናዊ ተዛምዶዎች በሁለት ርዕሶች እንመረምረዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ስለ ራሳችን በእግዚአብሔር ፊት ልመና ማቅረብ እንድንችል አስችሎናል፡፡ ሁለተኛ፣ የክርስቶስ ምልጃ ለሌሎች ሰዎች ጠበቃ እንድንሆን ያስገድደናል፡፡ አስቀድመን ስለራሳችን መሻቶች ለእግዚአብሔር ልመና እንድናቀርብ እንዴት እንዳስቻለን እንመለከታለን፡፡

## ልመና

እንደተመለከትነው፣ በእኛ ምትክ ሆኖ ስለከፈለው መስዋዕት እግዚአብሔር አብን በማሳሰብ እና በዚያም መስዋዕትነት ምክንያት እግዚአብሔር ይቅር እንዲለንና እንዲባርከን ኢየሱስ ይማልድልናል፡፡ እግዚአብሔር አብ ልጁን ስለሚወድና መስዋዕቱንም ስለሚያከብር፣ ልጁ ስለኛ ለሚያቀርበው ምልጃ በጎ ምላሽ ይሰጣል፡፡ የክርስቶስን ካህናዊ ልመና ስለሚሰማ፣ ይቅርታ፣ ቅድስና፣ ሕይወትና ሌሎችም የድነት በረከቶች ያለማቋረጥ በእኛ ሕይወት ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

የዚህ ነገር አንዱ አንድምታ ስለ መሻቶቻችን በየዕለቱ ወደ አብ መቅረብ መቻላችን፣ ታላቁ ሊቀ ካህናችን ስለ እኛ ስለሚማልድ ፀሎታችንን እንደሚሰማ እናውቃለን፡፡ ይህንንም በኤፌሶን ምዕራፍ 3 ቁጥር 12፤ ዕብራውያን ምዕራፍ 10 ቁጥር 19 እና በሌሎችም በርካታ ስፍራዎች ውስጥ እናየዋለን፡፡

አንድ ምሳሌ ለመጥቀስ፣ ዕብራውያን ምዕራፍ 4 ከቁጥር 14 እስከ 16 አድምጡ፡

> እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን፥ ጸንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ።
> ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፥ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም።
> እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ። (ዕብ 4፥14-16)

የዕብራውያን ጸሐፊ እንዳመለከተው፣ ኢየሱስ "በሰማያት አልፏል" ፡፡ ያም ማለት፣ ስለ እኛ ሊማልድ በራሱ ደም ወደ ሰማያዊቷ መቅደስ ገብቷል፡፡ በእርሱም ምልጃ ምክንያት፣ እግዚአብሔር እንደሚቀበለን እናረጋግጣለን ደግሞም ወደ እርሱ ስንጸልይ ምህረትንና ጸጋን ሊሰጠን ይወድዳል፡፡

ልመናችን የተለመዱትን ማለትም የዕለት እንጀራን ወይንም ልብስና መጠለያን አሊያም እጅግ የጠለቀውን ይቅርታና ድነት የሚመለከት ቢሆንም እንኳን ፈጣሪያችንን ስለ ሁሉም መሻቶቻችን ልንለምነው እንችላለን፡፡ የትኛውም መሻት አንሶ ክርስቶስ በእኛ ምትክ ካቀረበው ምልጃ ክልል ውጪ ሊወድቅ አይችልም፡፡ ደግሞም የትኛውም መሻት ተልቆ የእርሱ መስዋዕትነት ሊሸፍነው አያዳግተውም፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ጸሎቶቻችንንና ሁሉንም መሻቶቻችን ደግሞም የጽድቅ ጥያቄዎቻችን ወደ አፍቃሪ አባታችን በድፍረትና በመተማመን ለማቅረብ ልንበረታታ ይገባናል፡፡

የክርስቶስ ምልጃ ስለ ራሳችን በእግዚአብሔር ፊት ልመና የምናቀርብበትን ድፍረትና ሙብት የሰጠን መሆኑን ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ለሌሎች ጠበቃ እንድንሆን እንዴት እንደሚያበረታታን እንመልከት፡፡

## ጠበቃ

> *ኢየሱስ የሚማልድ ከሆነ፣ ስለ ሌሎች ሰዎች ለመጸለይ ለምን እንቸገራለን? እንደማስበው ምክንያቱ "እኔን ተከተሉኝ" በሚሉት በሁለት ጣምራ ቃላት ተገልጧል፡፡ ኢየሱስ የሚማልድ ከሆነ፣ እንድትከተሉኝ እፈልጋለሁ ደግሞም እናንተም እንድትማልዱ እሻለሁ ብሏል፡፡ ደግሞም ጸሎቶቻችን ተፅዕኖ እንደሚፈጥሩም አምናለሁ፡፡ በተጨማሪም፣ ጸሎቶቻችን ተፅዕኖ መፍጠራቸው ብቻ ሳይሆን የማንጸልይ ከሆነ አንዳንድ ነገሮች የማይከናወኑበት ጊዜ እንደሚኖርም ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተምራሉ፡፡ ታዲያ፣ በጸሎት ልናምን*

*ይገባናልን? አዎን፡፡ ግን ለምን? ምክንያቱም ኢየሱስ ተከተሉኝ አለና ጸለየ፡፡ [ዶ/ር ማት ፍሬድማን]*

ከክርስቶስ ሰማያዊ ምልጃ ከምንማራቸው አስፈላጊ ትምህርቶች አንዱ በጸሎት ስለሌሎች ጠበቃ በመሆን የእርሱን ምሳሌነት ልንከተል የተገባ መሆኑ ነው፡፡ ስለ ሌሎች ያለን ፍቅርና ተቆርቋሪነት በእነርሱ ምትክ ሆነን እግዚአብሔርን ልንለምን፣ ባሉበት በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔር ምህረቱንና ፍቅሩን እንዲያሳያቸው እንድንጠይቅ ሊያበረታታን ይገባል፡፡

በኤፌሶን ምዕራፍ 6 ቁጥር 18 ውስጥ ጳውሎስ የጻፈውን አድምጡ፡

> በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ፤ (ኤፌ 6፥18)

በዚህ ስፍራ፣ ስለሌሎች ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርቡ ጳውሎስ አማኞችን ሁሉ ያዝዛል፡፡ ይህንን ስናደርግም፣ የእኛ ጥብቅና የሚመሠረተው ክርስቶስ ስለ እነርሱ በከፈለው መስዋዕትነት፣ ማለትም ኢየሱስ ስለ እኛ ከሚፈፅመው ጥብቅና ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡

> *ኢየሱስ ለምን ይጸልያል፣ መሻቶቼን ያውቃል፣ መሻቶቼንም ይረዳል፣ ታዲያ መማለድ ለምን ያስፈልገዋል? ብዬ ራሴን ስጠይቅ፣ በምልጃ መሠረት ውስጥ እንድን የእግዚአብሔርን ልብ የምናይበት ተምሳሊት አለ፣ ያም እርሱ የሚሸከም መሆኑ ነው፡፡ በትስጉተ እግዚአብሔር ሕይወት ውስጥ፣ በስላሴ ሕይወት ውስጥ፣ የሰውን ዘር ሸከም የሚቀበል፣ የሚሸከም ፍቅር አለ፡፡ የመስቀል መሠረቱ፣ ከኢየሱስ ጋር የምጓዘው ጉዞ መሠረቱ ያ ነው፡፡ ነገሩን ጌታ የነገረኝ በትዕዛዝ መልክ ነው፣ ምክንያቱም እውነታውን እንድረዳ ስለሚፈልግ ሲሆን፣ ይህን ብቻ ሳይሆን ሌሎችን በልቤ የምሸከምበትን ዕድልም ሰጥቶኛል፡፡ ነገሩን በዚህ መንገድ ካስቀመጥሁት፣ የእያንዳንዱ ሰው መሻት መልሱ የሚገኘው በሌላ ሰው ውስጥ ነው ማለት ነው፡፡ በእርግጥ የሁላችንም መሻት መልሱ ያለው በኢየሱስ ልብ ውስጥ ነው፡፡ እርሱም ደግሞ፣ በራሱ አምሳል ፈጥሮናል ደቀመዛሙርቱ እንድንሆንም ጠርቶናል፣ እናንተም ሌሎችን እንድትሸከሙ እሻለሁ፡፡ ልክ እንደ እስራኤል ካህናት እንድትሆኑ እሻለሁ ፡፡ ልክ እንደ አሮን በልባችሁ እንድትሸከሙ እሻለሁ፡፡ የዓለምን መሻት፣ ልክ እንደኔ በልባችሁ እንድትሸከሙ እሻለሁ ብሏል፡፡ እናም ምልጃ የእግዚአብሔር ልብ መግለጫ ነው፡፡ [ዶ/ር ቢል ዑሪ]*

የጥብቅና ምልጃዊ ፀሎት በየትኛውም የሕይወት ገፅታ ውስጥ ሊተገበር ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ እንደ ሮሜ ምዕራፍ 15 ቁጥር 30፤ ኤፌሶን ምዕራፍ 6 ቁጥር 20፤ ቆላስይስ ምዕራፍ 4 ቁጥር 4፤ 1ተሰሎንቄ ምዕራፍ 5 ቁጥር 25 እና ዕብራውያን ምዕራፍ 13 ቁጥር 19 በመሳሰሉት ስፍራዎች ለክርስቲያናዊ አገልግሎቶች ስኬት እንድንጸልይ ተበረታትተናል፡፡

1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 16 ስናነብብ ደግሞ፣ በመንፈሳዊ አደጋ ወይንም በኃጢአት ውስጥ ስላሉት እንድንፀልይ ተምረናል፡፡ ኢየሱስ በማቴዎስ ምዕራፍ 6 ቁጥር 13 እና በሉቃስ ምዕራፍ 22 ቁጥር 32 የተገለጠውን ምሳሌና ትምህርት ከተከተልን ሌሎች ከፈተና እንዲጠበቁ ልንጸልይ ገባናል፡፡ ስለጤንነታቸው ልንጸልይ፣ የልብና የአካል ጉዳታቸውን እግዚአብሔር እንዲፈውስ ልንጠይቅ ይገባናል፡፡

በያዕቆብ ምዕራፍ 5 ከቁጥር 14 እስከ 16 ያለውን መመሪያ አድምጡ፡

> ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ሽምግሌዎች ወደ እርሱ ይጥራ፤ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት።
> የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሣዋል፤ ኃጢአትንም ሠርቶ እንደ ሆነ ይሰረይለታል።
> እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ። ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች። (ያዕ 5፥14-16)

ስለ ሌሎች በጌታ ስም ጥብቅና ስንቆም፣ ያም ማለት፣ እነርሱ የጌታ መሆናቸውን በማሳሰብ ስለ እነርሱ ስንማልድ፣ ጌታም የእኛን ጥብቅና ይቀበላል ልመናችንንም ያደምጣል ማለት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ብዙ መሻት ላላቸው ጥብቅና የመቆምን ዕድል በሙላት ልንጠቀምበት ይገባናል፡፡

> *በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ላይ ፈፅሞ የማይናወጥ መተማመን አለኝ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን በአብ ዙፋን ፊት ስለ እኔና ስለ አማኞች ሁሉ እንደሚማልድም ምሉዕ መተማመን አለኝ፡፡ እኔን የሚያስፈልገኝ ሁሉ በክርስቶስ ውስጥ እንዳለ ምሉዕ መተማመን አለኝ፡፡ ሰዎች መሻት እንዳላቸው እያወቅሁ አለመጸለዬ የሚያመጣው ጉዳት አለን... እኔ ልንገራችሁ፣ በዚያ መሻት ውስጥ የሆነ ሰው ያንን የመሰለ ጥያቄ አይኖረውም፡፡ እኔም በትልቅ መሻት ውስጥ የነበርኩበት ጊዜ ነበር፡፡ በህክምና አነጋገር ሊበጠስ በደረሰ ቀጭን ገመድ ላይ ነበርሁ፡፡ በዚያን ወቅት የታመኑ ሰዎች ጸሎት እጅግ አስፈላጊ ነበር፡፡ በክርስቶስ ወንድሞቼና*

*እህቶቼ ስለ እኔ የጸለዩት ጸሎት እጅግ አስፈላጊ የሆነን ነገር በሕይወቴ እንደፈጸመ አውቃለሁ፡፡ ፍፁም የምተማመነው በእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና በከበረው ክርስቶስ ላይ ነው፣ ሆኖም ለክርስቶስ ያለን ታማኝነት ክርስቶስ ያዘዘንን እንድንፈፅም ያም ማለት ለታመኑት እንድንጸልይ ግድ ይለናል፡፡ የዚህንም አንድ አስፈላጊ ምክንያት አውቃለሁ፣ ያም መሻት እንዳላቸው ለማውቃቸው ስጸልይ የበለጠ ታማኝ ክርስቲያን የምሆን መሆኑ ነው፡፡ [ዶ/ር አር. አልበርት ሞህለር ትንሹ]*

በእርግጥም፣ በዕለታዊ የሕይወት ጉዳዮች ስለሌሎች ጥብቅና ልንቆም ይገባል፡፡ ለምሳሌ፣ ስለ ራሳችን የዕለት እንጀራ እንደምንጸልይ ሁሉ፣ ለሌሎችም ጥብቅና ልንቆም እና የዕለት እንጀራቸውን እንዲሰጣቸው እግዚአብሔርን ልንለምን ይገባናል፡፡ ለህዝቡም በረከትን እንዲሰጥ ማለትም፣ የጤና፣ የሥራ እና በሌሎችም ግንኙነቶቻቸው ስኬትን እንዲሰጣቸው ልንለምነው ይገባል፡፡ በግል ሕይወታችን ያሉ ሁኔታዎች በልባችን ውስጥ ሲከብዱ፣ እግዚአብሔር እንዲረዳን ልንለምን ይገባናል፡፡ በተመሳሳይም መንገድ፣ መሻቶቹ ትልቅም ሆኑ ትንሽ ስለሌሎችም መሻት ግድ ልንሰኝ ይገባናል፡፡

*ሰዎች በተደጋጋሚ ጊዜ የጸሎት ምሥጢር ግር ያሰኛቸዋል፡፡ መጸለይ ለምን ያስፈልገናል፡፡ እግዚአብሔር ሁሉን የሚያውቅ ከሆነና ኢየሱስም እየማለደ ከሆነ መጸለይ ለምን ያስፈልገናል? አንድ የጎደለ ነገር አለ፣ ወይስ ስለ ዓለምና ሰለሌሎች አለመጸለያችን የሚያመጣው ጉዳት አለን? እንደማስበው ለጥያቄው መልሱ አዎን ነው፣ አንድ የሚጎዳ ነገር አለ፣ ለምን እንደሆነም እነሆ፡- በመጀመሪያ፣ እግዚአብሔር እንድንጸልይ አዝዞናል፣ ባንማልድ እግዚአብሔርን አለመታዘዛችን ነው፡፡ በአንድ በኩል፣ ልናውቅ የሚገባን ነገር እርሱ ነው፡፡ ነገሩ የሚከናወንበትን ምሥጢር መረዳት አያስፈልገንም፡፡ እግዚአብሔር እንድንጸልይ አዞናል፡፡ እኛም የምንወደውና የምንታመነው ከሆነ፣ እንጸልያለን፡፡ ሁለተኛው ግን፣ እግዚአብሔር እንድንጸልይ ብቻ አላዘዘንም፣ ግን ነገሩን የበለጠ ምስጢር የሚያደርገው፣ በኢየሱስ ምልጃ ውስጥ የቅዱሳንንም ጸሎት ማካተቱ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ፊት የመዓዛ ሽታ ሆኖ የቅዱሳን ጸሎት እንደሚቀርብ የተገለጠበት የራዕይ መጽሐፍ ምስል በጣም ያስገርመኛል፡፡ የማንጸልይ ከሆነ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት እንደሚታወክ ዓይነት ሆኖ ነው የቀረበው ምክንያቱም እርሱ በዓለም ላይ እየሠራ ባለው ሥራ ውስጥ እኛም ተሳታፊ እንድንሆን ይፈልጋልና ነው፡፡ ከእርሱ ጋር አብረን በመሥራት ከእርሱ ጋር ወደጠለቀውና ሙሉ ወደ ሆነው ግንኙነት እንድንመጣ እየጋበዘን ነው፣*

*ጳውሎስም እርሱና ሌሎች በምልጃ አማካይነት የእግዚአብሔር ቤዝዎታዊ ሥራ ተካፋዮች እንደሆኑ ገልጦታል፡፡ እንዲህ ከሆነ ባናደርገው ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ይጎዳል፡፡ ሦስተኛ ግን፣ ከሁሉ የበለጠው ምሥጢር እነሆ፡፡ እግዚአብሔር ዓለምን የሚቤዠው ከውስጥ እርሱው በሚሰጠው ጸጋ እንጂ ከውጪ በሚከናወን ተግባር እንዳይሆን ወስኗል፡፡ እናም ከኢየሱስ ጋር ስንማልድ፣ እግዚአብሔር አንድ የማይፈልገውን ነገር እንዲያደርግ ልናሳምነው የምንሞክር ዓይነት አድርገን ልናስብ አይገባንም ወይንም በኢየሱስ ጸሎት ላይ እንደምንጨምር ልናስብ አይገባንም፡፡ ለዓለምም ሆነ ለራሳችን የምናቀርበውን ምልጃ በዚህ ዓይነት መመልከት ይገባናል፡፡ ሰዎች እግዚአብሔር እንዲገኙ በሚፈልጋቸው ስፍራ ላይ እንዲገኙና ሊቀበሉ የሚገባቸውን በረከትና ጸጋ እንዲቀበሉ ወደዚያ ልንስባቸው እንሞክራለን፡፡ እንግዲያው፣ እኛ የማንጸልይ ከሆነ በእግዚአብሔር ምስጢራዊ ዕቅድ ውስጥ አንድ የሚጎል ነገር አለ፣ ምክንያቱም የዳኑ ልጆቹን በፍጥረቱ ውስጥ ያስቀመጣቸው፣ የመጨረሻውን የመዳናቸውን ቀን እንዲጠባበቁ ብቻ ሳይሆን፣ ዓለምንና ሌሎችን እግዚአብሔር ሊያድናቸው ወደሚችልበት ስፍራ በመጥራቱና በመሳቡ ሥራ ላይ እንዲሳተፉም ጭምር ነው፡፡ [ዶ/ር ስቲቭ ብላከሞር]*

## 5. ማጠቃለያ

በካህኑ በኢየሱስ ላይ ባተኮረው በዚህ ትምህርት፣ የኢየሱስን አገልግሎት ብሉይ ኪዳናዊ ዳራ ተመልክተናል፣ ካህናትን የሾመው የእርሱ ህዝብ በረከቱን ወደ ሚቀበልበት ወደ ቅዱስ ህላዌው ለማስገባት እንዲያዘጋጁለትና እንዲመሩለት መሆኑን አይተናል፡፡ በተጨማሪም ኢየሱስ ታላቁ ሊቀ ካህናችን በመሆን ይህንን አገልግሎት በአዲስ ኪዳን እንዴት እንደፈፀመም ተመልክተናል፡፡ ደግሞም የኢየሱስን ክህነታዊ የአገልግሎት መርሆች በእኛ ዘመን እንዴት ተግባራዊ እንደምናደርጋቸውም ዳስሰናል፡፡

ኢየሱስ የመጽሐፍ ቅዱሳዊው የክህነት አገልግሎት ፍፃሜ ነው፡፡ እንደ ታላቅ ሊቀ ካህናችንም፣ በእግዚአብሔር የተቀደሰ ኅላዌ ውስጥ እንድንኖር ያዘጋጀናል ደግሞም አስገራሚ በሆነ መንገድ በእግዚአብሔር እንድንባረክ ያደርገናል፡፡ እነዚህም በረከቶች ለወደፊት ብቻ የተጠበቁ አይደሉም፡፡ በኢየሱስ መስዋዕትና ምልጃ በኩል፣ የዘላለም ሕይወትን ቅምሻ አሁን በዚህ፣ በምንኖርበት ዓለምም እንድናጣጥመው እግዚአብሔር አብ ፈቃዱ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ የክርስቶስ ተከታዮች በኢየሱስ ክህነታዊ አገልግሎት ደስ ሊሰኙና በራሱ በኢየሱስ አማካይነት ወደ እግዚአብሔር ቅዱስ ኅላዌ የሚገቡባትን ያችን ቀን ሊናፍቁ ይገባል፡፡ በዚህም ዘመን ኢየሱስ እንደ ታላቁ ሊቀ ካህናችን በሚሰጠን አገልግሎት ደግሞም በሰማያት ስለ እኛ አሁን በሚማልደው ልንታመንና ልንጠቀም ይገባናል፡፡